http://www.mudco.gov.et/web/guest/home

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT, HOUSING & CONSTRUCTION

# የ2006 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት

# የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

ሚያዚያ 2006
አዲስ አበባ

# ማውጫ


መግቢያ ........ 1

I. የቁልፍ ስራዎች /የማስፈጸም አቅም ግቦች (LEARNING AND GROWTH) ዕይታ፡- ........ 3

1. የለውጥ ሥራ አመራርና የአቅም ግንባታ ሥራዎቻችን፡- ........ 3

1.1. የከተማ የለውጥና የልማት ሠራዊት ግንባታን በተመለከተ፣ ........ 3

1.2. የለውጥ አተገባበር የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ፣ ........ 6

1.3. የመረጃና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራዎች፣ ........ 8

II. የዋና ዋና ተልዕኮዎች ግቦች(INTERNAL PROCESS) ዕይታ፡- ........ 10

2.1. የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች፡- ........ 10

ሀ) ለፈጻሚ አካላት የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና፣ ........ 17

ለ) አክስዮን ማህበሩን በማጠናከር ወደ ሥራ ከማስገባት አንጻር፣ ........ 18

2.2. የከተማ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች፡- ........ 20

2.2.1. መልካም አስተዳደርን በተመለከተ ........ 20

2.2.2. የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ ........ 21

2.2.3. የሕዝብ ተሳትፎና ያልተማከለ አስተዳደር ማሻሻያና ማጠናከሪያን በተመለከተ ........ 24

2.3. የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን፣ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች፡- ........ 25

2.4. የተቀናጀ የመኖሪያ ቤቶች ልማት ሥራዎች፡- ........ 32

2.4.1. የቤት ልማት ስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት ሥራ፣ ........ 32

2.4.2. የቤቶች እና የህንጻ ግንባታ አቅም ግንባታ ሥራ ........ 33

2.4.3. የቤቶች እና የህንጻ ግንባታ ግብዓት ጥናትና አቅርቦት ሥራ ........ 33

2.4.4. የቤቶችና የመንግሥት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሕንጻ ዲዛይን ዝግጅትና ትግበራ ሥራዎች፡- ........ 34

2.4.5. የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም አፈጻጸም፡- ........ 35

2.4.6. የቤቶች ማስተላለፍና የፋይናንስ ሥራዎች፣ ........ 36

2.4.7. የፌደራል የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር ሥራዎች፣ ........ 38

2.4.8. የከተማ ቤቶች መረጃ አስተዳዳር እና ድጋፍ ሥራዎች፣ ........ 40

2.5. የተቀናጀ የከተማ መሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች፡- ........ 40

2.6. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ስራዎች፡- ........ 41

2.7. የከተሞች ጽዳትና ውበት ሥርዓት ማሻሻያ ስራዎች፣ ........ 45

III. የሕዝብ ተጠቃሚነት ግቦች(CUSTOMER PERSPECTIVE) ዕይታ፡- ........ 48
3.1 በሚኒስቴር መስሪያቤቱ በሚሰጡ አገልግሎቶች የተገልጋይ እርካታን በተመለከተ፣ ........ 48
3.2 የትምህርታዊና ልማታዊ ኮሚኒኬሽንና የህዝብ ግንኙነት ስራ፣ ........ 49
3.3 የባለብዙ ዘርፍ ሥራዎች፣ ........ 49
IV. የተቋሙ የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት፣ ........ 50
V. ከሌሎች ተቋሞች ያለው ቅንጅታዊ አካሄድና ሥራ አፈጻጸም፣ ........ 51
VI. ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ ያለበት ሁኔታ፣ ........ 51
VII. በአፈጻጸም ሂደት ያገጠሙ ችግሮችና እየተወሰዱ ያሉ የመፍትሔ እርምጃዎች፡- ........ 52
VIII. ማጠቃለያ፡- ........ 54

## መግቢያ

የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በከተማ ልማት ዘርፍና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የተሰጠውን ሀገራዊ ልማት ኃላፊነት ለመወጣት በ2006 በጀት ዓመት በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ፕሮግራም፣ በቤቶች ልማት ፕሮግራም፣ በከተሞች መሠረተ-ልማት ፕሮግራም፣ በከተሞች መልካም አስተዳደር ፕሮግራም፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እና በለውጥ ሥራ አመራር ዙሪያ ሥራዎችን ለማከናወን ከሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንፃር አጣጥሞ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የበጀት ዓመቱ ዕቅድ በከተሞች አካባቢ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትን በማስወገድ ልማታዊ የፖለቲካል-ኢኮኖሚ ሥርዓት በመፍጠር ብቃት ያለውና በለውጥ ቅኝት የሚሰራ የልማት ሠራዊት መፍጠርን ቁልፍ ተግባር አድርጎ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማትን ማስፋፋት፣ ልማታዊ የከተማ መሬት አስተዳደር፣ የቤቶች ልማት ሥራ፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ አቅም ግንባታ እና ከተሞችን በሰው ኃይል በማጠናከር ፕላናቸውን የማስተግበርና የመሠረተ-ልማት አቅርቦት ሥራዎች ዋና ዋና ተግባራት ሆነው ተለይተዋል፡፡ በዚሁ መነሻነት በ2006 በጀት ዓመት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተጣሉ ግቦች የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም በዋና ዋና ሥራዎች ላይ በማተኮር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## I. የቁልፍ ስራዎች /የማስፈጸም አቅም ግቦች (Learning and Growth) ዕይታ፡-

### 1. የለውጥ ሥራ አመራርና የአቅም ግንባታ ሥራዎቻችን፡-

### 1.1. የከተማ የለውጥና የልማት ሠራዊት ግንባታን በተመለከተ፣

የከተማ የለውጥና የልማት ሠራዊት ከመገንባት አንጻር በዘጠኝ ወራት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት እና በዘርፉ ከሚኖሩት ሠራተኞች 65% የከተማ የለውጥና የልማት ሠራዊት ለማድረግ በታቀደው መሠረት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የለውጥ ሠራዊት ለመገንባት በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ለማከናወን የተናበበ አደረጃጀት የመፍጠር እና ዕቅድ የማናበብ ተግባራት አቅዷል፡፡ በዚህ መሠረት ባለፉት ዓመታት አደረጃጀት የማናበቡ ተግባር ከሞላ ጎደል ተጠናቋል፡፡ ዕቅድን በተመለከተ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዕቅድ ከክልሎች ጋር ተናቦ የመግባቢያ ሰነድ የመፈራረም ሥራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዘርፉ የለውጥና የልማት ሠራዊት ለመገንባት ሲካሄድ የነበረው ጥረት የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ እንዳይሆን የአደረጃጀት እና የአሰራር ሥርዓት ክፍተት ችግር የፈጠር መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የከተማ የልማት ሠራዊት ግንባታ ጋይድ ላይን የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡ ጋይድ

ላይኑ በሴክተር ደረጃ የለውጥ ሠራዊት ወጥ በሆነ አደረጃጀት እና በተናበበ የአሰራር ሥርዓት ለመምራት እንዲቻል የተዘጋጀ በመሆኑ ለአገሪቱ ከፍተኛ አመራሮች እና ለዘርፉ የበላይ አመራሮች በሦስት መድረኮች አማካኝነት ቀርቦ ግብዓት ተሰባስቦ እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በተለያዩ ጊዜ በተካሄዱ መድረኮች ለሠራተኞች ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡

ፈጻሚን በማዘጋጀት ረገድ አጠቃላይ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አመራሮች የተሳተፉበት የ7ቀናት መድረክ በማዘጋጀት የ2005 አፈጻጸምን በጥልቀት በገምገም በመልካም አፈጸጸሞች ላይ የመማማር እና ማነቆዎችን ለይቶ የማውጣት ተግባራት ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በ2006 ዕቅድ ላይ በመወያየት የማስተካከልና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች የመለየት ሥራ ተከናውኗል፡፡ የአጠቃላይ ሠራተኛውን በተመለከተ ሦስት ቀናት የፈጀ የአፈጻጸም ግምገማ የዕቅድ ዝግጅት መድረክ በየሥራ ክፍሎችና የለውጥና የልማት ቡድኖች ተካሄዷል፡፡ በመጨረሻም በበላይ አመራሩ የተመራ የአንድ ቀን የአጠቃላይ ሠራተኛ መድረክ በማዘጋጀት በየደረጃው በተለዩ የአፈጻጸም ደረጃዎች፣ ማነቆዎች፣ የ2006 ዕቅድ እና አፈጻጸም አቅጣጫ ላይ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

በተግባር ምዕራፍ በየደረጃው የንቅናቄ መድረኮችን ለመፍጠር፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር አምርረው የሚታገሉ ተኪ አመራሮችን ለማፍራት እና በተለይም ለአመራሮች የማነቆ አፈታት እና ሌሎች ልማታዊ አመለካከት የሚያዳብሩ ሥልጠናዎች ለመሥጠት ታቅዶ የነበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሠረት ላይ በዘርፍ ደረጃ የአራት ቀናት መድረክ በማካሄድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትና ከፍተኛ አመራሮችን በዘርፉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና እና ፕሮግራሞች ላይ እንዲወያዩ ተድርጓል፡፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መካከለኛ አመራሮች የለውጡን ዓላማና ፋይዳ በሚገባ ተገንዝበውና በአሰራር መመሪያዎች ላይ በቂ ክህሎት አዳብረው ከመፈጸምና ከማስፈጸም አንጻር የነበረባቸውን ክፍተት ለመሙላት በተያዘው ዕቅድ መሠረት 48 ለሚሆኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከለኛ አመራሮችና ባለሙያዎች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት፣ በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ሥርዓት (ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 9) በራስን ማብቃት ዕቅድ አዘገጃጀት ማንዋል፤ በለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት መመሪያ ላይ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ለውጡን በመምራትና በማስተባበር ረገድ ወሳኝ ሚና ካላቸው መምሪያዎች የተወጣጡ 21 መካከለኛ አመራሮች የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናትና የሚዛናዊ የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት ጽንሰ ሀሳብና ተቀናጅተው የሚተገበሩበት አግባብን በተመለከተ ክህሎት የሚያጎለበት የ10 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የሥልጠና መድረክ 15 ባለሙያዎች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት አካሄድ ላይ የሁለት ቀናት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል አዲስ በመቀጠር ወደ ሚኒስቴር መሥሪያ

ቤቱ የሚገቡ ሠራተኞች በለውጡ እና በለውጥ ሠራዊት ግንባታ ዓላማ፣ ፋይዳ እና አሰራር ላይ ግንዛቤ ጨብጠው ቶሎ ወደ ሥርዓቱ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ እንዲቻል በተያዘው ዕቅድ መሠረት ለ33 አዲስ ሠራተኞች የማስተዋወቂያ ሥልጠና ተሠጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ በሚ/ር መ/ቤቱ 56 አመራሮች የአመራርና ማነቆ አፈታት (Problem Solving) ለመሥጠት የተያዘው ዕቅድ ሥልጠናውን የሚሰጥ በቂ ክህሎት ያለው ባለሙያ ለማግኘት ባለመቻሉ ለማካሄድ አልተቻለም፡፡

ለፈጻሚ ተልዕኮ ሰጥቶ በአፈጻጸም ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረመልስ እየሰጡ በመሄድ የለውጥና የልማት ሠራዊቱን ለመገንባት እንዲቻል ተቋማዊው የውጤት ተኮር ዕቅድ በግብ ተኮር ተግባራት መንዝሮ በማውረድ ለእያንዳንዱ አመራርና ፈጻሚ ተልዕኮ ተሰጥቷል፡፡

ተከታታይነት ያለው የአፈጻጸም ድጋፍ በማድረግ ረገድ ሠራተኛው ተልዕኮውን ለመፈጸም የሚያስችለው አመለካከት እንዲጨብጥና ክህሎት እንዲያዳብር ለማድረግ የሚያስችል የሜንተሪንግ እና ኮቺንግ ሥርዓት በመዘርጋት ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህም አዳዲስ የሚቀጠሩ፣ በዝውውር የሚመጡ እና አፈጻጸማቸው የደከመ ሠራተኞችን ከጠንካሮች ጋር በማስተሳሰር አቅማቸውን ለመገንባት ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡ ሠራተኞች በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሚደረግላቸው ድጋፍ ባሻገር ዕርስ በርሳቸው እንዲማማሩ ለማድረግ በተዘረጋው ሥርዓት በ69 የለውጥና የልማት ቡድኖቻቸው አማካኝነት አመለካከትና ክህሎትን ለማዳበር የሚያስችሉ ርዕሶች በመምረጥ በየሳምንቱ ዕርስ በርስ ይማማራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የራስን ማብቃት ዕቅድ ያዘጋጁ ሲሆን አፈጻጸሙም በየሩብ ዓመቱ እየተገመገመ ግብረመልስ እየተሰጣቸው ይገኛል፡፡

የአፈጻጸም ክትትል፣ ግመገማና ግብረመልስን በተመለከተ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተደራጁት 69 የለውጥና የልማት ቡድኖች በየሳምንቱ በሚያደርጉት ስብሰባ ሳምንታዊ አፈጻጸማቸውን የመገምገምና የቀጣይ ሳምንት ሥራዎች የመከፋፈል ተግባር ያከናውናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት እና የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ግምገማዎችን አከናውነው በየሚመለከተው ኃላፊ ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡

የአፈጻጸም ምዘናን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ በዕቅድ በተያዘው መሠረት ሁለት ምዘናዎች ተካሂደዋል፡፡ በዚህም መሠረት በ2005 በጀት ዓመት 2ኛ ግማሽ ዓመት በሦስቱ የግምገማና ምዘና መሥፈርቶች (በውጤት ተኮር፣ ራስን በማብቃት፣ እንዲሁም በዙሪያ መለስ ግምገማ) መመዘን ከነበረባቸው 296 ተመዛኞች ውስጥ 34 አመራሮች እና 239 ፈጻሚዎች በድምሩ 273 ሠራተኞች ተመዝነዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ በላቀ አፈጻጸም ደረጃ (ደረጃ 4) የለም፣ 152(55.68%) ከፍተኛ አፈጻጸም (በደረጃ ሶስት)፣ 111(40.66%) ጥሩ አፈጻጸም (በደረጃ ሁለት)፣ 3(1.10%) ዝቅተኛ አፈጻጸም እና 7(2.56%) በጣም ዝቅተኛ አፈጻጸም ዉጤት አግኝተዋል፡፡ በ2006 በጀት ዓመት የወርሃዊ እና የሩብ ዓመት አፈጻጸምን

በለውጥና ልማት ቡድን ደረጃ እንዲከናወን በማድረግ የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ የ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የስራ አፈጻጸም ግምገማም የተከናወነ ሲሆን ውጤቱ በሚኒ ካቢኔ ተገምግሞ ከጸደቀ በኋላ ግልጽ የሚደረግ ይሆናል፡፡

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የለውጥ መሳሪያዎች በፌዴራልና በክልል 100% የተናበቡ በማድረግ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እና በማስፋፋት እንዲሁም የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ሥራዎችን በመስራት እና ምቹ የሥራ አካባቢ በመፍጠር በዘርፉ በየደረጃው በሚሰጡት አገልግሎቶች የተገልጋዮች እርካታ 90% እንዲደርስ የማድረግ፣ ለውጡን በትግል የሚመሩና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትንና ተግባራትን አምርረው የሚታገሉ 25% ተኪ አመራሮችን ማፍራት፣ ከሚፈጠረው ተኪ አመራር ውስጥ ደግሞ 25% ሴቶች እንዲሆኑ ማድረግን በተመለከተ በየሥራ ክፍሎቹ በሥራ አፈጻጸማቸው ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸውን ፈጻሚዎች የመለየትና በተለዩት ላይ መረጃ የመሰብሰብ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በማከናወን ተኪ አመራር ሊሆኑ የሚችሉ 40 ዕጩዎች የተለዩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 10 ሴቶች ናቸው፡፡ ተኪ አመራሮችን አጽድቆ የማብቃት ተግባር በቀጣይ ግማሽ ዓመት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 1.2. የለውጥ አተገባበር የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ፣

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወደ ተግባር የገቡትን የለውጥ መሣሪያዎች አፈጻጸም በየጊዜው በመከታተል፣ በመገምገምና ግብረ-መልስ በመስጠት የሥራ አፈጻጸም ውጤትና ግብረ-መልስ 100% በውጤት ተኮር የምዘና ስርዓት /BSC/ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ለማድረግ በተቋሙ የልማትና የለውጥ ስራዎቻችንን ውጤታማነት የሚያፋጥን የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል፡፡

በዚህም መሠረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ማንዋል ተዘጋጅቶ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተገባ ሲሆን በዚህም መሠረት በየሥራ ክፍሉ በወር ሁለት ጊዜ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በየወሩ ለሥራ ክፍሎቹ ግብረ-መልስ የመስጠት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የሥራ ክፍሉን የውጤት ተኮር ዕቅድ ለሠራተኞች በግብ ተኮር ተግባራት በማውረድ፣ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመትና የግማሽ ዓመት አፈጻጸም የመከታተል፣ የመገምገምና የመመዘን ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ተከናውነዋል፡፡ እንዲሁም ሣምንታዊ የዕርስ በርስ የመማማር ሥርዓት በለውጥና የልማት ቡድኖች አደረጃጀት መመሪያ ተደግፎ በሚገባ በተጠናከረ ሁኔታ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡

በዘጠኝ ወራት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚሰጡ አገልግሎቶች የተገልጋይ እርካታን 86% ማድረስ በተመለከተ በየደረጃው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ ለማድረግ በተገልጋዮች የሚቀርቡ ቅሬታዎች በደንቡና በመመሪያው መሰረት ምላሽ እንዲያገኙ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ የተገልጋይ ቅሬታ የሚነሳበት የሥራ ተቋራጮች፣ ባለሙያዎች፣ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ

የሥራ ክፍል ላይ በተገልጋዮች የሚቀርበውን ቅሬታ ለመፍታት እንዲቻል በበጀት ዓመቱ  በተዘጋጀው የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍቻ አጣዳፊ ዕቅድ መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም መሠረት የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍቻ አጣዳፊ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ የሥራ ክፍሉን አደረጃጀትና አሰራር ለማሻሻል እንዲቻል የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ የተሻሻለው ጥናት ተጠናቆ ወደ ሥራ እስኪገባ ድረስ ለችግሩ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ ደንበኞችን በበቂ መጠን ማስተናገድ የሚያስችል በቂ ስፋት ያለው ቢሮ በማዘጋጀት፣ አዳዲስ የፋይል ካቢኔቶች በግዥ በማሟላት ከ80ሺ የሚበልጡ ማህደሮች በአዲስ መልክ በማደራጀት፣ የሠራተኞች ዕጥረትን ለመፍታት ከሌሎች የሥራ ክፍሎች 24 ሠራተኞች በውስት በመመደብ እና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች በማሟላት በተሻሻለው አዲሱ የምዝገባ መመሪያ መሠረት ፈጣን አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል፡፡ እንዲሁም የደንበኞችን ቅሬታ ማስተናገድ ይቻል ዘንድ በምዝገባ መምሪያ የቅሬታና አስተያየት መቀበያ ዴስክ በመክፈት አንድ ባለሙያ ተመድቦ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በዚሁ የሥራ ክፍል ላይ ተገልጋዮች በአካል በመገኘትና በጽሁፍ ለሚያቀርቡት ቅሬታ፣ አቤቱታ ወይም ጥቆማን በመቀበል በመመሪያው መሠረት በመመርመርና በማጣራት ለተገልጋዩ ውሣኔውን የማሳወቅ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአስተያየት መሥጫ ሳጥኖች ውስጥ አስተያያታቸውን የሚሰጡ ተገልጋዮች ቁጥር በጣም አነስተኛ  ሆኖ ተግኝቷል፡፡

የ360 ዲግሪ ግምገማን ተገባራዊ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በየደረጃው ባሉ አደረጃጀቶች የ2005 በጀት ዓመት ተቋማዊ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ተካሂዷል እንዲሁም የ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ግምገማ ተከናውኗል፡፡ በዚህም ግምገማ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚገኙ የሥራ ክፍሎች የነበረውን የግቦች አፈጻጸም በመገምገም አፈጻጸማቸው (ከ80%) በታች ለሆኑ ግቦች የነበሩ ማነቆዎችን ከአመለካከት፣ ከክህሎት፣ ከግብዓት አቅርቦት፣ ከአሰራርና አደረጃጀት፣ ከክትትልና ድጋፍ ሥራዎች አንጻር የመለየት ሥራ ተከናውኗል፡፡

የመሰረታዊ አሠራር ሂደት ለውጥ /BPR እና የውጤት ተኮር ሥርዓት ግንባታ /BSC አተገባበርና ውጤት በየደረጃው በየወሩ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቀናጀ የለውጥ መሣሪያዎች አተገባበር ላይ በየወሩ ሁለት ጊዜ በመምሪያዎች ደረጃ ክትትል ሲደረግበት ቆይቷል፡፡ በዚህም የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሂደት የሥራ ክፍሎች በሚ/ር መ/ቤቱ የውጤት ተኮር ማስፈፀሚያ ማንዋል መሰረት የፈጻሚዎችን ውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀታቸውን፣ በዕቅዱ ላይ የጋራ ስምምነት መፈራረም እና አመታዊ ዕቅዱን መነሻ በማድረግ የፈጻሚዎች ወርሃዊና ሳምንታዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ መዘጋጀቱን እንዲሁም ወርሃዊ የውጤት ተኮር ዕቅድን በየሳምንቱ

ለፈጻሚዎች መከፋፈሉን፣ ይህንንም መሰረት በማድረግ በመምሪያዎች በየሳምንቱ የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ መደረጉን በተጨማሪም በአመራሩና በፈጻሚው ዕለታዊ የአፈጻጸም መረጃ ምዝገባና ሳምንታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ፣ በለውጥና በልማት ቡድኖች የዕርስ በርስ መማማር መደረጉን፣ ራስን የማብቃት ዕቅድ የማዘጋጀትና ወደ ትግበራ መገባቱን እንዲሁም በየወሩ የውጤት ተኮር ምዘና መከናወኑ፣ በየሩብ ዓመቱና በየግማሽ ዓመቱ የውጤት ተኮር፣ የዙሪያ መለስና ራስን የማብቃት ዕቅድና አፈጻጸም ምዘና መከናወኑን በተመለከተ በየወሩ ክትትል እየተደረገ የጽሁፍ ግብረመልስ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የሥራ አፈጻጸም ውጤትና ግብረ-መልስ 100% በውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት BSC ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግን በተመለከተ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከጥር 1/2004 ዓ.ም ጀምሮ የሚዛናዊ የውጤት ተኮር ሥርዓት በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ዓመታዊ ዕቅዱ በግብ እና በግብ ተኮር ተግባራት ተመንዝሮ ለእያንዳንዱ የሥራ ክፍል እና ሠራተኛ ወርዷል፡፡ በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የ2005 በጀት ዓመት የሁለተኛ ግማሽ ዓመት እንዲሁም በአጋማሹ ላይ ደግሞ የ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የተቋማዊ፣ የሠራተኞችና አመራሮች በውጤት ተኮር፣ በዙሪያ መለስና ራስን ማብቃት ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ መሠረት ተከናውኗል፡፡

### 1.3. የመረጃና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራዎች፣

በዘርፉ መሠረታዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለፕሮግራሞች ውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ ግምገማ የመረጃ ምንጭ የሚሆኑ 4 ጥናቶችን ለማካሄድ በታቀደው መሠረት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት እያበረከተ ያለውን ሚና በሞዴል የታገዘ እንዲሆን ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በ2005 በጀት ዓመት የተጀመረው ጥናት የተጠናቀቀ ሲሆን ጥናቱን ለማስተዋወቅ በቀጣይ አውደ ጥናት ይዘጋጃል፡፡ የከተሞች መሠረተ-ልማትና አገልግሎት አቅርቦትን እና ፍላጎትን የሚዳስስ ጥናት በአማካሪ ለማስጠናት በተያዘው ዕቅድ መሰረት የጥናት መረጃዎችን በማሰባሰብ ወደ ኮምፒውተር በማስገባት መረጃውን ለትንተና በመዘጋጀት ላይ ሲሆን የአፈጻጸም ደረጃው 70 በመቶ ደርሷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዘርፉን የአምስት ዓመታት የልማት ስራ ለመገምገም የሚያስችለውን አመታዊ ስታቲስቲካል አብስትራክት (2001-2005) በማጠናቀቅ እንዲሰራጭ ለማድረግ በታቀደው መሰረት የስታትስቲካል አብስትራክቱ ማካተት የሚገባውን ዋና ዋና መረጃዎች የማሰባሰብ ስራ ተከናውኖ የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን ሰነዱን አጠናቅቆ ለማሰራጨት የአርትዖትና የህትመት ስራ ይቀራል፡፡

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልል ካሉ የዘርፉ ተቋማት ጋር የጋራ ዕቅድ በማቀድ በአካባቢው ከሚገኘው የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ጋር በጋራ በመሆን ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ የወረዳ ኔት ተዘርግቶ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አግዟል፡፡ ከዚህ ውስጥ የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ በአማራና በአፋር ክልል ያሉት የዘርፉ ተቋማት የሎካል ኤሪያ ኔትወርክ ተዘርግቶላቸው አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የወረዳ ኔት የተዘረጋ ሲሆን የአማራና የአፋር የዘርፉ ተቋማት በቀሪው በጀት ዓመት ወራት እንደሚገባ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም የኦሮሚያ፣ የትግራይና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ስራ ያሉ የዘርፉ ተቋማት ቀደም ብሎ የወረዳ ኔት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

የሚኒስቴሩ መስሪያ ቤቱ ዌብ ፖርታል በሁሉም ክልል ያሉ የዘርፉ ቢሮዎችንና የ86 ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶችን ዌብ ሳይት የያዘ ሲሆን ይህንን ዌብ ፖርታል በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል በዚሁ በጀት ዓመት በመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለ66 ባለሙያዎች በዌብ ፖርታል አጠቃቀም ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 22 ለፌዴራል እና 44 በክልል ላሉ የዘርፉ ቢሮዎችና በከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ለሚገኙ ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም የዘርፉን ዌብ ፖርታል በአግባቡ ለማስተዳደርና ለመጠቀም እንዲቻል ሁሉም ባለሚና አካላት የሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት፣ በክልሉ የሚገኙ የዘርፉ ተቋማትና የከተማ አስተዳደሮች ጽ/ቤቶች ስር የሚገኙ ዌብ ሳይቶች መረጃዎችን በየወቅቱ በመጫን መረጃዎቹ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ኃላፊነታቸውንና ተግባራቸውን ማሳወቅ የሚያስችል መመሪያ ፀድቆ ሁሉም አካላት እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ /BPR/ እና የውጤት ተኮር ስርዓት ግንባታ (BSC) ትግበራ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ በሙከራ ለተያዙ ሶስት ቢሮ ተጠቃሚዎች የውጤት ተኮር የአውቶሜሽን ስራ የተጠናቀቀ ቢሆንም በሙከራ ትግበራ ወቅት የታዩት ችግሮች ለማስወገድ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመሆን የታዩትን ቴክኒካል ችግሮችን ለመፍታት እየተሰራ ነው፡፡ በመሆኑም በተመረጡ ሶስት ቢሮዎች የውጤት ተኮር ስራው በአውቶሜሽኑ እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቁ ወደ ሌሎች ቢሮዎች የማስፋት ስራው አልተጀመረም፡፡

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአቅርቦትና የግምጃ ቤት፣ የሰው ኃይል አስተዳደር እና የተቀናጀ የጠቅላላ አገልግሎት የመረጃ ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲለማ ታቅዶ የመረጃ ሥርዓት የማልማት ስራው ሙሉበሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የለማውን የመረጃ

ሥርዓት ወደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ፍላጐት በማምጣት ወደትግበራ ለመግባት ለፈጻሚ ባለሙያዎች ስልጠና በመሰጠት ላይ ነው፡፡

# II. የዋና ዋና ተልዕኮዎች ግቦች(Internal Process) ዕይታ፡-

## 2.1. የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች፡-

### 2.1.1. የአመለካከትና የክህሎት ግንባታ ሥራ፣

የልማት ሰራዊት ግንባታ ሥራዎችን ጋር በተያያዘ ከፌዴራል ኤጀንሲው እስከ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች 5,582 የባለሙያ አባላት ያካተተ 765 የዘርፉ ኮማንድ ፖስት፣ 9,203 አባላት ያሉዋቸው 1517 የልማት ቡድኖች እና 1,978 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል፡፡ ነባር አንቀሳቃሾችን በተመለከተ 511,037 አባላት ያሏቸው 31,127 የልማት ቡድኖች እና 87,627 አንድ ለአምስት አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን በዚህም ችግሮችና ማነቆዎችን በራሳቸው የመፍታት፣ አቅም የመገነባባት ጅምር እንቅስቃሴዎች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዘርፉ ስትራቴጅና የማስፈጸሚያ መመሪያዎች ላይ አመራሮችና ባለሙያዎች የጠራ ግንዛቤና ዕውቀት እንዲኖራቸው ለማስቻል በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ በድምሩ ለ3385 ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮችና ለ11343 ዝቅተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች የአመለካከትና የክህሎት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ የሴቶች ተሳተፎ ከከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች 401 ሲሆን የዝቅተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች 211 ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፌዴራል ደረጃ ከካይዘን ኢንስቲቲዩት ጋር በመተባበር ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ 221 ባለሙያዎች የካይዘን ስራ አመራር የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በኤጀንሲው ለሚገኙ 250 ባለሙያዎችና አመራሮች በጥቃቅንና አነስተኛ አንተርፕራይዞች ስትራቴጂና በተለያዩ የማስፈጸሚያ መመሪያዎችና ማንዋሎች ላይ በከፍተኛ ባለሙያዎች ለ3 ቀናት እንዲሁም ከሁሉም ክልሎች ለተውጣጡ 135 አመራርና ባለሙያዎች ለ3 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

### 2.1.2. የአቅም ግንባታ ፕሮጄክት ስራዎች አፈጻጸም፣

**የሴቶች ኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ፕሮግራም** በ 5 ዓመታት ውስጥ በዓለም ባንክ ድጋፍ 20,000 ሴት ኢንተርፕረነሮችን በክህሎት ስልጠና እና በፋይናንስ አቅርቦት የሚደግፍ ፕሮግራም ሲሆን በደቡብ፣ በትግራይ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ አስተዳደር እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ 45 ቱን በመምረጥ

በአገልግሎት አሰጣጣቸው የተሸሉ እንዲሆኑ የማዕከላቱን ጥገና የማከናወን፣ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎችን የማሟላት፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ሞተር ሳይክሎች የማቅረብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም 365 ለሚሆኑ የማዕከላቱ ኦፊሰሮች፣ አስፈጻሚ እና ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥቷል፡፡ ለተጠቃሚዎችም የክህሎት ስልጠና ለመስጠትና የ43 ሚሊየን ዶላር ብድር ለማሰራጨት የሚያስችል ዝግጅት ተጠናቆ ወደ ብድር አቅርቦት ስራ ተገብቷል፡፡

በአዲስ አበባ፣ አዳማና ባህር ዳር 1426 ሴት ኢንተርፕረነሮች ለብድርና ስልጠና ተመዘግበው በአዲስ አበባ 149 ሴቶች 45.6 ሚሊየን ብር፤ በባህር ዳር 31 ሴቶች 6.2 ሚሊየን ብር፤ በአዳማ 50 ሴቶች 16.1 ሚሊየን ብር ብድር አግኝተዋል፡፡ በድሬዳዋ የተመረጡት የአንድ ማእከል አገልግሎቶች የተጠቃሚዎችን ምዝገባ የጀመሩ ሲሆን ብድር የመሥጠቱ ሥራም ተጀምራል፡፡ይሁን እንጂ ለብድር የተዘጋጀው ብር 212,188,980.40 ውስጥ በጥቅም ላይ የዋለው አነስተኛ መሆኑን የኢትዮጵያ ልማት ባንክና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በመገምገምና የጋራ ውይይት በማካሄድ የሚሻሻልበት ሁኔታ ታይቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ማግኘት የሚያስችል የክህሎት ስልጠና ካሪኩለምና የሞጅሎች ዝግጅት በማከናወን ለቴ/ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ መምህራን የአሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጥ የአማካሪ ድርጅት ምርጫ ተከናውኖ በዓለም ባንክ በኩል ይሁንታ አግኝቷል፡፡

የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች የቢሮ ጥገና ከአዲስ አበባ ማዕከላት በስተቀር የሌሎች አምስት ከተሞች ተጠናቋል፡፡የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሰው ኃይል በቅጥር ለማሟላት በተደረገው ጥረት የሰው ኃይል የተሟላ ሲሆን የፕሮጀክቱ ስድስት ከተሞች የአስተባባሪዎች ቅጥር በሂደት ላይ ነው፡፡

በፕሮጀክቱ እንደ ችግር የታዩት የብድር አጠቃቀም፤ የአስፈጻሚዎች ስለፕሮጀክቱ ያላቸው ግንዛቤና የከተሞች አፈጻጸም ተመሳሳይነት መጓደል፤ የሴት ኢንተርፕረነሮች ስልጠና መዘግየት ሲሆኑ በቀጣይ በተሻለ መንገድ ለመምራት የሚመለከታቸው የከተማ አመራሮች ትኩረት የሚሻ መሆኑ ላይ ውይይት ተደርጎ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

**የኢትዮጵያ የኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ማዕከል** የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የአሰልጣኞች ስልጠና ወንዶች 60 ሴቶች 13 በድምሩ 73 የሰለጠኑ ሲሆን፣የንግድ ልማት አገልግሎት ሴቶች 32 ወንዶች 77 በድምሩ 109  እና በኢንተርፕርነርሽፕ ወንዶች 734 ሴቶች 369 በድምሩ 1413 ስልጠኞች በተለያዩ ዙሮች በአዲስ አበባ ከተለያዩ ኢንስቲቲዩቶች፣ ከመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ ከቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲዎችና ኮሌጆች፣ ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ ከሌሎች ፋይናንስ ተቋማት) እና ከግል/ ፖቴንሺያል ኢንተርፕረነርስ እና የክልል ከተሞችም በሐዋሳ፣ በአዳማ፣ በባህርዳር፣ ደሴ እና በመቀሌ በተለያዩ ዙሮች  በስልጠናው ፕሮግራም

ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ ከክልሎቹ የበላይ አመራሮች ጋር በመወያየት ቅርንጫፎቹን ለመክፈት የሚያስችሉ ስራዎች ተከናውኗል፡፡

**የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማት** (LED) **ፕሮግራም** በተመረጡ 4 ክልሎች በ27ቱ ከተሞች ዉስጥ የክላስተር ልማትን ለማከናወን ብሔራዊ የጥቃቅንና አነስተኛ ክላስተር ልማት መመሪያን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ አንድ የዓለም አቀፍ አማካሪ ተቀጥሮ ባዘጋጀዉ ረቂቅ መመሪያ ላይ የፌደራልና የክልል ፈጻሚና አጋር አካላት በተገኙበት ተገምግሞና ተስተካክሎ ከፀደቀ በኋላ እንዲታተም ተደርጓ ተሰራጭቷል፡፡ በክላስተር ልማት መመሪያው መሠረት የክላስተር መምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ በ4ቱም ክልሎች በፕሮገራሙ የታቀፉት ከተሞች አዋጪ ነዉ ብለዉ ያመኑባቸዉን ምርት ዓይነቶች አቅርበዉ ተወዳድረዋል፡፡ እያንድአንዱ ክልል ካለዉ ዕምቅ ሀብቱ እና ለሀገር ኢኮኖሚ ከሚያደርገዉ አስተዋጽኦ አኳያ አንድ አንድ ክላስተር መምረጥ ተችለዋል፡፡በዚህም መሠረት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል የሚዛን-አማን የፈራፍሬ ማቀነባበሪያ፣ በኦሮሚያ ብ/ክልል የቢሾፍቱ የዶሮ ዕርባታና የዶሮ ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ፣ በትግራይ ብ/ክልል የአዲግራት እንጨትና ብረታብረት ማምረቻ፣ እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልል የደሴ ጨርቃጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ክላስተሮች በየክልሎቹ በተቋቋሙ የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላት በተገኙበት ተመርጠዋል፡፡ ይህ ሥራ የክልሎችን አንጻራዊ ጠቀሜታ (comparative advantage) ከግምት ያስገባ ነው፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ክልሎች ከአዋጪነት አኳያ በተለያዩ ምረቶች ላይ የተሠማሩ ክላስተሮችን የመረጡ በመሆኑ በአንድ ክልል ከአንድ የምርት ክላስተር ላይ የሚገኝ ተሞክሮ እየተቀመረ በሌሎች ክልሎች እንዲሰፋ ይደረጋል፡፡ለዚህም በ4ቱ ክላስተሮች የአፈፃፀም ስትራተጂ የሚያዘጋጅ አንድ የአማካሪ ድርጅት የሚመረጥበት ቢጋር የተዘጋጀ ሲሆን፣ በቢጋሩ መሠረት ከቀረቡት ድርጅቶች መካከል ተሽሎ የተገኘ አንድ ድርጅት እንዲለይ ተደርጓል፡፡ሆኖም ግን በየደረጃው ያለ አመራር በባለቤትነት እንዲይዘው በማድረግ በቀጣይነት መደጋገፍ ይጠይቃል፡፡

በክትትልና ግምገማ ረገድ ላለፉት 9 ወራት በ27ቱ የ LED ከተሞች በአካል በመገኘት በብድር አሠረጫጨትና አመላለስ ላይ እንዲሁም በኢንተርፕራይዝ ልማት እና በሥራ ፈጠራ ላይ አስፈላጊዉ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## 2.1.3. የምሩቃንና ሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ እና ኦረንቴሽን፣

በ2006 በጀት ዓመት የስራ ፈላጊዎችን የምዝገባ መረጃ በተደራጀ ከልክ በቋሚነት ለመያዝና የመረጃ ጥራቱን ደረጃ ለማሻሻል በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የስራ ፈላጊዎች መመዝገቢያ ተዘጋጅቶ ለክልሎች ተሰራጭቷል፡፡ በዚህም መሰረት ወንድ 1,049,001 ሴት 743767 በድምሩ 1,795,768 ስራ ፈላጊዎች የተመዘገቡ ሲሆን ከተመዘገቡት ስራ ፈላጊዎች ውስጥ 41,298 የዩኒቨርስቲ፤ 310,010 የኮሌጅና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ሲሆኑ የተቀሩት 1,444,460 ስራ ፈላጊዎች በተለያየ የትምህርት

ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ከተመዘገቡት የምሩቃን ስራ ፈላጊዎች ውስጥ 25.3% ሴቶች ሲሆኑ በአጠቃላይ ከተመዘገቡትም 41.1% ሴቶች ናቸው፡፡ በዘርፉ ስለሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች ለ813,620 ስራ ፈላጊዎች የአመለካከት ግንዛቤ ፈጠራ የተደረገ ሲሆን ገለፃ ከተደረገላቸው ውስጥ 163,334 ያህሉ ምሩቃን ስራ ፈላጊዎች ናቸው፡፡ባለፉት 9 ወራት 39,935 ወንድ 24,645 ሴት በድምሩ 64,580 ምሩቃን የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

የሳውዲ አረቢያ ተመላሽ ዜጎችን ተቀብሎ አሰልጥኖ ወደ ስራ ከማስገባት አንጻር 6215 ወንድ 5412 ሴት በድምሩ 11627 ሥልጠና የወሰዱ ሲሆን 11531 ወንድ 7879 ሴት በድምሩ 19410 ዜጎች ተደራጅተው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡

### 2.1.4. የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራ፣

በዘጠኝ ወራት ውስጥ በመደበኛ 709,199 የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 963,806 (135.9%) የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን የስራ ዕድል ፈጠራው በዘርፍ ሲታይ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ 180,413 (81%)፣ ኮንስትራክሽን ሥራዎች 297,425 (170%)፣ በአገልግሎት 224,725 (171%)፣ በከተማ ግብርና 123,907 (137%) እና በንግድ 137,336 (228%) ነው፡፡ በመደበኛ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ ቋሚ 722,855 (75%) ጊዜያዊ 240,951 (25%) ነው፡፡ ከተፈጠረው ስራ ዕድል ውስጥ 570,862 (59.23%) ወንድ ሲሆን 392,944 (40.77%) ሴቶች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ በመንግስት ፕሮጀክቶች 750,000 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ750,117(100%)፣ ሰዎች የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን ከተፈጠረው ስራ ዕድል ውስጥ 450,070 (60%) ወንድ ሲሆን 300,047 (40%) ሴቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በመደበኛና በመንግስት ፕሮጀክቶች የተፈጠረው የሥራ ዕድል ወንድ 1,020,932፣ ሴት 692,991 በድምሩ ለ1,713,923 ሰዎች የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡የሴቶች ተጠቃሚነት 40.43% ደርሷል፡፡

### 2.1.5. የተደረጉ ድጋፎች፣

ለነባርና አዲስ አንቀሳቃሾች እንደ የዕድገት ደረጃቸው በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትና በተለያዩ ተቋማት የቴክኒክ ክህሎት ክፍተት ማሚያ ሥልጠና እና የኢንተርፕርነርሺፕና የንግድ ሥራ አመራር ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ለኢንተርፕራይዞች ከሚሰጡ ዋና ዋና ድጋፎች ውስጥ አንዱ ነው ፡፡ በዚህ መሰረት በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ በንግድ ሥራ አመራር 1,090,710 አንቀሳቃሾችን ለማልሰጠን ታቅዶ 575,108 (53%) አንቀሳቃሾች የሰለጠኑ ሲሆን በተመሳሳይ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና 540,239 አንቀሳቃሾችን ለማልሰጠን ታቅዶ 730,182 (135.2%) አንቀሳቃሾችን ማሰልጠን ተችሏል፡፡

የመስሪያና የመሸጫ ቦታ አቅርቦትን በተመለከተ በ2006 ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለአንቀሳቃሾች አገልግሎት የሚውል 35,180,949 ካሬ ሜትር ቦታ በማዘጋጀት፣ 6,499 ሼዶችንና 224 ህንጻዎችን ለመገንባት ታቅዶ 14,460,887.39 ሜትር ካሬ ቦታ በማዘጋጀት 4685 ሼዶችንና 275 ህንጻዎችን መገንባት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም በመሬት ዝግጅት 41% በሼድ 73% ህንጻ ግንባታ 123% ይሆናል፡፡በዚህም 225,618 አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

የገበያ ትስስርን በተመለከተ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶች እና አገልግሎቶች የሀገር ውስጥ ገበያ ትስስር በመፍጠርና በማስተሳሰር ብር 7,763,277,512.5 የገበያ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ብር 6,742,202,361.14 (86.85%) ለ 1,007,411 አንቀሳቃሾች ለመፍጠር ተችሏል፡፡ አንድ አገር አቀፍ የ ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤግዚቢሽንና ባዛር ተዘጋጅቶ 153 ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና 4 ነጋዴ ሴቶችን በአጠቃላይ 157 ኢንተርፕራዞች 6 ልዩ ልዩ ተቋማት ተሳትፈውበታል፤ 30,000 ጎብኝዎች ተጎብኝቶ የብር 6,000,000 (ስድስት ሚሊዮን ብር) የገበያ ትስስር መፍጠር ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2006 ዓ.ም በዘጠኝ ወራት ውስጥ 304 ሚሊዮን ብር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ምርቶች ለዉጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተገኘዉ መረጃ መሰረት ብር 263,860,006 የሚያወጡ ምርቶች ለዉጭ አገር ገበያ መቅረባቸዉ ተረጋግጧል፡፡ አፈፃፀሙም 82.99% ነው፡፡

የፋይናንስ አቅርቦትን በተመለከተ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ወደ ሥራ ለሚገቡ አዲስና ነባር አንቀሳቃሾች ብር 3,377,002,998.12 የብድር አገልግሎት ለማመቻቸት ታቅዶ ብር 2,355,336,577.48 (70%) ለአንቀሳቃሾች ብድር ማመቻቸት ተችሏል፡፡ የብድር ማስመለስ እንቅስቃሴን በተመለከተም በበጀት ዓመት ሊመለስ ከሚገባው ብር 2,235,889,190 ለማስመለስ ታቅዶ ብር 1,602,021,318.26 (71.65%) ተመላሽ ሆኗል፡፡ እንዲሁም በዘርፉ አንቀሣቃሾችና ተማሪዎች ብር 3,084,283,084.46 ለማስቆጠብ ታቅዶ ብር 3,598,927,113.57 (116.7%) (ማስቆጠብ ተችሏል፡፡ በኦሮሚያና በሀረሪ ክልል የሚገኙ 1536 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብር 211,543 ትምህርት ላይ እያሉ ቁጠባ አድርገዋል፡፡

ለኢንተርፕራይዞች የአደረጃጀት ድጋፍና ህጋዊነት ከመስጠት አኳያ በተለያዩ ዓይነቶች አደረጃጀቶች 70,500 ኢንተርፕራይዞችን ለማደራጀት ታቅዶ 89,253 (58.4%)ያህል ኢንተርፕራይዞች ሊደራጁ ችለዋል፡፡ 180 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ለማጠናከር ታቅዶ በሴቶች ኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ፕሮግራም በደቡብ፣ በትግራይ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ አስተዳደር እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ የአንድ ማዕከል አግልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ 45ቱን በመምረጥ በአገልግሎት አሠጣጣቸው የተሻሉ እንዲሆኑ የማዕከላቱን ጥገና የማከናወን፣ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎችን የማሟላት፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ሞተር

ሳይክሎች የማቅረብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም 316 የአንድ ማዕከላትን ለማጠናከር ታቅዶ 463 በሰው ሀይልና በማቴሪያል የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡ የማዕከላቱን ተደራሽነት ለማሳደግም በ9 ወሩ 100 አዲስ ማዕከላትን ለማቋቋም ታቅዶ 144 ተጨማሪ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች እንዲከፈቱ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ነባሮቹን ጨምሮ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ በአጠቃላይ 1,242 የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎች ተደራጅተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

## 2.1.6. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰር፣

በአመራሩና በባለሙያ ደረጃ የመስክ ዕይታ በማድረግ በሁሉም ክልሎች ለትስስሩ ምቹ ሁኔታዎች ባሉባቸው ከተሞች የተጀመረውን የትስስር መፍጠር ሥራ ያለበትን ደረጃ በመረዳትና በማስረዳት እና ያሉትን ክፍተቶች በመለየት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል፤ በዚህም በኦሮሚያ 513፣ አማራ 771፣ በደቡብ 391፣ በትግራይ 167፣ በአዲስ አበባ 719፣ በአጠቃላይ 2561 ለሚሆኑ አመራሮች፣ ለባለሙያዎችና ኢንተርፕራይዞች ጋር ውይይት ለማድረግ ተችሏል፡፡

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰርን በማስመልከት የተሞክሮ ልውውጥ ማድረግ ተጀምሯል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካካለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ለማስተሳሰር በ2006 በጀት ዓመት በተጠናከረ ሁኔታ እንቅስቃሴ መደረግ በመቻሉ በአንዳንድ ከተሞች የምርት፣ የግብዓት አቅርቦት እና የኢንዱስትሪ ውስጥ የሥራ ዕድል ፈጠራ ትስስር የመፍጠር ጅምር እንቅስቃሴዎች እየታዩ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የጥቁር አባይ ጫማ ፋብሪካ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ ሁለት የቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንተርፕራይዞች ጋር የምርት ትስስር በመፍጠር ወደ ውጭ ሀገር ኤክስፖርት የሚደረግ ጫማ የላይኛውን ክፍል በመስፋት ሥራ በንዑስ ተቋራጭነት ተሰጥቷቸው እየሠሩ ሲሆን ኢንተርፕራይዞቹ እያንዳንዳቸው ከ2000 በላይ የጥንድ ጫማ የላይኛውን ክፍል ሰፍተው ለፋብሪካው አስረክበዋል፡፡ በዚህ ትስስር ኢንተርፕራይዞቹ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር ከመተዋወቅና ተጨማሪ የጫማ አመራረት ክህሎት ከማግኘታቸውም በላይ አስተማማኝ የሆነ ገበያ ማግኘታቸውን ገልጸዋል፡፡ በፋብሪካው በኩልም ለተጨማሪ ምርት የሚያወጣውን የማስፋፊያ፣የሰው ኃይል ቅጥር፣ የሱፐርቪዥን እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችን ከመቀነሱም በላይ ከደምበኛ የተሰጡትን ሥራዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በሚፈለገው መጠን ለማቅረብ እንዳስቻለው የፋብሪካው ኃላፊዎች ተናግረዋል፡፡ በሂደትም ኢንተርፕራይዞቹ አንዳንድ የሚጎድሏቸውን ዘመናዊ የማምረቻ መሳሪያዎች (ባለ 3 መርፌ የቆዳ መስፊያ ማሽን) በሚያሟሉበት ወቅት እና ሥራዎች እየተስፋፉ ሲሄዱ ተጨማሪ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ሥራው የሚያስገቡ መሆኑ ታይቷል፡፡

በግብዓት አቅርቦት ከተፈጠሩ ትስስሮች መካከል በአዲስ አበባ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ለሚገኙ የሹራብ ሥራ ኢንተርፕራይዞች ከሳይገን ዲማ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የተለያዩ የሹራብ ሥራ ክሮችን በተመጣጣኝ ዋጋ በመግዛት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

አነዚህን ተሞክሮዎች ከድሬዳዋ አስተዳደር የመጡ 9 አመራር፣ ባለሙያዎችና ኢንተርፕራይዞች ካላይ የተጠቀሱት ጅምር ሥራዎችን እና አጠቃላይ በትስስሩ ዙሪያ እየተደረጉ ያሉትን እንቅስቃሴዎች ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ በአካል ኢንተርፕራይዞች ዘንድ እና ፋብሪካዎቹ ጋር በመሄደ ተዘዋውረው አሰራሩን አስመልክቶ ተሞክሮ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

## 2.1.7. የፌደራል ተቋማት አፈጻጸም፣

ከኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት ጋር ባለን የጋራ ዕቅድ መሰረት ሳይገን ዲማ ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማህበር በተፈጠረው የገበያና የምርት ትስስር 6,541,455.87 ብር ዋጋ ያለው 62.179 ሺህ ኪሎ ግራም ድርና ማግ እንዲሁም 15000 ሜትር ጨርቅ በዘርፉ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማቅረብ ተችሏል፡፡ አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበር ተደራጅተው በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱ ኢንተርፕራይዞች ጋር በተፈጠረው የገበያና የምርት ትስስር 466,000 ብር ዋጋ ያለው 104,510 ኪ.ግ. ተረፈ ምርት ማቅረብ ችሏል፡፡ ናስ ፉድስ ድሬደዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የ12,829 ብር የጥጥ ክር ማቅረብ ችሏል፡፡

ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር ባለን የጋራ ዕቅድ መሰረት በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ ትግራይ፣ አዲስ አበባና ድሬደዋ 1500 አንቀሳቃሾች ከምርቶቻቸው ጋር በተያያዘ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በኮንስትራክሽን፣ አበግሮፕሮሰሲንግ ፣ ጨርቃጨርቅና ቆዳ ኬሚካልና ኬሚካል ውጤቶች ዘርፎች ለ1027 ወንድ እና ለ837 ሴት በድምሩ 1864 ስልጠና ያገኙ ሲሆን፣ በእነዚሁ ክልሎችና ዘርፎች ለ500 የTVET መምህራን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት ታቅዶ ለ172 ወንድና ለ67 ሴት ለ TVET መምህራን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ የአዲስ አበባ፣አማራና፣ደቡብ ክልሎች በስልጠናው ለመሳተፍ ፍላጎት ማነስ ታይቷል፡፡ ደረጃ ላልተሰጣቸው ምርቶች ደረጃዎች እንዲወጣላቸው በታቀደው መሠረት የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ዝርዝር ተፈላጊ ደረጃዎችን ለመስጠት በወጥ ቁሌት፣ በዶሮ ቀይ ወጥ ፣ በስጋ ቀይ ወጥ፣ በሽሮ በርበሬ ዱቄትና የማር ጠጅ የረቂቅ ደረጃ ዝግጅት ተጀምሯል፡፡

በኮንስትራክሽን በአግሮፕሮሰሲንግ በቆዳና ጨርቃጨርቅ ምርት ስራ ለተሠማሩ 170 ኢንተርፕራዞች የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ምርቶቻቸውን በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ሰርቲፋይድ እንዲሆኑ ማድረግ ሲሆን የኢንተፕራይዞቹ ምርቶች ለሰርተፍኬሽን ብቁ እንዲሆን ለ31

ኢንተርፕራይዞች የቴክኒክ ድጋፍ የተሠጠ ሲሆን የፐሪካስት በታይልስ በእንጀራና ማር ምርት ዘርፎች ከኢንተፐራይዞቹ የግንዛቤ ማነስ ምክንያት የተፈለገውን ውጤት ማግኘት አልተቻለም፡፡ በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ሥር በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች ለ19108 አንቀሳቃሾች ትስስር ተፈጥሯል፡፡

## 2.1.8. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ለማስተግበር በተደረገ ድጋፍና ክትትል የተገኘ ውጤት፣

### ሀ) ለፈጻሚ አካላት የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና፣

i. **አማራ ክልል** በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት መመሪያ ላይ እና በአጠቃላይ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ልማት ጋር ተያይዞ በተመረጡ 7 ከተሞች ለ85 (ወንድ 76 ሴት 9) አመራሮች፣ ለ405 (ወንድ 245 እና ሴት 160) ባለሙያዎች እና ለ227 (ወንድ 205 ሴት 22) አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በአጠቃላይ ለ771 (ወንድ 529 ሴት 188) ፈጻሚ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት በቀጣይ ለሥራው ዝግጁ እንዲሆኑ እና የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ለማከናወን በቅንጅት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

በተመረጡ ከተሞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናው ላይ ከተሳተፉት 227 ኢንተርፕራይዞች ውስጥ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ያላቸው 147 ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀውን ቅጽ ላይ የካፒታል ዕቃ ፍላጎታቸውን የገለጹ ሲሆን በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የካፒታል ዕቃዎችን ለማምረት አቅም ያላቸው ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ያላቸውን አቅም ለማየት በተከናወነው ሥራ በ7 ከተሞች ከተመረጡ 93 አብዢ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ አቅም ያላቸው 43 የሚሆኑትን በአካል በሥራ ቦታቸው በመገኘት ያላቸውን የሰው ኃይል፣ የማሽነሪ እና የፋይናንስ አቅም ተለይቷል፡፡ በተጨማሪም ያለባቸውን ሲሆን ክፍተት በመለየት በከተማው ለሚገኙ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና አስፈጻሚ አካላት በቅንጅት ክፍተቱ እንዲሞላ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

ii. **አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር** በ10 ክፍለ ከተሞች ለሚገኙ 102 አመራርና ባለሙያዎች፣ እነዲሁም 617 ኢንተርፕራይዞች በድምሩ ለ719 ሰው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ከተሰጣቸው 617 ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 300 የሚሆኑት የንግድ ሥራ ዕቅድ በማቅረብ የካፒታል ዕቃ ፍላጎታቸውን ገልጸዋል፡፡

iii. **የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል** በክልሉ በተመረጡ 5 ከተሞች ለሚገኙ 180 አመራርና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም 513 ኢንተርፕራይዞች በድምሩ ለ693 ሰው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ከተሰጣቸው 513 ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 198 (ከ4 ከተሞች የተገኘ መረጃ ነው) የሚሆኑት ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፍላጎታቸውን ገልጸዋል፡፡ የካፒታል

ዕቃዎችን ለማምረት አቅም ያላቸው አብዢ ኢንተርፐራይዞችን ከመለየት አንጻር 61 አብዢ ኢንተርፕራይዞች ተለይተዋል፡፡

iv. **የትግራይ ብሄራዊ ክልል** በሰባት ከተሞች ለሚገኙ 154 ኃላፊና ባለሙያዎችና በክልል ደረጃ ለ13 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

v. **የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል** በአምስት ከተሞች (በሀዋሳ፣በዲላ፣በአርባ ምንጭ፣ በወላይታ ሶዶና በሆሳዕና) ከተሞች በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራር ስርዓትና በፍሌክሴብል ወርክሾፕ ላይ በአምስቱ ከተሞች ለ138 አመራርና ባለሞያዎች እንዲሁም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ ለሚሆኑ 253 የኢንተርፕራይዝ ተወካዮች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል በአምስቱ ከተሞች የመሳሪያ ሊዝ ተጠቃሚ የሚሆኑ 215 ኢንተርፕራይዞች ተለይተዋል፡፡

ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አክስዮን ማህበር የማምረቻ መሳሪያ ሊያቀርቡ የሚችሉ አብዢ እንተርፕራይዞችን በመለየት በኩልም በሶዶ 5 በሆሳዕና 6 በሀዋሳ 15 ኢንተርፕራይዞች የተለያዩ የማምረቻ መሳሪያዎችን ለማምረት አቅም ያለቸው መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን በቀጣይ የክልሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ክፍተታቸውን በማየት ስልጠና እንዲሰጣቸው መግባባት ላይ ተደርሷል፤ በአምስቱም ከተሞች ለተርኒኪ ፕሮጀክት ግንባታ የሚሆን ቦታ ተዘገጅቷል፣ በየከተሞቹ ለሚገነቡ ወርክ ሾፖች ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር ውል ተፈራርመዋል፡፡

## ለ) አክስዮን ማህበሩን በማጠናከር ወደ ሥራ ከማስገባት አንጻር፣

i. **አማራ ክልል** ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተሟልተው መቅረብ ያለባቸውን ሠነዶችና መረጃዎች አሟልቶ በማቅረብ አክሲዮን ማህበሩ የንግድ ፈቃዱን ከብሔራዊ ባንክ ለማግኘት ችሏል፡፡ በዋናው መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደረጃ መሟላት ያለባቸውን ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ለማሟላት የሚያስችለውን የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያ በማዘጋጀት እና በቦርድ በማጸደቅ በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ መሟላት ካለባቸው የስራ ሃላፊዎች መካከል ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ የፋይናስ ደጋፊ የስራ ሂደት ስራ አስኪያጅ እና የሰው ሃይል አስተዳደርና ፋሲሊቲ ደጋፊ የስራ ሂደት ስራ አስኪያጅ የማሟላት ስራ ተከናውኗል፡፡ በዋናው መስሪያ ቤት ደረጃ ለሚኖሩት ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች ለስራ የሚያፈልጉ ቢሮዎችን እና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች የማሟላት ተግባርም ከሞላ ጎደል በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

በቦርዱ ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ካለው የአስተዳደር መመሪያ በተጨማሪ የኦፐሬሽን፣ የፋይናንስ፣ የኦዲት፣ የግዥ እና የሪስክ መመሪያዎችን በማዘጋጀት በቦርድ ለማጸደቅ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

ከክልሉ የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራዞች ልማት ኤጀንሲ ቢሮ እና ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ጋር በመቀናጀት በክላስተር ማዕከላ በመግባት በማኑፋቸሪንግ ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አነስተኛና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራዞች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሳሪያዎችን ለመግዛ የጨረታ ሂደት እየተከናወነ ያለበት ሁኔታ ከመኖሩ በተጨማሪ የክላስተር ማዕከላት ከተገነቡባቸው የክልሉ 11 ዋና ዋና ከተሞች በ7ቱ የፌዴራ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ልማት ኤጀንሲ፣ የኢፌዲሪ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን፣ የክልሉ የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራዞች ልማት ቢሮ  እና የዋልያ የካፒታ ዕቃ ፋይናስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበር ተወካዮች የተሳተፉበት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ለተመረጡ ከተሞች የዞን አመራሮች፣ የከተማ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ፈላጊ ኢንተርፕራዞች  በተሰጠው የግንዛቤ ፈጠራ ስልጠና ላይ አክስዮን ማህበሩን የማስተዋወቅ ስራ ለማከናወን ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ መንግስት ዋስትና ከኢትዮጵ ንግድ ባንክ በብድር የሚገኘውን ገንዘብ ለመጠቀም እንዲቻል በባንኩ እንዲሟሉ የተጠየቁ መረጃዎችን በማሟላት የብድር ውል ስምምነት ከኢትዮጵያ ንግድ ባክ ጋር ለመዋዋል መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች ለማሟላት ጥረት በማድረግ ላይ ከመሆኑም በተጨማሪ ከተሞች ለአክሲዮን ማህበሩ በጽህፈት ቤትነት የሚያገለግሉ ቢሮዎችን እና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶችን ከወዲሁ ማመቻቸት የጀመሩ ሲሆን በቀጣይም የሰው ሃይሉን በየደረጃው በቅጥር ለማሟላት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡የፋይናንስ አቅርቦት ተጠናቋል፡፡

ii. **አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር** ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተሟልተው መቅረብ ያለባቸውን ሠነዶችና መረጃዎች አሟልቶ በማቅረብ  አክሲዮን ማህበሩ የንግድ ፈቃዱን ከብሔራዊ ባንክ ለማግኘት ችሏል፡፡ የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያ በማዘጋጀት እና  በቦርድ በማጸደቅ 6 የሚሆኑ አመራር እና ባለሙያዎች የተቀጠሩ ሲሆን የቀሩትን ባሙያዎች ለማሟላት ቅጥር እየተከናወነ ይገኛል፡፡ለአክስዮን ማህበሩ ለስራ የሚያፈልጉ ቢሮዎችን እና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች የማሟላት ተግባርም ከሞላ ጎደል በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ሁለት ተሽከርካሪ ለአክስዮን ማህበሩ የተሰጠ ሲሆን ተጨማሪ ሁለት በግዢ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ የፋይናንስ አቅርቦት ተጠናቋል፡፡ ከብረታብረት ኮረፖሬሽን ጋር በጋራ መስራት ተጀምሯል፡፡

iii. **የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል** ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተሟልተው መቅረብ ያለባቸውን ሠነዶችና መረጃዎች አሟልቶ በማቅረብ በብሔራዊ ባንክ ሰነዶቹ ከተገመገሙ በኋላ ወደ ውልና ማስረጃ ተልኳል፡፡ የሰው ሃይል አስተዳደር መመሪያ በማዘጋጀት እና በቦርድ የማጸደቅ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል የሰው ኃይል ቅጥር አልተጀመረም፡ ለአክስዮን ማህበሩ ለስራ የሚያፈልጉ ቢሮዎችን እና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ሁለት ተሽከርካሪ ለአክስዮን ማህበሩ የተሰጠ ሲሆን ተጨማሪ ሁለት በግዢ ሂደት ላይ ይኛል፡፡ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብድሩን ለመውሰድ ለአክስዮን ማህበሩ የንግድ ሥራ ዕቅድ መጠናቀቅ ስላለበት ያንን የማጠነቀቅ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለብድሩ የሚጠይቀውን ሰነዶች የማሟላት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

iv. **የትግራይ ብሄራዊ ክልል** አክስዮን ማህበሩ የንግድ ሥራ ፍቃድ ለማግኘት ወደ ብሔራዊ ባንክ መሟላት ያለባቸው ሰነዶች ተልከው እየታየ ይገኛል፡፡ ለአክስዮን ማህበሩ የሚያስፈልጉ ቢሮ፣ 1 ተሽከርካሪ የተመቻቸ ሲሆን ለሥራ የሚያስፈልጉ የቢሮ ቁሳቁሶች በመሟላት ላይ ናቸው፡፡ የሰው ሃይል ከማመሟላት አንጻር ሥራ አስኪያጅ እና 1 ረዳት ባለሙያ የተቀጠረ ሲሆን የሰው ኃይል ቅጥር መመሪያው በቦርድ ጸድቆ ወደ ቅጥር አልተገባም፡፡ ከብረታብረት ኮረፖሬሽን ጋር በጋራ መስራት ተጀምሯል፡፡

v. **የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል** አስፈላጊውን ፎርማሊቲ በማሟላት ከብሄራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኙ ሲሆን ከንግድ ሚኒስቴር የንግድ ፈቃድ ለመውሰድ በውልና ማስረጃ መሟላት ያለበትን ማስረጃ አቅርበዋል፣ በተጨማሪ ለአክሲዮን ማህበሩ አንድ መኪና ክልሉ መድቦለታል፣መዋቅር ተዘጋጅቶ ለቦርድ አባለት ተሰጥቷል፡፡ የፋይናንስ አቅርቦት ተጠናቋል፡፡ ከብረታብረት ኮረፖሬሽን ጋር በጋራ መስራት ተጀምሯል፡፡

## 2.2. የከተማ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች፡-

### 2.2.1. መልካም አስተዳደርን በተመለከተ

በከተሞች የሚስተዋሉትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት እንዲቻል የመልካም አስተዳደር ስትራቴጂ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የአጭርና የረጅም ጊዜ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በዋናነት ከመንግስት ቤቶች አስተዳደር ጋር በተያያዘ፣ በኮንስትራክሽን ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ እንዲሁም ከግዢ ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት አጣዳፊ እቅድ ታቅዶ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በኮንስትራክሽን ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ የሚስተዋለውን የአገልግሎት አሰጣጥ እና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች በመቅረፍ ረገድ ተጨባጭ ለውጦች እየመጡ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም

በግዥ አፈፃፀም የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ክፍተቶችን በመለየት በግዥ ሂደት ላይ የሚመለከታቸውን በተለይም (በዓለም አቀፍ ግዥ) ላይ የባለሞያውን ክፍተት ለመሙላት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጨረታ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ከፕሮጀክት ስራ አመራርና ከሃብት ስራ አመራር፣ከክልል እና ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ አመራሮችና ባለሞዎች ከዓለም ባንክና ከኢትዮጵያ ማኔጅመንት ኢንስቲዩት ጋር በመተባባር ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ሌላም የሚፈፀሙ ግዥዎች ላይ ግልጽነትን ለመፍጠርና በጊዜው ለሚመለከታቸው አካላት ለማድረስ ተገልጋዮችና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሞያዎች በቅርብ ሊከታተሉ በሚችሉበት በሚስቴር መ/ቤቱ ፖርታል ላይ የማውጣት፣ መረጃዎችና የግዥ ሂደቶች ያሉበትን ደረጃ ግልፅ የማድረግ ስራ፣ እንዲሁም ከዚህ በኋላ ለሚወጡ ጨረታዎችና ውጤቶች በቀጣይነት ለተጠቃሚዎች ግልፅ የሚሆንበት የአሰራር ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

## 2.2.2. የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ

በከተሞች ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራርን በመዘርጋት ውጤታማና ቀልጣፋ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን ለነዋሪዎቻቸው ማቅረብ እንዲችሉ በ4 አዳዲስ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች 20 የሙያ ስታንዳርዶች፣ 20 የመመዘኛ መስፈርቶች እና በ6 የማዘጋ ቤታዊ አገልግሎቶች የሙያ መስኮች ላይ 400 የብቃት አሃዶች የመማሪያ ማስተማሪያ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 25 የሙያ ስታንዳርዶች (125%) እና 300 (75%) የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች የተዘጋጁ ሲሆን ለመመዘኛ መስፈርቶቹ ዝግጅት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ሰነዱን የሚሰራ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡ በተጨማሪም በመስኩ 84 መሪ መዛኞች፣ 80 የትብብር ስልጠና ሰጪ መምህራን ለማፍራት እና 34 የብቃት ምዘና ጣቢያዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ 57 የምዘና ጣቢያ (167.65%) ሲዘጋጅ መሪ መዛኞች እና የትብብር ስልጠና ሰጪ የውጭ ሀገር መምህራን ቅጥር ለመካሄድ ዓለም አቀፍ የመምህራን ቅጥር ጨረታ ወጥቶ ይገኛል፡፡ ሆኖም ከGIZ ጋር በመተባበር በህዝብ ተሳትፎ ሙያ 7 (8%) መሪ መዛኞች እና በነዚህ መሪ መዛኞች በተሰጠ ስልጠና ደግሞ 7 (8.75%) የትብብር ስልጠና ሰጪ የኢንዱስትሪ አሰልጣኞችን ማፍራት ተችሏል፡፡ ከትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲና ከብቃት ምዘና ማዕከላት ጋር በመተባበር የአብይና የኦፕሬሽን ኮሚቴዎችን ማቋቋሚያ ሞዴል ማንዋል ተዘጋጅቶ ሞዴል ማንዋሉ ለ19 የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማት ፕሮጀክት (ULGDP) ከተሞች የተሰራላቸው ሲሆን የመካከለኛ እና የዝቅተኛ ሙያዎች የሰው ሀይል ለማብቃት ስራውን የሚመሩ በፌደራል አንድ፣ በክልሎች 11 ኮሚቴዎችን በማቋቋም በተፈጠረው የጋራ ስምምነት መሠረት የዘርፉን የሰው ኃይል ውጤታማ ለማድረግ በየሩብ ዓመቱ (3) መድረኮችን በማካሄድ አቅጫዎችና በአፈፃፀም ሂደት ላጋጠሙ ችግሮች ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማሳካት ዘርፉ የሚጠይቀውን በመጠን፣ በእውቀትና ክህሎት የተገነባ የሰው ኃይል ማፍራት ወሳኝ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የሥራ ላይ የትምህርትና ስልጠና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በተዘጋጁ የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂዎችና ማንዋሎች ላይ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎች ለ200 (50% ሴቶች) አመራሮችና ባለሙያዎች ለመስጠት ታቅዶ የስልጠና ፕሮፖዛል እና የትምህርትና ስልጠና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ለትላልቅ ስልጠናዎች ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ ትኩረት በመስጠቱና አጫጭር ስልጠናዎች ወደ 4ኛው ሩብ ዓመት እንዲሸጋገሩ በመደረጉ ምክንያት የዘገዩ ስልጠናዎቹን ለመስጠት ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ እንገኛለን፡፡ እንዲሁም ኮዲፋይድ በሆኑ 12 የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት የሙያ መስኮች በዘርፉ ውስጥ ተሰማርቶ ለሚገኙ 5,000 (50% ሴቶች) አመራሮችና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ከታቀደው አኳያ ለ8299 ተመዛኞች (5062 ሴቶች 61%) ስለ ምዘና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም ለ5000 አመራሮችና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ሥራ ግን ከውጪ መዛኞች ቅጥር መዘግየት ጋር ተያይዞ በአንድ ሙያ 7 ባለሙያዎች ብቻ የተመዘኑ ሲሆን የሴት ተመዛኝ ብዛት አንድ ነው፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ያለውን የሰው ኃይል ፍላጎት 12 የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የተለየ ሲሆን በዚሁ መነሻነት ከቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ከሌቭል አንድ እስከ አምስት ባሉ ደረጃዎች ለ10,000 (50% ሴቶች) ሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 421 (4.21%) ሰልጣኖች ሥልጠናውን እንዲከታተሉ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሲሆን የቻለው ወደ ሥራ የገቡት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የአማራ ክልል እንዲሁም የትግራይ ክልል ብቻ በመሆናቸው ነው፡፡ በተለያዩ የከተማ ልማት ሙያዎች 2,000 በድህረ ምረቃ እና 17 ሰልጣኞች ከማስተርስ በላይ ስልጠና ለመስጠት በታቀደው መሰረት 742(37.1%) የድሕረ ምረቃ ስልጠና እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 64ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዋና ዋና ስራዎች (pillars) ከመጀመሪያ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ ደረጃ የስልጠና ፕሮግራሞች በማዘጋጀት በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ስልጠና የሚሰጥበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የአዳዲስ ፕሮግራሞች ዝግጅት ፕሮፖዛል ለማከናወን ታቅዶ ተከናውኗል፡፡

በከተሞች የመኖሪያ ቤት አቅርቦት በማሻሻል የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማጎልበት፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን‌ና በከተሞች ቀጣይነት ያለው ፈጣን ልማትን ለማምጣት በሕዝብ ተሳትፎና በተጠናከረ ያልተማከለ አስተዳደር የታጀበ የልማት እንቅስቃሴን ማጎልበት ወሳኝ ነው፡፡ ይህን ያገናዘቡ የህብረተሰብ ልማት ፕሮጀክቶች፣ የሀብት አሰባሰብና አስተዳደር ስርዓት እና የምዘና ስነ-ምግባር ተጠያቂነት 2 ጋይድ ላይን ረቂቅ ሰነድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት ሰነዱ ተዘጋጅቷል፡፡ በከተሞች የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች ህብረተሰቡ በጉልበቱና እውቀቱ የሚያደርገው አስተዋፅኦ 30% ለማድረስ ከተያዘው

ዕቅድ አንፃር በግማሽ ዓመቱ ያደረገው አስተዋፅኦ 30% የደረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሴቶች ድርሻ 15% ነው፡፡

የማዘጋጃቤታዊ የአገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽንና ምዘናን በማጎልበትና ያልተማከለ አስተዳደርን በማጠናከር አገልግሎቶች በታችኛው የመንግስት አስተዳደር እርከን እንዲቀርቡ ለማስቻል 2 ማስፈጸሚያ ሠነዶችን ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረጊያ እና የከተሞች የበጀት ድጋፍ የአሰራር ስርዓት ሰነዶች የተዘጋጁ ሲሆን የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረጊያ ሰነድ በተመለከተ በሶማሌ ክልል በተመረጡ 2 ከተሞች እንዲሞከሩ የሚያግዝ ሞዴል የአፈፃፀም ሰነድ ተዘጋጅቶ የተላከላቸው ሲሆን በመስክ ድጋፍም እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ያልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን በማጠናከር በከተሞች የተጀመረውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች ቀጣይነት ለማረጋገጥ 30 በመቶ አገልግሎቶች ወደታችኛው የመንግስት የአስተዳደር እርከኖች በ25 ከተሞች እንዲወርድ ለማድረግ በታቀደው መሰረት ከተለዩ 8 ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ውስጥ 3 ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ማለትም የፅዳት፣ የውበትና የነዋሪዎች ኩነቶች አገልግሎቶች በሁሉም ክልል ዋና ከተሞች እና ሌሎች የክልል ከተሞች በአጠቃላይ በ32(128%) ከተሞች አገልግሎቶች እየተሰጡ ይገኛል፡፡

በ43 ከተሞች የቅሬታ እና አቤቱታ ማስተናገጃ ስርዓትን ለመዘርጋትና ለማጠናከር ታቅዶ ከመልካም አስተዳደር ግንባታ ጋር ተያይዞ የተዘረጉ ስርዓቶች አጠቃላይ እንቅስቃሴ በመገምገም በተለይ በዘርፉ የአገልግሎት መስጫ በሆኑት ተቋማት የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓቱ ያለበትን ደረጃ፣ ያከናወናቸውን ተግባራት፣ ያሉባቸውን ተግዳሮቶችና፣ የሚያስፈልጋቸውን የድጋፍ አይነት በ44 ከተሞች ለመለየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ በዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ የሚከሰቱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች አያያዝና አፈታትን ለማሻሻል የሚያግዝ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያሉበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ መመሪያ እና የዜጎች ቻርተርን መሠረት ያደረገ የአገልግሎት ስታንዳርዶች የተዘጋጁ ሲሆን ሰነዶቹን የማፀደቅ ሂደት ጊዜ በመውሰዱ ወደ ተግባር የማውረድ ሥራ በቀጣይ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ከተሞቻችን ዓለም አቀፍ ደረጃን ስታንዳርድ የጠበቁ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ 12 ስታንዳርዶች ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ6 ዋና ዋና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችና ለ35 ዝርዝር አገልግሎቶች 6 (5 ረቂቅና 1 የፀደቀ) የስታንዳርዶች ዝግጅት የተከናወነ ሲሆን በፀደቀው የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ስታንዳርድ እና በተዘጋጁ የምዘና መለኪያ መሥፈርቶችና ማስፈፀሚያ ማንዋሎች ላይ ለ26 አመራሮችና ባለሙያዎች (10.36%) የአሰልጣኞች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ሁሉንም ሰነዶች አጽድቆ በ12 ከተሞች ወደ ታችኛው የመንግስት መዋቅር በማውረድ ተግባራዊ

ማድረግ እና 2 ስኬታማ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለ27 ከተሞች ማስፋፋትን በተመለከተ ሰነዶቹ የቀሩት ሰነዶች እንደፀደቁ በቀጣይ የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

### 2.2.3. የሕዝብ ተሳትፎና ያልተማከለ አስተዳደር ማሻሻያና ማጠናከሪያን በተመለከተ

በከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና በከተሞች ቀጣይነት ያለው ፈጣን ልማትን ለማምጣት በሕዝብ ተሳትፎና በተጠናከረ ያልተማከል አስተዳደር የታጀበ የልማት እንቅስቃሴን ማጎልበት ወሳኝ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከ9ኙ ክልሎችና ከሁለት የከተማ አስተዳደር ለተውጣጡ 357 የከተማ ምክር ቤት አባላት፣ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ለህዝብ አደረጃጀት ተወካዮች በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ የከሞች ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረጊያ እና የከተሞች የበጀት ድጋፍ የአሰራር ስርዓት ማስፈጸሚያ 2 ሰነዶች ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን በከተሞች የቅሬታ አፈታት ስርዓት መዘርጋት የሚያስችል ሞዴል የአሰራር መመሪያ ረቂቅ ሰነድ እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የህዝባዊ ውይይት መድረክ የሚመራበት ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ ተከታታይነት ያለው የፕሮሞሽንና የቅስቀሳ ስራ በመስራት የከተሞች ሳምንት በዓል በህዝብ ንቅናቄ በማክበር የተወዳዳሪ ከተሞችን ቁጥር በ2005 ዓ.ም ካለበት 132 ወደ 150 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ በተደራጀ መንገድ ስራዎችን በማከናወን 186 ከተሞችንና 6 ድርጅቶች በድምሩ 192(145%) ከተሞችና ድርጅቶች ማሳተፍ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የከተማነት እውቅና ያልተሰጣቸው የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ህጋዊ የከተማነት እዉቅና እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ በደቡብ ክልል 68 እና በትግራይ ክልል 20 በድምሩ 88 ያህል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት ዕውቅና እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ያልተማከለ አስተዳደር ስርአት በከተሞች ለማጠናከር የሚያስችል 2 ተሞክሮዎች ለመቀመር የተያዘውን እቅድ በተመለከተ የደብረማርቆስ ከተማ ያልተማከለ የፋይናንስ ስርዓት ተቀምሮ በ5ኛው የከተሞች ሳምንት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በደቡብ ክልል ለከተሞች የመሰረት ልማት ማስፋፊያ የሚውል የበጀት ድጋፍ አሰራር ተሞክሮ ቅመራ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ሠነዱን የበለጠ ማዳበር በማስፈለጉ መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስፈልጉ የቅደመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቀዋል፡፡

ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን ከመደገፍና የማስፈጸምና የመፈጸም አቅማቸውን ከማጎልበት አኳያ የ2006 በጀት አመት የልዩ ድጋፍ ዕቅድ ከተዘጋጀና የጋራ መግባባት ላይ ከተደረሰበት በኂላ ለሚመለከታቸው አካላት የተላከ ሲሆን አፈጻጸሙ ላይም ድጋፋዊ ክትትል በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

http://www.mudco.gov.et/web/guest/home

## 2.3. የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን፣ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች፡-

### 2.3.1. የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅትና የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስራ፣

በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ፕላን ተቋማት የፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን በተሟላ መልኩ ለማከናወን የሚያስችላቸውን አቅም ለማጎልበት በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች በኩል 6 የህግ ማዕቀፍ፣12 ማንዋሎች፣ 7 ጥናቶችና 2 ስታንዳርዶች ለማዘጋጀት ታቅዶ 4 የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች፣ 12 ማኑዋሎችን፣ 7 ጥናቶችንና አንድ ስታንዳርድ የተዘጋጀ ሲሆን ከታቀደው በአማካይ 89 በመቶ ተከናውኗል፡፡ የከተማ ፕላን አፈፃፀም ጉድለት ጥናት ከአራት ክልሎችና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ሰነዱ ተዘጋጅቶ ከተለያዩ አካላት የተገኙትን ግብዓቶች በማካተት ሰነዱ ተዘጋጅቷል፡፡ በተመሳሳይ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ሥራዎች ተገቢውን የጥራት ቁጥጥር እንዲደረግባቸው የሚያስችል የከተማ ፕላን ዝግጅት እና አፈፃፀም ጥራት ቁጥጥር ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

የሃገር አቀፍ የልማት ቀጠና እና የልማት ማዕከላትን ታሳቢ ያደረገ የከተማ ልማት ስኪም (National Urban development scheme)፣ ሀገራዊ የመሬት አጠቃቀም ፕላን፣ በሀገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ የከተሞች ስርዓት (System) እንደዚሁም የአዲስ አበባ ከተማን ተወዳዳሪ ሆኖ ማስቀጠል የሚያስችል ጥናት በአለም አቀፍ አማካሪዎች እየተዘጋጀ ሲሆን በዝክረ ተግባሩ እና በኮንትራት ስምምነቱ መሰረት ኢንሴፕሽን ሪፖርት (Inception Report) ቀርቦ መረጃዎችም ተሰባሰበው እየተደራጁና እየተጠናቀሩ ሲሆን የአፈጻጸም ደረጃው ከታቀደው አንጻር 68 በመቶ ነው፡፡በሀገሪቱ የተመረጡ 12 ከተሞች የሚካሄደው የአካባቢ ልማት ፕላን ዝግጅትም የዚሁ ጥናት አካል ነው፡፡

በ36 የከተማ ፕላን ዝግጅት ተቋማት የፕላን ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት በተዘጋጁ 90 ፕላኖች ላይ የጥራት ቁጥጥር በማድረግ ግብረ-መልስ ለመስጠት ታቅዶ በ9ኙ ተቋማት የፕላን ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በ30 የተዘጋጁ ፕላኖች ላይም የጥራት ቁጥጥር ተካሂዷል፡፡ የፕላን ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋቱ የተዘጋጁ ፕላኖች በመስፈርቱ መሰረት እንዲዘጋጁ አስችሏል፡፡ የከተማ ፕላን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በከተማ ፕላን ጥሰት ላይ ያተኮረ ሲሆን በዚህም መሠረት በሁሉም ክልሎችና በበሁለት ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ 90 ከተሞች ላይ የክትትልና ግምገማ ስራ ተከናውኖ በክትትል የታዩ የፕላን አፈጻጸም ጥሰቶች የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶች እና ግብረ-መልስ ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡

በ61 የፕላን ተቋማት የፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም እንዲሁም የካርታና የቅየሳ አሃዶች እንደየ ከተሞቹ የእድገት ደረጃ ተቋማዊ የአደረጃጀት ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው በማድረግ ክትትልና ግምገማ ለማካሄድ በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ በተያያዘም ከፌዴራል እስከ ከተሞች በሚገኙ የከተማ ፕላን ዝግጅት የአፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስን በሚያከናውኑ 109 ተቋማት ወጥ የሆነ የከተማ ፕላን መረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና ልውውጥ ሥርዓት ለማጠናከር ታቅዶ በ9 ተቋማት ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

የ63 ከተሞች መሠረታዊ መረጃዎችን (Urban Profile) በማሰባሰብና በማደራጀት በድረ-ገጽ (በኢ.ኮ.ቴ) ለተጠቃሚዎች ዝግጁ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ የ80 (126.9%) ከተሞችን መሠረታዊ መረጃ ተደራጅቶ በድረ-ገጽ እንዲለቀቁ ማድረግ ተችሏል፡፡

መሠረታዊ ካርታ እና መሠረታዊ የከተማ ፕላን ለሚዘጋጅላቸው 200 አነስተኛ ከተሞች አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ በታቀደው መሰረት ለ130 ከተሞች መሠረታዊ ካርታ እንዲሁም ለ70 ከተሞች መሠረታዊ ፕላን ዝግጅት ላይ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ የጽሁፍ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡ በተመሳሳይ በ24 ከተሞች በሚዘጋጁ የመዋቅራዊ ፕላኖች እንዲሁም በከተሞች በሚዘጋጁ 80 የአካባቢ ልማት ፕላኖች ዝግጅት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 5 መዋቅራዊ ፕላኖች እና 52 የአካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ የጽሁፍ ግብረ-መልስ ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም በስኳር ልማት ፕሮጀክቶች፣ በዩኒቨርሲቲዎች እና በማዳበሪያ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በሚሆኑባቸው ከተሞች በሚዘጋጁ 4 የመዋቅራዊና 4 የአካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ በየሩብ ዓመቱ ክትትል ለማድረግ የታቀደ ሲሆን በዚሁ መሰረትም ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ 2 የመዋቅራዊ ፕላንና 2 የአካባቢዊ ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡

ባለሩት ዘጠኝ ወራት በ193 ከተሞች የከተማ አመራሮች ኘላኖችን በአግባቡ ተገንዝበው እቅድ እንዲያዘጋጁ ለማስቻል ከየከተሞቹ ለተውጣጡ 522 አስፈጻሚዎች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ በ482 ከተሞች ለ996 ከተማ አመራሮች ሥልጠናው የተሰጠ ሲሆን ለ3,179 ከተማ ከንቲባዎች፣ ሥራ አስኪያጆችና ባለሙያዎች ስለ ከተማ ኘላን አዘገጃጀትና አተገባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ2,623 ከንቲባዎች፣ ሥራ አስኪያጆችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በመንግስት ተቋማት በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ለተሰማሩ ለ458 ባለሙያዎች በሶሺዮ ኢኮኖሚ፣ በፊዚካል፣ በስፓሻል እና በጂ.አይ.ኤስ ሙያ ዘርፍ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ499ኙ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በከተማ ፕላን ስትራቴጅዎች ዙሪያ በአካልና በፕላዝማ አማካይነት ለ12,200 መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ተሳታፊዎች /ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻና አረንጓዴ ልማት ጋር የተያያዙ ስትራቴጅዎች/ ላይ አገር አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለማከናወን የታቀደ ቢሆንም ይህንን ሥራ ከህዝብ ንቅናቄ ሥራ ጋር በማቀናጀት እንዲተገበር ስምምነት ላይ ስለተደረሰ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ለማከናወን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፓይለት ደረጃ የመሬት ላይ የቅየሳ ዘዴን በመጠቀም ከከተማው ለተውጣጡ 75 የቅየሳ ባለሙያዎች በ25 ቡድኖች/አሃዶች በአማካሪነት እንዲደራጁ ድጋፍ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኩል አሃዶችን ለማደራጀት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ባለማከናወኑ ሊተገበር አልቻለም፡፡

## 2.3.2. የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች፣

መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ሥራዎችን በተመለከተ ለ250 ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ ወሰን እንዲኖራቸዉ እና 7000 ሄክታር መሬት ተቆጥሮ እንዲመዘገብ በማድረግ በጊዜያዊነት ለማዕድን ማውጫ፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ፣ ለከተማ ግብርና እና የእርሻና የግጦሽ መሬቶች እየተጠቀሙ ለሚገኙ 1500 ተጠቃሚዎች ጊዚያዊ የመጠቀሚያ ሰነድ አዘጋጅቶ ከመስጠት ረገድ በ9 ወራት ውስጥ በአማራ 45 ከተሞች፤ በደቡብ ክልል 45 ከተሞች በትግራይ 46 ከተሞችና በኦሮሚያ 79 በድምሩ 215 (86%) ከተሞች ወሰናቸውን እንዲከልሉና የመሬት ሃብታቸውን በሚገባ ማስተደደርና መጠበቅ እንዲችሉ አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ ሥርዓት መሠረት በሁሉም የክልል ከተሞች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ለተለያዩ አገልግሎቶች 7,000 ሄክታር መሬት ተቆጥሮ እንዲመዘገብ ለማድረግ ታቅዶ በደቡብ ክልል በ11 ከተሞች 920.83 ሄክታር፤ በትግራይ ክልል በ13 ከተሞች 1,471.23 ሄክታር በአማራ ክልል በ 21 ከተሞች 1,874.16 ሄክታር፤ በኦሮሚያ ክልል በ31 ከተሞች 2,420.78 ሄክታር በድምሩ 6,687 ሄ/ር መሬት ተቆጥሮ የተመዘገበ ሲሆን አፈጻጸሙ 95.5 በመቶ ነው፡፡

በከተሞች የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በጊዜያዊነት ለማዕድን ማውጫ፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ፣ ለከተማ ግብርና እና የእርሻና የግጦሽ መሬቶች እየተጠቀሙ ለሚገኙ 1,500 ተጠቃሚዎች ጊዚያዊ የመጠቀሚያ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ በትግራይ ክልል በሚገኙ ከተሞች ለ478፣ በአማራ ለ300 እንዲሁም በደቡብ ለ522 በአጠቃላይ 1,300 (86.7) ጊዚያዊ የመጠቀሚያ ሰነድ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በተለያዩ የከተማ አካባቢዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 3,500 ሄክታር መሬት መሰረተ ልማት ተሟልቶለት እንዲዘጋጅ ከማድረግ ረገድ በአማራ 1200 ሄ/ር በኦሮሚያ 3,170.89 ሄ/ር፤ በደቡብ

3,174.73 ሄ/ር በትግራይ 379.60 ሄ/ር እንዲሁም በአዲስ አበባ 1,300.94 ሄ/ር በድምሩ 9,226.16 ሄ/ር መሬት መሰረተ ልማት ተሟልቶለት ተዘጋጅቷል፡፡

የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ በዘጠኙ ክልሎችና በተመረጡ ከተሞች የደቀቁና የተጎሳቆሉ የከተማ አካባቢዎችን ሽፋን በአማካሪ ለማስጠናት በተያዘው ዕቅድ መሰረት የአማካሪ ግዢ ለመፈጸም በወጣው ጨረታ አራት ተጫራጮች ፍላጎታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎበት ለፋይናንስ የተላለፈ ሲሆን በቀጣይ የአማካሪ ግዢው ተፈጽሞ ወደ ስራ የሚገባ ይሆናል፡፡

የደቀቁና የተጎሳቆሉ የከተማ አካባቢዎችን ገጽታ ለመቀየር በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በተጀመሩ 5 የመልሶ የማልማት ፕሮጀክቶች 231 ሄክታር መሬት በተቀናጀ የመልሶ ማልማት ሥራ እንዲለማ ለማድረግ ታቅዶ 6 የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች የተዘጋጁ ሲሆን በዘጠኝ ወራት ውስጥ በአዲስ አበባ 4 ክፍለ ከተሞች (ልደታ፣ አራዳ፣ ቂርቆስ እና አዲስ ከተማ) 64.03 ሄ/ር መሬት በአማራ ክልል ጎንደርና ደሴ ሁለት ፕሮጀክቶች 36 ሄክታር በድምሩ በ6 የመልሶ ማልማት ፕሮጀክች 100.03(43.3%) ሄ/ር እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመልሶ ማልማት ኦፐሬሽናል ማኑዋልን የሌሎች ሀገሮችን ልምድና ተሞክሮ ባማከለ መልኩ ቀደም ሲል የተዘጋጀውን አሻሽሎ የማዘጋጀት ስራ የተሰራ ሲሆን በቀጣይም በማኑዋሉ ላይ ለባለሙያዎችና አመራሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች የሚሰጥ ይሆናል፡፡

በዘጠኝ ወራት ውስጥ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች 6 የኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲለሙ ለማድረግ ታቅዶ 5 (በአማራ ክልል ገንደውኃ፣ ወልዲያ እና ኮምቦልቻ ከተሞች እና በኦሮሚያ ክልል ጅማና አምቦ ከተሞች) የኢንዱስትሪ ዞኖች ተከልለው እንዲለሙ ተደርጓል፡፡

በክልል ከተሞችና በከተማ አስተዳደሮች በካሳ ግመታ እና በምትክ አሰጣጥ ስርዓትና ትግበራ ላይ የሚታይ ክፍተት እንዲጠና እና ጥናቱ በወርክሾፕ እንዲዳብር ለማድረግ በአዲስ አበባ በአምስት ክፍለ ከተሞች (ቦሌ፣ የካ፣ አራዳ፣ ኮልፌ እና ቂርቆስ)፣ በደቡብ ክልል ወላይታ ሶዶ እና ሀዋሳ በኦሮሚያ ክልል ሻሸመኔ ከተሞች ላይ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን ከተለያዩ ከተሞች 164 ተሳታፊዎች በተገኙበት በሰነዱ ላይ ውይይት ተደርጎበት ሰነዱን የማዳበር ስራ የተሰራ ሲሆን በቀጣይ ተጨማሪ መረጃ ከሌሎች ከተሞች በማሰባሰብ በካሳ ግመታ እና በምትክ አሰጣጥ ስርዓትና ትግበራ ላይ የሚታየውን ክፍተት የሚያሳይ መረጃ የማዘጋጀት ስራ ይሰራል፡፡

ከ20 ሺህ ሕዝብ በላይ ባላቸው ከተሞች ዘመናዊ የከተማ ማዕከል ግንባታን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ጥናት ለማስጠናት የአማካሪ ቅጥር በመፈጸም ስራው እንዲጀመር የተደረገ ሲሆን በቀጣዩ ወር የጥናት ስራው ሙሉ በሙሉ ይጀመራል፡፡

በከተሞች ያለፈቃድ የተያዙ ይዞታዎችን ስርዓት ከማስያዝ አኳያ በከተሞች ያሉ ሰነድ አልባ እና ህገ-ወጥ ይዞታዎች 50% ሥርዓት እንዲይዙ ለማድረግ ታቅዶ በአማራ ክልል 11,520፣ በአዲስ አበባ 1,053፣ በደቡብ 18,742፣ ቤኒሻንጉል 416፣ እንዲሁም በትግራይ 3183 በድምሩ 34,914 ይዞታዎች ሰነድ የተሰጠ ሲሆን በተመሳሳይ በአምስት ከተሞች አማራ 2,803፣ ደቡብ 1,824፣ ቤኒሻንጉል 496፣ በትግራይ 562፣ ኦሮሚያ 6,416 እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳድር 1,000 በድምሩ 13,101 ህገ-ወጥ ይዞታዎች ሥርዓት እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ20 ከተሞች ነባር የይዞታ ማህደሮች እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ትግራይ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር በድምሩ በ67 ከተሞች እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ የመሬት መረጃ አያያዝ ስርዓቱን ከማዘመን አንጻር ለአራት ከተሞች ሾኔ፣ በቆጂ፣ እንደባጉና እና አሶሳ ሶስት ሶስት ዘመናዊ የይዞታ ማህደር ካቢኔቶች እንዲተከል የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ ላይም የቅርብ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

ሊዝ ተግባራዊ ያልተደረገባቸው 100 ከተሞች ወደ ሊዝ ስሪት እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ በኦሮሚያ 214፤ በደቡብ 88፤ በትግራይ 30 በአማራ 68 በቤኒሻንጉል 7 ሱማሌ 3 እንዲሁም በጋምቤላ 2 ከተሞች በድምሩ 412 ከተሞችን ወደሊዝ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ 26 ከተሞች የሊዝ መነሻ ዋጋ እንዲከልሱ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በአዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ፤ በአማራ፤ በኦሮሚያ፤ በደቡብ እና በትግራይ ክልሎች በሚገኙ 67 ከተሞች የመሬት ኪራይ፣ የቤት ግብር ተመን እና የሊዝ መነሻ ዋጋ ዝግጅትና ክለሳ ያደረጉ ሲሆን ሁሉም ወደ ሊዝ የገቡ 412 ከተሞች የሊዝ መነሻ ዋጋ አዘጋጅተዋል፡፡ ምንም እንኳን የመሬት ኪራይና የቤት ግብር ተመን ፕሮጀክት ፅ/ቤት የመሬት ኪራይና የቤት ግብር ተመን ክለሳ የሚሰራ ቢሆንም በተደረገው ክትትልና ድጋፍ 242 ከተሞች የመሬት ኪራይና የቤት ግብር ተመን ክለሳ ማከናወናቸው ተረጋግጧል፡፡

የመሬት አቅርቦት፣ ግብይትና አስተዳደር ሥራዎች በተመለከተ ለቤቶች ልማት ፕሮግራም፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች እና ለተለያዩ አገልግሎቶች (ለንግድ፣ ለመኖሪያ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለማህበራዊ ወዘተ) የሚዉሉ መሬት በሊዝ ምደባና ጨረታ በሊዝ አዋጅ መሰረት እንዲተላለፍ ከማድረግ ረገድ 2,500 ሄክታር መሬት በጨረታና በምደባ ለማስተላለፍ ታቅዶ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በጨረታ 2,371.57 ሄ/ር እና በምደባ 2,290.3 ሄ/ር በድምሩ 4,661.87 ሄር መሬት ለተጠቃሚዎች መተላለፉ ተረጋግጦ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡

የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ፕሮግራምን ለማስፈጸም የሚያስችሉ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ለ317,023 አመራሮች እና ፈጻሚዎች (30% ሴቶች) ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በ3 መድረኮች በድምሩ ለ249 አመራሮች እና ባለሙያዎች ስልጠናውን ያገኙ ቢሆንም ከተያዘው ዕቅድ አንጻር አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

http://www.mudco.gov.et/web/guest/home

### 2.3.3. የከተማ መሬት የጂኦስፓሻል እና የይዞታ መረጃ ማደራጀትና ሥርዓት ዝርጋታ ሥራ፣

የመሬትና መሬት ነክ ምዝገባን ለማጎልበት የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመዘርጋት እንዲሁም የአየር በረራ የተደረገባቸው ከተሞችና በሳተላይት ስትሪዮ ምስል 44 የከተሞች መሰረታዊ ካርታ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለከተሞች የአድራሻ ሥርዓት ትግበራ መሰረት የሚጥል አንድ ስታንዳርድ እና ማኑዋል ለማዘጋጀት የተያዘውን ዕቅድ በተመለከተ በዘጠኝ ወራት ውስጥ የአድራሻ ሥርዓት ስታንዳርድ ማፀደቅና የትግበራ ማኑዋሉን የማዘጋጀት ስራ የተጠናቀቀ ሲሆን በቀጣይ ለሚመለከታቸው አካላት ይሰራጫል፡፡ ለ22 ከተሞች የመሠረዊ ካርታ ዝግጅት የሚያስፈልጉ መረጃዎች በማደራጀትና ለኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ በማስረከብ የካርታ ዝግጅት ስራው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲከናወን የክትትልና ድጋፍ ሥራም ተከናውኗል፡፡

በተጨማሪም በ16 ከተሞች ተጀምሮ የነበረውን 1,385 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች እንዲዘረጉ ከማድረግ አኳያ በ11(68.75%) ከተሞች 1,158 (83.6%) የቅየሳ ነጥቦችን የመለየት፣ የልኬት መነሻ የቅየሳ ነጥቦችን በኮንክሪት የማዘጋጀትና የመትከል ሥራ እንዲሁም የ40 ከተሞች በሳተላይት ስቴሪዮ ምስል መሰረታዊ ካርታ ዝግጅት ስራን ለማጠናቀቅ የመሬት ምስል መቆጣጠሪያ ነጥቦች ተከላ ስራ በ29(72.5%) ከተሞች ተሰርቷል፡፡ የተቀናጀ የከተማ መሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ የመረጃ ሥርአት ለመዘርጋት እንዲቻል የቅየሳ መረጃ አያያዝ ስርዓት እና መረጃ ቋት ዝግጅትን በ42 ከተሞች ለማከናወን ታቅዶ በኦሮሚያ ክልል በ15 ከተሞች፣ በትግራይ ክልል ለ6 ከተሞች እና በደቡብ ክልል ለ10 ከተሞች በድምሩ ለ31 (75.6%) ከተሞች የመረጃ ቋት የተዘጋጀ ሲሆን የመሬት እና መሬት ነክ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ለማድረስ የሚያስችል አንድ አገራዊ ዌብ ፖርታል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲዘጋጅ የድጋፍና ክትትል ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

በመሬት መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና ዕድሳት ዙሪያ ከኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ እና ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር አንድ የምርጥ ተሞክሮ (Lesson Learnt) ሰነድ ለማዘጋጀት የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሰነዱ እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡

ከሠው ኃይል ልማት አኳያ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ኘሮግራምን ለማስፈፀም የሚችሉ 1,450 ሠልጣኖችን በአጭር ጊዜና 1,225 ሠልጣኞችን በመካከለኛ ጊዜ ለማሰልጠን በተያዘው ዕቅድ መሰረት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ለ986 (68%) የመሬት ዘርፍ ባለሙያዎች በሰርቨይንግ፣ በጂአይኤስ፣ በዌብ ማፕንግ እና ዳታ እንኮዲንግ ላይ የአጭር ጊዜ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በየክልሉ በሚገኙ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት አማካይነት ለ685 (55%) ሰልጣኞች በ Urban Land Management፣ Cadasteral Surveying፣ Urban Planning የሙያ ደረጃዎች የመካከለኛ ጊዜ ስልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ለመሬት ዘርፍ ከተዘጋጁት የሙያ ደረጃዎች አንጻር የመሪ መዛኝነትና የትብብር ስልጠና አሰልጣኝነት

ሥልጠናና ምዘና በመንግስትና በግሉ ሴክተር ለሚገኙ 2000 ባለሙያዎች ለመስጠት ዓለም አቀፍ ጨረታ በማዉጣት እና የቴክኒክ ግምገማ በማድረግ መስፈርቱን ያሟሉ 242 አሰልጣኝና መዛኝ ተቋማትን የመለየት፣ የምዘናውንና የስልጠናውን የጊዜ ሰሌዳ የማዘጋጀት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቀዋል፡፡ ይህም ከዕቅዱ አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀሪዎቹ ወራት የተሻለ ለመፈጸም ርብርብ ማድረግ ይጠበቃብናል፡፡

የረጅም ጊዜ ስልጠና ለመስጠት እየተደረገ ያለውን ዝግጅት በተመለከተ በመሬት ዘርፍ ላይ በ6 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለያየ የትምህርት ደረጃ (BSc, MSc) ሥርዓተ ትምህርት ቀርጸው የመማርና የማስተማር ሥራ ለማስጀመር እና በመሬት ዘርፍ ጎልቶ የሚታየውን የአሰራርና የማኔጅመንት ችግር በጥናትና ምርምር በተደገፈ አግባብ ለመፍታት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በተደረገው ስምምነት መሰረት የካሪኩለም ዝግጅት እና የልህቀት ማዕከል የማቋቋም ሂደት ላይ ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን 12 የተለያዩ የመሬት ዘርፍ ፕሮግራሞች ተለይተው የካሪኩለም ዝግጅት ስራው ከጀርመን አገር የተገኘውን ተሞክሮ በማካተት በመናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

## 2.3.4. የከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ሥራ፣

የመሬትና መሬት-ነክ ምዝገባን ለማጎልበት የህግ ማዕቀፍ ዝግጅትን በተመለከተ የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት ውይይት ከተካሄደበት በኋላ የፌደሬሽን ምክር ቤት ይሁንታን አግኝቶ የጸደቀ ሲሆን በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ለክልል የመሬት ተቋማት እና ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ ይህን የህግ ማዕቀፍ ተከትሎ በማስፈጸምያ መሳሪያነት ከሚጠበቁት መካከል የደንብ ዝግጅቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በመሆኑም በአገር አቀፍ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባን ማስፈጸም የሚያስችሉ ሁለት ደንቦች (የከተማ መሬት ይዞታን ማረጋገጥ እና ምዝገባ ረቂቅ ደንብ እና የከተማ ካዳስተር ቅየሳ ደንብ) ዝግጅት በተመለከተ ግብዓት ተሰባስቦ የማጠቃለያ ሥራ የተሰራ ሲሆን በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ እንደሚጸድቅ ይጠበቃል፡፡

የስታንዳርድ ዝግጅትን በተመለከተ የአይ.ኤስ.ኦ.19152 የመሬት አስተዳደር ሞዴል እና በመረጃ ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተዘጋጀው የጂ.አይ.ኤስ ስታንዳርድ በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃ ኤጀንሲ በኩል እንዲፀድቅ ግፊት በማድረግ ላይ የሚገኝ ቢሆንም እንድንጠቀምበት ከኤጀንሲው ፈቃድ ተገኝቶበት በሚኒስቴር መ/ቤታችን ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ረቂቅ ስታንዳርድ የተዘጋጀ ሲሆን የከተማ ካዳስተር ካርታ ቅጠል ስፋት ስታንዳርድ እና አገራዊ ስያሜ ስርዓት ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል፡፡ ማኑዋል ዝግጅትን በተመለከተ ሃገራዊ የከተማ መሬትና መሬት ነክ ተቋማት የሥራ ጥራት ኦዲት አሰራር ማንዋል ተዘጋጅቶ ተጠናቋል፡፡

በእስከአሁኑ አፈጻጸማችን ህጋዊ ካዳስተር ሥርዓቱ በዋናነት በአገር ደረጃ መናበብ የሚያስችለውን ቴክኖሎጂ የሚገነባበትን ደረጃ የሚያስጠብቅ ከአዋጅ እስከ መመሪያ ድረስ የሚናበብ እና የሚመጋገብ የህግ ማዕቀፍ ኖሮት ወደ ቀጣይ ሥራዎች መግባት የሚያስችል መሰረት የመጣል ተልዕኮን አሳክተናል፡፡

የዘርፉን የሰው ኃይል አቅም ከማጎልበት አንጻር በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለማከናወን በዕቅድ ከተያዙ ስራዎች አንዱ የከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ለማስፈጸም የሚያስችሉ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት 99,612 (30% ሴቶች) ተሳታፊዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት 13,880(14%) ተሳታፊዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ 150 የተደራጀ ነባር የመሬት ይዞታ መረጃ ከወረቀት ወደ አሃዛዊ መረጃ እንዲለወጥ ከማድረግ ረገድ ደረጃውን የጠበቀ 150 የፓርሴል ኢንዴክስ ካርታ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በተያየዘም 111,675 ነባር ይዞታዎችን ወደ አሃዝ ለመቀየር ታቅዶ 48,000(42.98%) የተደራጀ ነባር የመሬት ይዞታ መረጃ ከወረቀት ወደ አሃዛዊ መረጃ እንዲለወጡ የማድረግ ስራም ተሰርቷል፡፡ እነዚህ ሥራዎች ባለፉት ስድስት ወራት ያልተከናወኑ የነበረ ሲሆን በሶተኛው ሩብ ዓመት በተደረገው ርብርብ አበረታች ውጤት በመታየቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በዘጠኝ ወራት ውስጥ በዕቅድ ተይዘው ያልተከናወኑ ስራዎች በተመለከተ ከተሞች መሬት ይዞታ በማረጋገጥ /Adjudication/ ለምዝገባ ዝግጁ ማድረግ፣ እንዲሁም ከተረጋገጡ ይዞታዎች ውስጥ 37,500 ይዞታዎች መመዝገብና የባለይዞታነት ማረጋገጫ በመስጠት ጥራቱን የጠበቀ መረጃ እንዲኖር ማድረግ የሚሉት ስራዎች በዕቅድ ተይዘው ያልተከናወኑ ቢሆንም በቀጣይ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚተገበሩ ናቸው፡፡

## 2.4. የተቀናጀ የመኖሪያ ቤቶች ልማት ሥራዎች፡-

### 2.4.1. የቤት ልማት ስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅት ሥራ፣

የቤት ልማት አማራጮች ተግባራዊ ለማድረግ እና የቤት ልማት ዘርፍና አስተዳደር ህግና ሥርዓት የተከተለ እንዲሆን ለማስቻል የሚረዱ የህግ ማዕቀፎች ዝግጅትን በተመለከተ 2 አዋጆች፣ 2 መመሪያዎች፣ 2 የስትራቴጂክ ሰነዶችን እና 2 ደንቦችን ለማዘጋጀት ታቅዶ የመኖሪያ ቤቶች ልማትና ግብይት አዋጅ በረቂቅ ደረጃ የተጠናቀቀ ሲሆን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵውያን የቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ማስፈጸሚያ ረቂቅ ሞዴል መመሪያም ተጠናቆ እንዲጠቀሙበት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተልኳል፡፡ በተጨማሪም በመንግሥትና በግል ዘርፍ የቤት ልማትን በአጋርነት ለማከናወን የሚያስችል የስትራቴጂ ሰነድ እና በመንግስትና በግል ባለሃብት የቤት ልማት ለማካሄድ የሚያስችል ደንብ

የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ የተዘጋጁ ሲሆን በሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ አመራር ደረጃ ውይይት ተደርጎባቸው የሚፀድቁ ይሆናል፡፡

### 2.4.2. የቤቶች እና የህንጻ ግንባታ አቅም ግንባታ ሥራ

የቤቶች እና የህንጻ ግንባታ አቅም ግንባታ ሥራዎችን አፈጻጸምን በተመለከተ የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጐልበትን አስመልክቶ በቤት ልማት፣ በስኳር ልማት፣ በ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች፣ በማዳበሪያ ፋብሪካ ቤቶች ግንባታ ባለቤቶች፣ በፌዴራል የመንግሥት ህንጻዎች ለሚሣተፉ 69 አስፈጻሚ ባለቤቶች፣ 855 ሥራ ተቋራጮች፣ 47 አማካሪዎች የክህሎት ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ115 (240%) አስፈጻሚ ባለቤቶች፣ ለ880 (103%) ሥራ ተቋራጮች እና ለ123 (262%) አማካሪዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን 1,118 ሴቶች የክህሎት ሥልጠና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 121(10.82%) ለማሰልጠን ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በግንባታ ፕሮጀክቶች አሰራር ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣትና ወጥነት ባለው መልኩ አዋጪ አሰራሮችን ለመዘርጋት የካይዘን አሰራርን ለመተግበር ሚ/ር መ/ቤታችን ከኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ለ 396 ተሳታፊዎች ለማሰልጠን ታቅዶ በአምስት ዙር 480 የፕሮጀክት ባለቤቶችና ባለድርሻ አካላት፣ ከፍተኛና መካከለኛ ኃላፊዎችና ፈጻሚዎች እንዲሰለጥኑ የተደረገ ሲሆን በዚህ ስልጠና የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አንቀሳቃሾች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ስልጠናውን መሰረት በማድረግም የልማት ቡድኖች ተደራጅተው በፓይለት ደረጃ ወደ ትግበራ ከተገባ በኋላ በተለይ በግንባታ አፈጻጸም የግብዓት ብክነትን መቀነስ የተቻለ ሲሆን በጥራት ረገድ ከፍተኛ ለውጥና መሻሻሎች ተመዝግበዋል፡፡ ይህን ስርዓት በቴክኖሎጂ ለመደገፍ፣ በመረጃ ቅብብሎሽ ለማጠናከር፣ ለመመዝገብና ለመመዘን እንዲቻል ዘመናዊ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስርዓት ለመዘርጋትና ስርዓቱን በገመድ አልባ ኔት ወርክ ለማስተሳሰር እየተሰራ ይገኛል፡፡

### 2.4.3. የቤቶች እና የህንጻ ግንባታ ግብዓት ጥናትና አቅርቦት ሥራ

በመንግስት ለሚከናወኑ የቤቶችና የህንጻዎች ግንባታ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የግብዓት አይነቶች 6 ጥናቶች እንዲጠኑ እና እንዲቀርቡ ለማድረግ ታቅዶ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚያስፈልጉ የሲሚንቶ፣ የአግሮስቶን፣ የአርማታ ብረት፣ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ፣ የአሸዋና ጠጠር እንዲሁም ትራንስፎርመሮች፣ ቆጣሪዎች የኤሌክትሪክና የሳኒተሪ ዕቃዎች ግብዓት ፍላጎትና አቅርቦት የሚመለከቱ 6 ጥናቶች ለማዘጋጀት የተሟላ መረጃ ለማሰባሰብ የሚደረገው ጥረት በመቀጠሉ ስራው አሁንም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ያለውን የሲሚንቶ አቅርቦት መሠረት ያደረገ ሲሚንቶ በስፋት መጠቀም የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችና ምርቶች በመለየት ሲሚንቶ በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋል የተጀመረው

አንድ ጥናት ባለመጠናቀቁ ቀጣይ ስራው በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ፕሮጀክቶች የግንባታ ግብዓቶች ፍላጎት፣ አቅርቦት ሥርጭትና ንብረት አስተዳደር ጥናት በማካሄድ የሎጂስቲክስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ለማድረግ የሚያስችል አንድ ጥናት በአማካሪ ለማሰራት በታቀደው መሰረት አማካሪ ድርጅቱ ዝርዝር የጥናት ሠነድ አቅርቦ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

የኮንስትራክሽን ግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ በመኖሪያ ቤት ልማት፣ በስኳር ልማት ቤቶች ግንባታ፣ በ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች፣ በማዳበሪያ ፋብሪካ ቤቶች ግንባታ፣ በፌዴራልና በክልል ለሚካሄዱ የመንግሥት ህንጻዎች የሚያስፈልጉ የግንባታ ግብአቶች አቅርቦት ጋር በተያያዘ 392,247 ቶን ሲሚንቶ ታቅዶ 291,923 ቶን (74%) ቀርቧል፡፡ 80,480 ቶን የአርማታ ብረት ለማቅረብ ታቅዶ 40,755 ቶን(51%) የቀረበ ሲሆን ለ55,499 ቤቶች የሚሆን ሳኒተሪና ኤሌክትሪካል ዕቃዎች ለማቅረብ ታቅዶ ለ39,538 ቤቶች (71%) ለማቅረብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ 421,137 አግሮስቶን ፓኔል ለማቅረብ ታቅዶ 411,442 (98%) ማቅረብ የተቻለ ሲሆን 55,499 ትራንስፎርመርና ቆጣሪ ለማቅረብ ታቅዶ 23,651(43%) ለማቅረብ ተችሏል፡፡

ለግንባታ ኘሮጀክቶች አግሮስቶን ምርት ፍላጐት እንዲሟላ ከማድረግ አንጻር 8 ማዕከላት በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ለማድረግ ታቅዶ 6ቱ በሙሉ አቅማቸው በማምረት ላይ ሲሆኑ የደሴና ወልቃይት የሙከራ ምርት በማምረት ላይ ይገኛሉ፡፡ የማግኒዥየም ኦክሳይድ ፋብሪካ 14,999 ቶን ምርት እንዲያመርት ክትትል እና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 9,563(64%) እንዲያመርት ለማድረግ ተችሏል፡፡

በቤቶች ልማት፣ በስኳር ልማት ቤቶች ፣በ10 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ፣ በማዳበሪያ ፋብሪካ ቤቶች፣ በፌዴራልና በክልል የሚከራዩ እና በመንግስት ህንጻዎች ግንባታ የተጠናከረ የሥራ ትስስር በማድረግ ለ103,824 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በጥቅሉ 153,524 ዜጎች የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈጻጸሙም 148 ከመቶ ነው፡፡

### 2.4.4. የቤቶችና የመንግሥት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሕንጻ ዲዛይን ዝግጅትና ትግበራ ሥራዎች፡-

ቀደም ሲል ተሰርተው በሥራ ላይ የዋሉ ዲዛይኖች ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ምርትና የገበያ አገልግሎቶች የሚውሉ 2 (G+3 እና G+4)፣ የተለያየ ገቢ ላላቸው የገጠር ነዋሪዎች 3 የተለያዩ የገጠር ቤት ስታንዳርድ ዲዛይኖች፣ ለ40/60 የቤቶች ልማት ፕሮግራሞች ወደ ላይ እድገት ላይ ያተኮሩ አዳዲስ 3 ዲዛይኖች፣ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ዞኖች ለሚገነቡ 19 መኖሪያና መኖሪያ ያልሆኑ የመገልገያ ግንባታዎች በድምሩ 27 ዲዛይኖች ላይ የነበሩ ክፍተቶች ተለይተው መሠረታዊ የዲዛይንና የዋጋ ለውጥ ሳያስከትሉ እንዲሻሻሉ የተደረገ ሲሆን ከነዚህም በተጨማሪ በፌዴራል 2 እና በክልሎች 14 በድምሩ 16 ዲዛይኖችን የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ለፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶችና ተቋማት የቢሮ ክላስተር

ጥናትና ዲዛይን የተጀመረ ሲሆን፣ በጋራ በቤት ሕብረት ሥራ ማህበራት ለሚገነቡ ቤቶች የመጀመሪያ ዙር ዲዛይን ተዘጋጅቶ ዝርዝር ዲዛይኖችን የማዘጋጀት ስራ ላይ ይገኛል፡፡ የፌደራል ዳኞችን መኖሪያ ቤት ዝርዝር ዲዛይን፣ የፌዴራል የመሬት ተቋማት የሚገነባበትን ቦታ የአፈር ምርመራ ሥራ የአማካሪ ቅጥርን በተመለከተ በወጣው ጨረታ መሰረት አሸናፊው የተለየ በመሆኑ በቀጣይ የቅጥር ውል ተፈጽሞ ወደ ስራ የሚገባ ይሆናል፡፡

### 2.4.5. የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም አፈጻጸም፡-

የአገር አቀፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ከማሳካት አንጻር ያረጁና የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን ለማሻሻልና የመኖሪያ ቤት ዕጥረትን ለመቅረፍ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የአገር አቀፍ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ለማሳካት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሼዶች፣ የስኳርና ማዳበሪያ ፋብሪካ ቤቶች፣ ቀድመው የተጀመሩና አዲስ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በድምሩ 150,523 ቤቶች እንዲገነቡ፣ ቀደም ሲል በክልሎችና በድሬዳዋ አስተዳደር የተጀመሩ 12,396 እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግንባታቸው የተጀመሩ 71,127 የጋራ ቤቶች በድምሩ 83,523 መኖሪያ ቤቶች እና በአዲስ አበባ የተጀመሩት 24,288 የ10/90 አነስተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የጋራ መኖሪያ ቤቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ እንዲሁም ያልተላለፉትን ቤቶች የሚተላለፉበትን መንገድ ለማመቻቸት ከክልሎችና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ጋር የጋራ የውይይት መድረኮች በማመቻቸት የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተጠናክሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሰረት የድሬዳዋ አስተዳደር በጀት በመመደብ ግንባታውን አጠናቆ ለተጠቃሚው ለማስተላለፍ እየሰራ ሲሆን የአማራ እና የሐረሪ ክልሎች የነበረባቸውን ዕዳ ሙሉ በሙሉ እንዲዘጉ ተደርጓል፡፡ ሌሎች ክልሎች በ2000 በጀት ዓመት በክልሎች ግንባታቸው ከ80 በመቶ በታች የሆኑት የየራሳቸው አማራጮች በማፈላለግ እንዲያስተላልፉ፣ ከ80 በመቶ በላይ የደረሱት ደግሞ ለአፈጻጸሙ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት ተጠቃሚዎችን ለይተው ከባንክ ጋር እንዲያስተሳስሩ የተቀመጠውን አቅጣጫ ተከትሎ ክልሎችና ድሬዳዋ ከተማ የተጀመሩ ቤቶችን የማጠናቀቅና የማስተላለፍ ሥራዎች በመሥራትና በተለይም ቤቶቹን ሙሉ በሙሉ የማስተላለፍና ከባንክ ጋር የማስተሳሰሩ ሂደት የተጓተተ ነው፡፡

በሌላ በኩል የመኖሪያ ቤቶች ልማት ፕሮግራሙ በስፋት ተጠናክሮ በቀጠለበት በአዲስ አበባ ከተማ በ2003 እና በ2004 ዓ.ም በ20/80 ፕሮግራም የተጀመሩ 71,127 ቤቶች ግንባታ አፈጻጸም በአማካይ 90% የደረሰ ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት ግንባታቸውን ለመጀመር ከታቀዱ 50,000 ቤቶች ውስጥ የ3,000 ቤቶች የግንባታ አፈጻጸም 4.5% ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ በ10/90 ቤቶች ልማት ፕሮግራም በመገንባት ላይ የሚገኙ 24,288 ቤቶች አማካይ የግንባታ አፈጻጸም 62.17% ደርሷል፡፡ በሌላ በኩል በ40/60 የቁጠባ ቤቶች ግንባታን በተመለከተ በ2005 ዓ.ም በሰንጋተራ እና ክራውን ሳይቶች የተጀመሩ 1,292 ቤቶች

በአማካይ 45.29% አፈጻጸም ላይ የሚገኝ ሲሆን በ2006 የተጀመሩ 2,208 ቤቶች ግንባታ 18.07% ማድረስ ተችሏል፡፡ የቀሪዎች 9,792 ቤቶች የቅድመ ዝግጅት ስራው ተጠናቋል፡፡ በአጠቃላይ የግንባታዎቹ አፈጻጸም ዝቅተኛ ሲሆን ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሱት ውስጥ የመሰረተ ልማት አቅርቦት ችግር፣ የግንባታ ግብዓት አቅርቦት ስርጭትና አጠቃቀም ችግር፣ የሥራ ተቋራጮች፣ የአማካሪና ኩባንያዎቹ ብቃት ማነስና ያለው የባለሙያ እጥረት እንዲሁም የክትትልና ድጋፍ ውስንነት ናቸው፡፡

የስኳር ልማት ቤቶች ግንባታ በ5 አዳዲስ የልማት አካባቢዎች ማለትም በጣና በለስ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ወልቃይት፣ ፊንጫና ከሰም ከ2003 ጀምሮ በተለያየ ጊዜ የተጀመሩ በርካታ ሰፋፊ የስኳር ኢንደስትሪዎች የሚያስፈልጉ መኖሪያ ቤቶችና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 17.25% በማከናወን አጠቃላይ የግንባታው አማካይ አፈጻጸም 88.4% ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ 4,529 መኖሪያ ቤቶችንና 251 ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ተቋማትን በድምሩ 4,780 ቤቶችና ተቋማት ውስጥ 2,481 ቤቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነዋል፡፡ ለግንባታው መዘግየት ከሚጠቀሱት ዋና ዋና መንስኤዎች የመሰረተ ልማት አለመሟላት፣ የግንባታ ግብዓት እጥረት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ወጥ አለመሆንና የባለድርሻ አካላት አለመናበብ ለአብዛኛዎቹ ግንባታዎች አለመጠናቀቅና ለአዳዲሶቹም አለመፋጠን የሚጠቀሱ ዋና ዋና እጥረቶች ናቸው፡፡

የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ግንባታን በተመለከተ የዘመናዊ ፕሮጀክት አመራርን ለመተግበር፣ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ለሁሉም አመራርና ሠራተኛ የካይዘንና ዘመናዊ ፕሮጀክት ማኔጅመንት ለመተግበር የሚያስችል ሶፍት ዌር ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የ14 የመንግስት ቢሮዎች ግንባታን በተመለከተ የ4ቱ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ሲሆን አጠቃላይ የቢሮዎች ግንባታ አማካይ የአፈጻጸም ደረጃ 59.45% ላይ ደርሷል፡፡

ለማዳበሪያ ፋብሪካ ቤቶች ግንባታ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ የአፈር ምርመራና የዲዛይን ስራዎች ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ የኢንዱስትሪ ዞን ልማትን በተመለከተ ከአምስት የኢንደስትሪ ዞኖች ውስጥ በቦሌ ለሚ ኢንደስትሪ ዞን በ2004 ዓ.ም ግንባታቸው የተጀመረው የ5 ሼዶች ሙሉ በሙሉ ተጠናቀው ርክክብ የተፈጸም ሲሆን በ2006 የተጀመሩት 15 ሼዶች ግንባታ 60% ለማከናወን ታቅዶ 42.76% ደርሷል፡፡

## 2.4.6. የቤቶች ማስተላለፍና የፋይናንስ ሥራዎች፣

በመንግስት አስተባባሪነት ለሚገነቡ ቤቶች ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ብር 4 ቢሊዮን በቅድሚያ ስለመቆጠቡ ክትትል ለማድረግ በታቀደው መሰረት ከ20/80 ተመዝጋቢዎች ብር 1.09 ቢሊዮን፣ ከ10/90 ተመዝጋቢዎች ብር 0.023 ቢሊዮን፣ ከ40/60 ተመዝጋቢዎች ብር 2.69 ቢሊዮን እንዲሁም ከመኖሪያ

ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተመዝጋቢዎች ብር 0.31 ቢሊዮን በድምሩ ብር 4.1 ቢሊዮን (102.5%) መቆጠቡ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል በአዲስ አበባ ለሚካሄዱ የቤት ልማት ፕሮግራሞች የውጭ ምንዛሪ 50 ሚሊዮን USD በማስፈቀድ በስራ ላይ መዋሉን ክትትል ለማድረግ ታቀዶ 69.3 ሚሊዮን USD (138%) ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 42 ሚሊዮን USD በአዲስ አበባ ቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ለአርማታ ብረት ግዥ እንዲሁም 27.3 ሚሊዮን USD የሚሆን በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ለብረት፣ ለፒ.ቪ.ሲ ግዥ፣ ለአክሰሰሪና ሌሎች ግዥዎች የሚውል ኤል. ሲ ተከፍቶ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአዲስ አበባ በተቀናጀ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፕሮግራም ቀደም ሲል ግንባታቸው ለተጀመሩ እና በ2006 አዲስ ለሚጀመሩ ቤቶች ብር 6 ቢሊዮን የቦንድ ሽያጭ በማስፈቀድ ጥቅም ላይ መዋሉን ለመከታተል በታቀደው መሰረት በ2006 በጀት ዓመት ለአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ብር 4.75 ቢሊዮን እንዲሁም ብር 1.25 ቢሊዮን ለአዲስ አበባ ቁጠባ ቤቶች ልማት (40/60) በጠቅላላው ብር 6 ቢሊዮን የቦንድ ሽያጭ ብድር ጸድቋል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ9 ወር ብር 4 ቢሊዮን ወጪ ለማድረግ ታቅዶ ብር 3.7 ቢሊዮን (93%) ወጪ ሲሆን ይህም በአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ብር 3.175 ቢሊዮን እና ብር 525 ሚሊዮን በቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራዝ ወጪ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከቦንድ ሽያጭ ወጪ ከተደረገው ብድር ብር 6 ቢሊዮን ብድር ውስጥ በዘጠኝ ወራት ብር 2 ቢሊዮን ለማስመለስ ታቅዶ ዋና ገንዘብና ወለዱን ጨምሮ ብር 2.49 ቢሊዮን (124%) ብድር በ9 ወር ተመልሷል፡፡ ሆኖም የአዲስ አበባ ቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ከሚበደረው ቦንድ በየሩብ ዓመቱ የሚታሰብ ሲሆን ይኸውም በየጊዜው ከሚለቀቀለት ብድር እየተቀነሰ እንዲከፍል እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት ኢንተርፕራይዙ በ9 ወራት ብር 46.06 ሚሊዮን ወለድ የከፈለ ሲሆን ይህም የፋይናንስ አጠቃቀሙ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ያልተላለፉ ቤቶች ያሉባቸው የክልል ቤቶች ልማት ፕሮጀክቶች ቀሪ ዕዳን በተመለከተ ኦሮሚያ ብር 953 ሚሊዮን፣ ደቡብ ብር 345 ሚሊዮን፣ ትግራይ ብር 418 ሚሊዮን፣ ድሬዳዋ ብር 84.57 ሚሊዮን አለባቸው፡፡ ለክልል ቤቶች ግንባታ በጀት እጥረት መኖሩ፣ ቤቶቹን የማጠናቀቅና የማስተላለፍ ስራዎች በመጓተታቸው፣ የማስፈጸም አቅም ማነስና የባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶ ያለመስራት ችግሮች መኖር የብድር አመላለሱ እንዲዘገይ አድርጓል፡፡

በክልሎችና በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክቶች ለኮንዶምኒየም ቤቶች ግንባታ በሀገር ውስጥ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ አመላለስን በተመለከተ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ብር 250 ሚሊዮን እንዲመለስ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ብር 99.41 ሚሊዮን (40%) ተመላሽ ሆኗል፡፡

በክልሎችና በድሬዳዋ ተገንብተው ካልተላለፉ 12,396 ቤቶች ውስጥ በዘጠኝ ወራት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለማስተላለፍ ከታቀደው ውስጥ 3,864(31.2%) ቤቶች ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 704 ያህሉ ለሴቶች የተላለፈ ነው፡፡

## 2.4.7. የፌደራል የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር ሥራዎች፣

ቀደም ሲል ይቀርቡ በነበሩት የሚኒስቴር መ/ቤታችን ሪፖርቶች የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የተሰጠውን ተልዕኮ በመወጣት ላይ ክፍተቶች እንደነበሩበት ሲገለጽ ቆይቷል፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባካሄደው የሱፐርቪዥን ጥናት ላይ ተመርኩዞ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ትግበራውን ሲከታተል ቆይቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የሚከተሉት ዋና ዋና ሥራዎች ተከናውነዋል፡-

### i. የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች ዝግጅት በተመለከተ

ኤጀንሲውን ስትራቴጅክ በሆነ መንገድ ለመምራት የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ረቂቅ ፖሊሲ ሠነድ ተዘጋጅቶ ውይይት የተካሄደበት ሲሆን ከውይይቱ በተገኘው ግብዓት የማደበር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጁ የሚታዩ ክፍተቶችና የአዋጁ ማስፈፃሚያ ደንብ ሊያካትታቸው የሚገባቸው ጉዳዮችንም የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን፣ ከታገዱት ስድስት መመሪያዎች መካከል የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ፀድቆ ተግባራዊ ሲደረግ፤ የጥገናና ዕድሳት መመሪያና የኪራይ ተመን መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በቅርቡ በሚ/ር መ/ቤቱ አመራር ውይይት ተደርጎበት እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡

### ii. የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍታት በተመለከተ፡-

በሱፐርቪዥን ጥናት ከተለዩት ጉዳዮች በተከራይ አከራይ መመሪያ በተወሰደው እርምጃ ላይ ከቀረቡት አቤቱታዎችና ቅሬታዎች መካከል 150 የሚሆኑ ባሉበት እንድቀጥሉ፣ 106 ደግሞ ማስተካከያ ሲደረግባቸው፣ 26 ጉዳዮች በፍርድ ቤቶች ተይዘው ስላሉ እልባት አልተሠጠም፡፡ የተቀሩት 8 ጉዳዮች ውስብስብ ስለሆኑ በተጨማሪ ማጣራት ስራ እየተሰራባቸው ይገኛል፡፡ ከዚህም

በሌላ በኩል ደግሞ የኤጀንሲውን መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ተከትሎ የተቀነሱ 292 ሠራተኞች ጉዳይ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርና የሰራተኞቹ ተወካዮች ጋር በተደረገው ውይይት እድሜያቸው ለጡረታ የደረሱትን በጡረታ እንድወጡ፣ እድሜያቸው ለጡረታ ያልደረሰ ዳረጎት እንዲወስዱና በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበር ተደራጅተው ሲመጡ የንግድ ቤት በኤጀንሲው ተሰጥቶአቸው ለማቋቋም አማራጮች ቀርበው ውይይት እየተደረገበት ሲሆን፣ ከሁሉም ሠራተኛ ስምምነት ሲገኝበት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በኤጀንሲው መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ የተገልጋዮች የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ማኑዋል፣ የኪራይ ሰብሳቢነትን ለመታገል የሚያግዝ ስትራቴጅክ ሰነድና የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጎዋል።

### iii. የለውጥ ሥራዎች በተመለከተ፣

በኤጀንሲው የለውጥ መሳሪያዎች ተግባራዊ ያልሆኑበት በመሆኑ ፈጣን ለውጥ ከሚሹ ጉዳዮች ጀምሮ የተቋሙ ሰራተኞች ማንነትን የሚገልፅ ባጂ፣ ስምና ሃላፊነት፣ የአገልግሎት ስታንዳርድ፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ለተጠቃሚ በግልፅ ቦታ ማድረግ፣ እያንዳንዱ ሰራተኛ የየእለት ስራውን የመመዝገብና በየዕለቱ የመገምገም ባህል እንድያዳብር በመደረግ ላይ ይገኛል።

በኤጀንሲው የልማት ሠራዊት ለመገንባት በለውጥ ሠራዊት አስፈላጊነትና በለውጥ ቡድን(1ለ5) አደረጃጀትና አሰራር ላይ ስልጠና ተሰጥቶ፤ የኤጀንሲውን ሠራተኛ በ34 የልማት ቡድንና በ165 የ1ለ5 አደረጃጀት በማደረጃት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲገቡ በመድረግ ላይ ሲሆን፣ ልማታዊ የቤቶች አስተዳደር ሠራዊት ግንባታ ማኑዋልም ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

### iv. የቤቶች መረጃ የማጥራትና ካርታ ማውጣት በተመለከተ፣

ኤጀንሲው የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች በቁጥርና በአድራሻ ለመለየት በተደረገው እንቅስቃሴ በአዲስ አበባና ድሬደዋ በድምሩ 12,042 መኖሪያ ቤትና 5,507 የድርጅት ቤት በጠቅላለው 17,549 እንዳሉ ታውቋል። የቤቶች መረጃ አያያዝን ዘመናዊ ለማድረግ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተጀመረውን የተቀናጀ የቤቶች መረጃ አስተዳደር ስርዓት (ሲስተም) ግንባታ ከ90% በላይ የተሰራ ሲሆን የቤቶች ቆጠራ መረጃና ጂ.አይ.ኤሲ ወደ ሲስተሙ የማስገባት ሥራ ተጀምሯል።

ከዚህ በተጨማሪም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ላልወጣላቸው 448 ቤቶች ውስጥ 197 ቤቶች መረጃ ተሟልቶ ለካርታ ዝግጅት ስራ ሲተላለፍ፤ የ178 ቤቶች መረጃዎች በመደራጀት ላይ ይገኛል። 73 ቤቶች ደግሞ የተለያየ ችግር ያለባቸው መሆናቸው ተለይቷል። እስከሁን ድረስ በአዲስ አበባ የ13,813 ቤቶች ካርታ ወጥቶ ኤጀንሲው የተረከበ ሲሆን የ1,020 ቤቶች ካርታ ደግሞ ከየክፍለ ከተማዎች ለመረከብ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ይገኛል። በድሬደዋ ከተማም ካርታ ላልወጣላቸው 965 ቤቶች ካርታ እንዲወጣላቸው የሚያስፈልጋቸው በጀት ተላልፏል።

### 2.4.8. የከተማ ቤቶች መረጃ አስተዳዳር እና ድጋፍ ሥራዎች፣

በበጀት ዓመቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ 20,890 ካርታ ያልወጣላቸው የመንግስት ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወጥቶላቸው እንዲመዘገቡ ለማድረግ ታቅዶ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚያስተዳድራቸው 2,994 (ኪራያቸው ከብር 100.00 በላይ የሆኑ) የመንግስት ቤቶች ውስጥ ለ2,780 ቤቶች እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው 1,950 (ኪራያቸው ከብር 100.00 በላይ የሆኑ) የመንግስት ቤቶች ውስጥ ለ524 ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈው ዘጠኝ ወራት በአማራ እና በድሬዳዋ ለ3,304 የመንግስት ቤቶች ካርታ የተዘጋጀ ሲሆን ሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችን በተመለከተ በደቡብ ክልል ለሚገኙ 9,425 እና በአዲስ አበባ 80,000 የመንግስት ቤቶች ካርታ ለማዘጋጀት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ ይገኛሉ፡፡

## 2.5. የተቀናጀ የከተማ መሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች፡-

የከተሞችን መሠረተ ልማት አቅርቦትና ማኔጅመንት በተቀናጀና አቅሙ በተገነባ የሰው ኃይል ለማከናወን እንዲቻል ለ827 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በUGDP, LUSUP ለ38 እና በከተሞች መሰረተልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት አሀድ ለ388 በድምሩ ለ426 (51.5%) አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዘርፉ የተዘጋጁትን የፕሮግራም ሰነዶች ለማስፈፀም ብር 2.785 ቢሊዮን ከተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች እንዲገኝ ለማድረግ 11 የፕሮጀክት ሰነዶች ለማዘጋጀት ታቅዶ 4 (36.36%) ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚሁ መነሻነት ከአለም ባንክ ጋር በተደረገ የፋይናንስ ዕገዛ ስምምነት ለቀጣይ 5 ዓመታት የሚውል ከዕቅድ በላይ 7.4 ቢሊየን ብር ፈንድ የተፈቀደ ሲሆን ገንዘቡን በሥራ ላይ እንዲውል የማጽደቅ ሥራ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በከተሞች ከሚታዩ የልማት ማነቆዎች የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ችግር ለመፍታት ባለፉት ዘጠኝ ወራት በUGDP እና በULGDP ፕሮጀክቶች 141.31 ኪ.ሜ የጌጠኛ ድንጋይ/Cobblestone/ መንገድ ለማንጠፍ፣ 62.6 ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ ለመስራት፣ 81 ድልድይና ካልቨርት፣ 79.5 ኪ.ሜ የመንገድ መብራት መስመር ለመዘርጋት፣ 31 ኪ.ሜ የውሃ መስመር ለመስራት፣ 6 የገበያ ማዕከላና 4 የመሸጫ ሼዶች እና 354 የህዝብ የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዷል፡፡ ከዚህ አኳያ በሁለቱም ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ 104.8 ኪ.ሜ (74%) የጌጠኛ ድንጋይ/Cobblestone/ መንገድ ንጣፍ፣ 52.82 ኪ.ሜ (84.4%) ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ፣ 17(21%) ድልድይና ካልቨርት፣ 79.6 ኪ.ሜ (62%) የመንገድ መብራት መስመር ዝርጋታ፣

30.6 ኪ.ሜ (98.7%) የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ 10 የገበያ ማዕከላት (166.7%)፣ 13 የመሸጫ ሼዶች እና 26 (7%) የህዝብ የጋራ መፀዳጃ ቤት መገንባት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ በዕቅድ ያልተያዙት 3 ፓርኮችና አረንጓዴ ቦታዎች ግንባታ ተከናውነዋል፡፡

ሌላው ከተቀናጀ የመሰረተ-ልማት አቅርቦት ጋር በተያያዘ የማስፈጸሚያ የህግ ማዕቀፍ ሰነድ አዘጋጅቶ ለ1,151 የክልልና የከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት በሥራ ላይ በማዋል በ48 ከተሞች የተለያዩ የከተማ መሰረተ-ልማት ግንባታዎችን ለማከናወን የታቀደው ግብ የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማት ስትራቴጂና የህግ ማዕቀፍ ዝግጅት ላይ ጊዜ በመሥጠቱ ምክንያት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያልተገባ በመሆኑ ስራውን ለመፈፀምን አልተቻለም፡፡

## 2.6. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ስራዎች፡-

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚካሄደውን የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና የማሽነሪ ምዝገባ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የደረሰበትን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳትና በአግባቡ ለመምራት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለማሻሻል በዕቅድ በማካተት ተለያዩ ሥራዎች ሲካሄዱ ቆይቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የሥራ ተቋራጮች፣ ባለሙያዎች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥን የተቀላጠፈና ፍትሐዊ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወሰደው አቋም በዕቅዱ መሠረት አደረጃጀቱንና የአሠራር ሥርዓቱን በመፈተሽ የማስተካከያ ጥናት እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር በዘላቂነት ለማስወገድ የሚካሄደው የሥርዓት ማሻሻያ እንደተጠበቀ ሆኖ ወቅታዊ ምላሽ መስጠት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ በጊዜያዊነት ባለሙያዎች በመመደብ፣ ሰፊ የደንበኞች ማስተናገጃ ቢሮ በማደራጀት፣ አሰራሩን ቀልጣፋ በማድረግ የደንበኞችን ፍላጎት ለማርካት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም ጅምር አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

በዘጠኝ ወራት ውስጥ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ ሥራ ተቋራጭና አማካሪ ድርጅቶች አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል ከደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ ለሚሳተፉ ለ105 ሥራ ተቋራጮችና 42 አማካሪዎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 87 (203%) አማካሪዎች እና 136 (131%) የተለያዩ የሥራ ተቋራጮችን የወከሉ ሰዎች በተሳተፉባቸው ሁለት መድረኮች ስለ ISO 9001/2008 የጥራት ሥራ አመራር ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችሉ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ ይህም የግሉን ዘርፍ አቅም ከመገንባት አኳያ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽ ዕቅድ የተጣሉ ግቦች እየተሳኩ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

ዘርፉን የሰው ሀይል ልማት በማሳለጥ የተቋራጮችና የአማካሪዎችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ከትምህርት ሚኒስቴር /ምዘና ማዕከላት ጋር በቅንጅት በመስራት በዕቅዱ መሠረት 136 አዲስ መሪ መዛኞችን ለማፍራት የተቻለ ሲሆን ቀደም ሲል ያፈራናቸውን 700 መሪ መዛኞችን የሥራ ትብብር ተፈጥሮ ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በተያያዘ 500,000 ዝቅተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ቅድመ ምዘና ምዝገባ ለማከናወን ታቅዶ 78,996 (15.8%) ተከናውኗል፡፡ በመጀመሪያ ዙር 51,018 (28.92%) ዝቅተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች የተመዘኑ ሲሆን 23,926 (29.3%) ባለሙያዎች ደግሞ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በመጀመሪያ ዙር ምዘናውን ማለፍ ላልቻሉ ባለሙያዎች የክህሎት ማሟያ የኩባንያ ትብብር ስልጠና ለመስጠት ቢታቀድም የምዝገባ ጊዜው በመራዘሙና ወደ ምዘና ዘግይቶ በመግባቱ አልተከናወነም፡፡

በአጠቃላይ የሰው ኃይል ምዝገባና ምዘና አፈጻጸሙ ከዕቅድ አንጻር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለአፈፃፀሙ መቀነስ በምክንያትነት ከሚጠቀሱ ችግሮች ዋና ዋናዎቹ፡- የምዘና ስራው በክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ተገቢ አደረጃጀት ተፈጥሮና በባለቤትነት ተይዞ እየተከናወነ አለመሆኑ፣ በክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የምዝገባ ሥራውን ለማከናወን የሎጅስቲክና ፋይናንስ እጥረት መኖሩ እና የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች በምዘናው ሥራ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ቢሆንም ከተሰጠው ሰፊ የግንዛቤ መፍጠር ሥራ አንጻር ተሳትፏቸው በጣም ውስን መሆኑ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችን በመደገፍና ባለድርሻ አካላትን በማንቀሳቀስ አፈጻጸሙን ለማሻሻል ርብርብ ይደረጋል፡፡ አሰራሩን የአነስተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች አንድ የቅድመ-ምዝና ምዝገባና ምዘና መመሪያ ተዘጋጅቶ ለክልሎች የተሰራጨ ሲሆን ባለሙያዎች በአካል በመገኘት ግንዛቤ የመፍጠርና የማስተዋወቅ ስራ የሰሩ ሲሆን ክልሎችም ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር አጣጥመው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ በሌላ በኩል የወጪ መጋራት እና የሥራ ቅጥር፤ ዝውውርና ስንብት ሥርዓት መመሪያን የማዘጋጀትና በተነሱ አስተያየቶች መሰረት የማጠናቀቁ ስራ ተከናውኗል፡፡

የሕንፃ አዋጅ፣ ደንብና ተጓዳኝ መመሪያዎችን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ክልሎችና ከተሞች አሁን ያሉበትን ደረጃ በማመዛዘን የሕንፃ አዋጅ፣ ደንብ እና ተጓዳኝ መመሪያዎች 65 ከመቶ ያህል ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የሕንፃ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንባቸው 271 ከተሞች መካከል በዘጠኝ ወራት በ 66 ከተሞች አስፈላጊ አደረጃጀት እንዲፈጠር እና ወደ አፈፃፀም እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ በ80(121.2%) ከተሞች አስፈላጊ አደረጃጀት ተፈጥሮ ወደ አፈፃፀም ተገብቷል፡፡ የሕንፃ ህጉ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው 271 ከተሞች የሚገነቡ 8018(71%) የሚገመቱ ሕንፃዎች በሙሉ የግንባታ ፈቃድ ያገኙ ሲሆን 194(3.62%) ሕንጻዎችም የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ አንድ በማዕከል፣ 10 ክፍለ ከተማ እና 116 ወረዳዎች አዋጁ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በክልሎችና

የከተማ አስተዳደሮች ተገቢ አደረጃጀት ተፈጥሮና በባለቤትነት ተይዞ እየተከናወነ ባለመሆኑ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሆኗል፡፡

ለኢንዱስትሪው አስፈላጊ የሆኑ 19 ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንደርዶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ 4ቱ የጸደቁ ሲሆን 17ቱ ደግሞ በመጨረሻ የረቂቅ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሠረት በሥራ ላይ የሚገኙት 11 የሕንፃ ኮድ ስታንዳርዶች (1995) የማሻሻልና 3 አዳዲስ ሠነዶች ዝግጅት ሥራ፣ ቋሚ የሥራ ዝርዝርና የመለኪያ ዘዴ (Standard Specification and Method of measurement)፣ የኮንስትራክሽን ምዝገባ አዋጅ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ማቋቋሚያ ደንብ፣ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የኪራይ አገልግሎት መመሪያ፣ የመሰረት ልማት ቅንጅታዊ አሰራር ደንብ እና ብሄራዊ የኮንስትራክሽን ምዝገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ  የመጨረሻ ረቂቅ ሰነዶችን ተዘጋጅተው በማፀደቅ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ የንኡስ ሥራ ተቋራጭነት፣ የተባባሪ (Local Countrpart) እና የሽሙር (Joint Venture) አሰራር ሥርዓት በተመለከተ ጥናቱ ተጠናቆ ለውሳኔ ቀርቧል፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ እና ሁለት የምዝገባ መመሪያዎችና የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ ደንብ ሰነዶች ተዘጋጅተው እንዲጸድቁ ተደርገዋል፡፡ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትም 50 በመቶ ለማሳደግ በሚዘጋጁ ሰነዶች እንዲካተት ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የዘርፉን እንቅስቃሴ በህግ ማዕቀፍ የተደገፈ እንዲሆን ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከፍተኛ እንቅስቀሴ የተደረገ ሲሆን በቀጣይ ሁሉንም በማጸደቅ ወደ ትግበራ እንዲገቡ ጥረት ይደረጋል፡፡

በአካባቢ የግንባታ ግብዓቶች ላይ ምርምርና ሥርጸት ጥናት ከማድርግ አኳያ 5 ዩኒቨርሲቲዎችን በጥናቱ ለማሳተፍ በእቅድ ተይዞ 3ቱ የጥናት መነሻ ሃሳቦች/ ፕሮፖዛል በማቅረብ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ የተመረጡ ዩኒቨርስቲዎች በ4 አዳዲስ እና የተሻሻሉ ወጪ ቆጣቢ የአካባቢ ግንባታ ግብአቶች ላይ  ምርምር ለማካሄድ ቢታቀድም አንዱ ብቻ የተዘጋጀ ሲሆን ለግብዓቶች ደረጃ የማውጣት ሥራ ግን ገና ያልተጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በቀሩት ወራት የማካካሻ ሥራ ለማከናወን ጥረት ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል አዳዲስና የተሻሻሉ ወጪ ቆጣቢ ግንባታ ቴክኖሎጂዎችን ከማዘጋጀት አኳያ  በዕቅዱ መሠረት የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እያተዘጋጀላቸው ካሉት 2 የጥናት መነሻ ሃሳቦች በፕሪካስት ስላብ ላይ አንዱን ቴክኖሎጂ እያዘጋጀ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ በትግራይ ክልል ተዘጋጅተው ከተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች ውስጥ በአክሱም ቴክኒክ ኮለጅ ሞልድ ኮንክሪት ኮብል ስቶን መስራት የሚችል ቴክኖሎጂ እየተዘጋጀ ነው፡፡

ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከዚህ በፊት ደረጃ በወጣላቸው የግንባታ ግብዓቶች ላይ የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ቀደም አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸው 20 የግንባታ ግብዓቶች የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር እንዲደረግ ከደረጃዎች ኤጀንሲ 23 አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸው የግንባታ

ግብዓቶችና ለግንባታ ግብዓትነት የሚውሉ 21 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ዝርዝር የመቀበል ሥራ ተከናውኖ ለ9 ክልሎችና ለ2 ከተማ አስተዳደሮች የተሰራጨ ሲሆን በግንባታ ግብዓቶች ላይ የሚደረገውን የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር አፈፃፀም ሥራም በመስክ ጉብኝትም ጭምር በመታገዝ ተከታትሎ ለመደገፍ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ከአመታዊ የኮንስትራክሽን ተዋናዮችና መሳሪያዎች ምዝገባ አኳያ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 22,717(108%) መለስተኛና ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ 3,815 (62.65%)የስራ ተቋራጮች፣ 220 (87.6%) አማካሪዎች እና 1,505(97.72%) የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባና ሌሎች መረጃ ከማጥራትና ከማደራጀት ጋር የተያያዙ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በሌላ በኩል የ81,632 አነስተኛ ባለሙያዎች ምዝገባ ለማካሄድ በዕቅድ ቢያዝም ባለመቅረባቸው ምክንያት አልተመዘገቡም፡፡ በመሆኑም ከምዝገባ ጋር ተያይዞ ከአነስተኛ ባለሙያዎች ምዝገባ በስተቀር በሌሎች የተሻለ አፈጻጸም የተመዘገበ በመሆኑ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በቅርቡ በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 289/2005 የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በተመለከተ በያዝነው ዓመት ኢንስቲትዩቱን የማደራጀትና የሰው ኃይል ማሟላት ለማከናወን በዕቅድ ተይዞ እየተተገበረ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት ስራዎችን በተገቢው መንገድ የማደራጀት፣ አብሮ የሚጓዙ ተግባራትን ባንድ ላይ አስተሳስሮ ለማስኬድ እና ለስራ የሚያስፈልገውን ሀብት /ሪሶርስ/ ለይቶ ለማወቅ፣ የሚያስፈልገውን ሰው ሀይል በሙያ ዓይነትና ደረጃ ለይቶ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ለመስጠት፣ የስራዎቹን ቅደም ተከተል በማውጣት ዕቅድ ለማዘጋጀትና በዚሁም መሰረት ኢንስቲትዩቱ ቶሎ ወደ ስራ መግባት የሚችልበትን የመሸጋገሪያ ምዕራፍ የሚያመቻች ሰባት /7/ አባላትን የያዘ አደራጅ ኮሚቴ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሰይሞ ሥራ ጀምሯል፡፡

በዚሁም መሰረት ባለፉት ጥቂት ወራት ከተከናወኑት ዋና ዋና ሥራዎች መካከል ተቋሙን ማደራጀት በተመለከተ በሃገር ውስጥ ያሉ ተመሳሳይ መ/ቤቶችን አደረጃጀት ጥናት ተከናውኗል፣ ኢንስቲትዩቱን በቁልፍ ተግባራት ላይ ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል መዋቅር ማዘጋጀት፣ የስራ ዝርዝር ማውጣትና የአደረጃጀት መዋቅር፣ የስራ ምደባ፣ የደመወዝ እስኬልና የዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ መስፈርት ዝግጅት ተከናውኗል፡፡ አጠቃላይ የተቋሙ የሰው ሃይል ፍላጎትና መዋቅር የተዘጋጀ ሲሆን ለአሁኑ ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል 40 የሚሆኑ ሰራተኞች ፍላጎት ተለይቶ በቀሪዎቹ 3 ወራት የሚያፍልገውን ግብአት ከዚሁ አንጻር ተሰልቶ ቀርቧል፣

ከዚህ በተጨማሪ የቴክኖሎጂ ሽግግርን አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜያቶች ወደሃገራችን በመምጣት በኢቨስትመንት ሥራ ለመሰማራት ፍላጎት ካሳዩ የውጭ ኩባኒያዎች መካከል ከኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ጋር ቅርበት ያላቸው ድርጅቶቸን በማነጋገር በተለይ ከቤቶች ልማት አንጻር ጉልህ ሚና የሚኖራቸው

በደቡብ ኮሪያ የሚገኝ KOS Group የተባለ ኩባንያ እንዲሁም መሠረቱ በአሜሪካ የሆነውን NextGen Framing system, LLC የተባሉ ኩባንያዎች ለቀጣይ ግንኙነት ተመርጠዋል፡፡

## 2.7. የከተሞች ጽዳትና ውበት ሥርዓት ማሻሻያ ስራዎች፣

ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር የተያያዙ በፌዴራል፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች 8 የጥናት ሰነዶችን፣ ስታንዳርዶችንና የሕግ ማዕቀፎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 8 ሙሉ በሙሉ ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚሁም መሰረት በፌዴራል ደረጃ ከተሞች ሥርዓት እና ወጥነት ባለው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስታንዳርድ እንዲመሩ ከአማካሪ ጋር በመተባበር እንዲዘጋጅ በታቀደው መሰረት አንድ ስታንዳርድ እንደዚሁም አንድ ደጋፊ የስታንዳርዱ ገላጭ ሰነድ (Handbook) በማጠናቀቅ ከከተሞች ለተውጣጡ 40 ሰልጣኞች ለ 4 ተከታታይ ቀናት የአሰልጣኞች ስልጠና በመቀሌ ከተማ ተሰጥቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት የተዘጋጀውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ እንደዚሁም ከተለያዩ አካላት አስተያየቶችን በማሰባሰብ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቷል፡፡

የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓትን በተመለከተ በፌዴራል፣ በክሎሎችና በከተማ አስተዳደሮች በኩል 9 የጥናት ሰነዶችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 8ቱ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ በፌዴራል ደረጃ የህዝብ መፀዳጃ እና መታጠቢያ ቤት ማንዋል ከክልሎች እና ከሌሎች አካላት የተገኘውን ግብዓት መሰረት በማድረግ ማኑዋሉ ተዘጋጅቷል፡፡

በከተሞች የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም በከተማ ውበትና አረንጓዴነት ልማት ዙሪያ በ727 ከተሞች ለሚገኙ ለ5,613 አመራሮችና ፈጻሚዎች በ8 የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት በ7 የስልጠና መድረክ በማዘጋጀት ለ2,257 አመራሮችና ፈጻሚዎች ስልጠናው ተሰጥቷል፡፡ በተመሳሳይ በደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ለ1,490 አመራሮችና ፈጻሚ አካላት የተቀናጀ የግንዛቤ መፍጠር ወይም አመለካከትን ለማሳደግ የሚያስችል ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ2,257 አመራርና ፈጻሚ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ፣ በአረንጓዴ ልማትና በውበት ስትራቴጅዎች ዙሪያ በአካልና በፕላዝማ አማካይነት ለ12,200 (ከከተማ ፕላን ጋር የተያያዙ ስትራተጂዎችን ጨምሮ) ያህል መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ተሳታፊዎች አገር አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለማከናወን የታቀደ ቢሆንም ይህንን ሥራ ከህዝብ ንቅናቄ ሥራ ጋር በማቀናጀት እንዲተገበር ስምምነት ላይ ስለተደረሰ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ለማከናወን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

በከተማ ጽዳት (sanitaion) በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት ለ115 ሰልጣኞች ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ እንደዚሁም በከተማ ውበትና አረንጓዴ ማድረግ (Beautification and Gardening) በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ለ151 ሰልጣኞች ስልጠና እንዲሰጥ ለማድረግ የታቀዱ ሥራዎች ላይ ስርዓተ-ትምህርቱ ተዘጋጅቶ ለትምህርት ሚ/ር የተላከ ሲሆን ሥራውን በትምህርት ሚኒስቴር እንደሚያዘጋጅ ይጠበቃል፡፡

በከተሞች የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ የተዘጋጁ ህጎች፣ ስታንዳርዶችና የአሰራር ማኑዋሎች በሥራ ላይ ስለመዋላቸው በፌዴራል 12 ከተሞች እንዲሁም በ53 ከተሞች የክትትል እና ድጋፍ ስራ ተከናውኗል፡፡ ቀደም ብሎ በፌዴራል እና በክልሎች የክትትልና ድጋፍ ስራ ለተከናወነባቸው ከተሞች 22 የግብረ-መልስ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ ሕብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ በክልሎች አማካኝነት በመስፈርቱ መሰረት 95 የደረቅና 51 የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ማዘጋጀት የሚጠበቅባቸውን ከተሞች ዝርዝር ለየክልሎቹ የተሰራጨ ሲሆን በዚህም መሰረት 67 የደረቅና 22 የፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ቦታ ተዘጋጅቷል፡፡ የክትትልና ድጋፍ ስራ በተመለከተም ለክልሎች እና ከተሞች 18 የግብረመልስ ሪፖርት የተላከ ሲሆን ለዘጠኝ ወራት ከታቀደው አንጻር አፈጻጸሙ 61 በመቶው ተከናውኗል፡፡

በከተሞች 29 የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ተሽከርካሪ ግዥ እንዲፈጸም ክትትል በማድረግ በULGDP በጀት 10 የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ተሽከርካሪዎች ግዥ ተፈጸሞ ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኩልም 5 የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ተሽከርካሪዎች ግዢ ተፈፅሟል፡፡

አዲስ አበባን ጨምሮ በከተሞች 183 የህዝብ መጸዳጃና መታጠቢያ ቤቶች እንዲገነቡ፣ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ (Standard) መሰረት ስለመገንባታቸው እና (ቀድሞ የተገነቡትን ጨምሮ) በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ ለመስጠት የታቀደ ሲሆን በዚህም መሰረት መረጃ በተሰበሰበባቸው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተካደው ክትትልና ድጋፍ 108 የመጸዳጃ ቤቶች ተገንብቷል፡፡

ከአካባቢ እና ደን ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት ከኢንዱስትሪዎች፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ሌሎች ምንጮች የሚለቀቁ አደገኛ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን የመቀነስ፣ ብክለትን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ በተመረጡ 38 ከተሞች እንዲሰራ በፌዴራልና ክልሎች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በታቀደው መሰረት በ21 ከተሞች ከሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እንዲሰራ በማድረግ ብክለትን የመከላከል ስራ ተከናውኗል፡፡

በ9 ክልሎችና በ2ቱ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ በበጀት ዓመቱ 9 ወራት ለ3,920 ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ለማስቻል ክልሎችና ከተሞች የዘርፉን የስራ እድል ፈጠራ በእቅዳቸው እንዲያካትቱ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዘርፍ የስራ እድል ፈጠራ ጠቋሚ ሰነድ ለክልሎችና ከተሞች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ባለፉት 9 ወራት ለ2,674 ዜጎች(ከታቀደው 68 በመቶ) በዘርፉ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፤ ከዚህም ውስጥ 48 በመቶ ያህል ለሴቶች የተፈጠረ የሥራ ዕድል ነው፡፡

በበጀት አመቱ በአረንጓዴ ልማት እና ውበት የክትትል ድጋፍ እና ግብረ መልስ ስራ የሚከናወንባቸው ከተሞችን በመለየት ከከተማ ውበትና አረንጓዴ ቦታዎች ጋር በተያያዘ በሥራ ላይ እንዲውሉ የወጡ ህጎች እና የአሰራር ማኑዋሎች በማሰባሰብ ለከተሞች ተሰራጭቷል፡፡ የተሰራጩት ሰነዶችም የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፣ በከተሞች አረንጓዴነት ልማት የስራ እድል ፈጠራ ጠቋሚ የጥናት ሰነድ፣ የውሃ አካላቶችና ዳርቻ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ማንዋል፣ የከተማ ፕላን አዋጅ ቁ. 574/2000፣ የላንድስኬፕ አረንጓዴነት ልማት ማንዋል፣ እንዲሁም ከዘርፉ ጋር በተያያዘ የጉለሌ ክፍለ ከተማ እና የርዋንዳ ኪጋሊ የተሞክሮ ሰነድን ያካትታል፡፡ ሕጎቹና የአሰራር ማኑዋሎቹ በሥራ ላይ ስለ መዋላቸው በሁሉም ክልሎች አማካኝነት በ42 ከተሞች የክትትልና ድጋፍ ስራ ተከናውኗል፡፡

የውበትና አረንጓዴ ልማት ስራዎች በተሟላ የአሰራር ስርዓት መሰረት እንዲከናወኑ ለማድረግ እንዲቻል በፌዴራል፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በኩል 15 የጥናት፣ የህግ ማዕቀፍ፣ ስታንዳርድ እና ማንዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ 12 (80 በመቶ አፈጻጸም) ተዘጋጅተዋል፡፡ በፌዴራል ደረጃ የከተሞች ተፋሰስ ልማት ማንዋል ዝግጅት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግብዓት በማሰባሰብና ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻ ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጓል፤ የአረንጓዴ ልማትና ውበት ረቂቅ አዋጅም ተዘጋጅቶ የተለያዩ አካላት የሰጡዋቸው አስተያዬቶች ተካተዋል፤ የከተሞች አረንጓዴ ልማት ተሳትፎ ማንዋልም አስተያዬቶች ተሰጥተውበት ሰነዱ እየዳበረ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ስታንዳርድ ዝግጅት መረጃዎች በማጠናቀር የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

በ76 ከተሞች የአረንጓዴነት መሰረተ-ልማት አይነቶችን (green Infrustructure components) መሰረት ያደረገ የአረንጓዴነት ልማት እቅድ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስራዎችን በማከናወን ለ24 ከተሞች ግብረ-መልስ ለመስጠት ታቅዶ በ65 ከተሞች የአፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን ለ22ቱ ግብረ-መልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡

የውበትና አረንጓዴ ልማት ስራዎች በተሟላ የህግ ማዕቀፍ መሰረት እንዲከናወኑ ለማድረግ በታቀደው መሰረት የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን ለማሻሻል በተለዩት ችግሮች ላይ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች ጥናቶች ስለ መከናወናቸው ክትትልና ድጋፍ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ በ69 ከተሞች ከከተማ

ውበትና አረንጓዴ ቦታዎች ጋር በተያያዘ በሥራ ላይ እንዲውሉ የወጡ ሕጎችና ስታንዳርዶች በአግባቡ እየተተገበሩ ስለመሆኑ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስራዎችን ለማድረግ ታቅዶ በ 65 ከተሞች ተከናወኗል፡፡ 29 የግበረ-መልስ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 22 ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡

ከከተማ ውበትና አረንጓዴነት ልማት ጋር በተያያዘ በከተሞች 670 ሄክታር ቦታ የላንድስኬፕ ዲዛይን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲለማ ለማድረግ ታቅዶ የተለያዩ የአረንጓዴ መሰረተ ልማቶችን ያካተተ 570 ሄክታር እንዲለማ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ የላንድስኬፕ ዲዛይን በተመለከተ መሻሻል የሚገባቸውና በቀጣይም የሚጠናከሩ ጉዳዮች እንዳሉ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ከከተማ ውበትና አረንጓዴነት ልማት ጋር በተያያዘ 2,028 ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ማድረግ፣ ከሚፈጠረውም የሥራ ዕድል 50% ሴቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ባሉ ከተሞች ብቻ እንኳን ቢወሰድ 2,780 ዜጎች የስራ እድል ያገኙ ሲሆን የሴቶች ድርሻ በነዚሁ ክልሎች 1,351 ነው፡፡

## III. የሕዝብ ተጠቃሚነት ግቦች(Customer Perspective) ዕይታ፡-

### 3.1 በሚኒስቴር መስሪያቤቱ በሚሰጡ አገልግሎቶች የተገልጋይ እርካታን በተመለከተ፣

በየደረጃው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ ለማድረግ በተገልጋዮች የሚቀርቡ ቅሬታዎች በደንቡና በመመሪያው መሰረት ምላሽ እንዲያገኙ ከማድረግ አንፃር የሚ/ር መ/ቤቱ ተገልጋዮች በአካል በመገኘትና በጽሁፍ ለሚያቀርቡት ቅሬታ፣ አቤቱታ ወይም ጥቆማን በመቀበል በመመሪያው መሠረት በመመርመርና በማጣራት ለተገልጋዩ ውሣኔውን የማሳወቅ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሚ/ር መ/ቤቱ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና የሬጉላቶሪ ሥራዎች በሥራ ተቋራጮች፣ ባለሙያዎች፣ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ በአዲስ ፈቃድ አሰጣጥ እና እንዲሁም በፈቃድ እደሳት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በተገልጋዮች የሚቀርበውን ቅሬታ ለመፍታት እንዲቻል በበጀት ዓመቱ በሚ/ር መ/ቤቱ በተዘጋጀው የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍቻ አጣዳፊ ዕቅድ መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሠረት የሥራ ክፍሉን አደረጃጀትና አሰራር ለማሻሻል እንዲቻል የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናቱን የማሻሻል ሥራ በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን በቅርቡ ተጠናቆ ወደ ሙከራ ትግበራ የሚገባ ይሆናል፡፡ ጥናቱ ተጠናቆና ጸድቆ ወደ ትግበራ እስኪገባ ድረስ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች ጊዜያዊ የሰው ሀይል ዝውውር በማድረግና በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት በተጨማሪ የሰው ሀይል ለሥራው እገዛ የማድረግና በቂ

የአገልግሎት መስጫ መስኮቶችን (ዴስኮችን) ለመጨመር የሚያስችል ዕርምጃ ተወስዷል። የተሻሻለ የምዝገባ መመሪያም ጸድቆ ወደ ሥራ ገብቷል።

## 3.2 የትምህርታዊና ልማታዊ ኮሚኒኬሽንና የህዝብ ግንኙነት ስራ፣

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ እና የህትመት ውጤቶችን በመጠቀም ለሕብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት በስፋት ተደራሽ እንዲሆን ከማድረግ ረገድ በዘጠኝ ወራት ውስጥ 12 መጽሔት 54 ብሮሽርና በራሪ ወረቀት በማዘጋጀት የተሰራጨ ሲሆን በተመሳሳይ ዘርፉን የሚመለከቱ አምስት የዶኩዩመንተሪ ፊልሞች አምሳ ሦስት የተለያዩ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ፕሮግራሞች እንዲተላለፉ በማድረግ ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ የኮሙዩኒኬሽን ስራዎችን መስራት ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ የተቋሙን ሥራዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ 120 የተለያዩ የስራ እንቅስቃሴዎች በህትመትና በኤሎክትሬኒክስ ሚዲያ አማካይነት እንዲዘገቡ ተደርጓል። 50 ልዩ ልዩ መረጃዎች በፖርታልና በድህረ-ገጽ ላይ በመጫን ዘገባዎቹን በመከታተልና ወቅታዊ በማደርግ የውስጥና የውጭ ተገልጋዮች ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል። በሌላ በኩል የተቋሙን የስራ እንቅስቃሴዎች ከአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሁነቶች ጋር በማያያዝ 50 መልዕክቶች እንዲተላለፉ ተደርጓል።የዘርፉ ልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች ዙሪያ በዘጠኝ ወራት ውስጥ 108 ዜናዎች የተዘገቡ ሲሆን 6 ጋዜጣዊ መግለጫዎች ተሰጥተዋል።

ሌላው በዘርፉ የተያዙ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቀድን ከማሳካት ረገድ፤ እንዲሁም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ከማሳደግና ተሳታፊነቱን ከማረጋገጥ አኳያ 18 የፓናል ውይይቶች አንድ ፎረም፤ 20 የተለያዩ ጉባኤያት በማዘጋጀት ከህብረተሰቡ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ውይይቶች ተደርጋዋል።

በአጠቃላይ የህዝብ ግንኙነትና ልማታዊ ኮሙዩኒኬሽን ሥራችን በሳለፍነው ዘጠኝ ወራት ውስጥ በህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች አማካይነት በርካታ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ማድረስ የተቻለ መሆኑ አበረታች ሆኖ ሳለ በዘርፉ የልማት እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ወቅታዊ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ከመስጠት ረገድ ክፍተት ያለበት ሲሆን አምስት ህዝባዊ መድረኮችን ለማዘጋጀት በዕቅድ ተይዞ የማወያያ ሠነዶች ዝግጅት ጊዜ በመውሰዱ ምክንያት እስከዚህ ሩብ ዓመት አለመከናወኑ ሌላው ደካማ ጎን ነው።

## 3.3 የባለብዙ ዘርፍ ሥራዎች፣

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በዘርፉ በሚሠሩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች/ስልጠና እና የሥራ እድል ተጠቃሚነት ላይ 50% ያህሉ ሴቶች እንዲሆኑ በፌዴራል እና በክልሎች በሚዘጋጁ 11 የልማት

ዕቅዶች ውስጥ የተካተተ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ሥራ ተከናውኗል፡ የአፈጻጸም ክፍተት ለማጥበብ የድጋፍ እርምጃውን (Affirmative action) ተፈጻሚነትን ለማረጋገጥ፣ የሴቶችን ወደ ውሳኔ ሰጭነት ለማምጣት እንዲሁም ለከፍተኛ አመራር ከሚሰጠው ስልጠና ውስጥ 30% እና ለአነስተኛና መካከለኛ አመራር ከሚሰጠው ስልጠና 50% ሴቶች መሆኑን በየደረጃው በየሩብ ዓመቱ እና በዓመት በሚዘጋጁ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ውስጥ መንጸባረቃቸው የማረጋገጥ ስራ ተከናውኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢ ጥበቃና ልማትና የኤች.ይ.ቪ ጉዳዮች ሥራዎች በበጀት ዓመቱ ዕቅድ መካተታቸውና በየሩብ ዓመቱ ሪፖርታቸው አፈጻጸማቸው ተካትቶ እየቀረበ መሆኑ የማረጋገጥ ሥራ ተከናውኗል፡፡

## IV. የተቋሙ የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘረጋው የክትትል፣ ግምገማ፣ ግብረ-መልስና ድጋፍ ሥርዓት መሠረት የሴክተሩን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም የመከታተል ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ቀደም ሲል በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘረጋው የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት መሰረት በሳምንታዊ ሪፖርት፣ በእርስ በእርስ መማማር መድረክ እና በወርሃዊ ሪፖርት መነሻነት የለውጥ ሥራው አፈጻጸም ክትትል እየተደረገ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የቢሮ ማኔጅመንት በሳምንታዊ ስብሰባና የሚኒካቢኔ በየ 15 ቀኑ በሚያደርገው ቋሚ ግንኙነት ያለውን የለውጥና የልማት ስራዎች አፈጻጸም ግምገማ አካሄዷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የበላይ አመራሩ ቀደም ሲል በተቀመጠው አግባብ መሰረት የሴክተሩን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም በሁለት ደረጃዎች ግምገማ አካሄዷል፡፡ አንደኛው በየወሩ በሚካሄድ የGTP መድረክ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በእያንዳንዱ መምሪያ በምን ያህል ደረጃ እየተፈጸመ እንደሆነ በመገምገም ድጋፍ የመሥጠት እና አቅጣጫ የማስቀመጥ ሥራ ተከናውኗል፡፡ በዚህም ሂደት እያንዳንዱ መምሪያ እና ቢሮ በፈፀማቸው ሥራዎች መጠን ውጤት ተሰጥቶታል፡፡ ሁለተኛው የክትትል፣ ግምገማና የድጋፍ አግባብ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአቻ ክልል ቢሮዎች ጋር በጋራ በዓመት ሁለት ጊዜ በሚያዘጋጀው መድረክ አማካይነት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን አፈጻጸም የሚገመግምበት ሲሆን፣ በዚህ በጀት ዓመት መግቢያ ላይ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የዘርፉ ተቋማት የ2005 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ምዘና ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተዉጣጡ ባለሙያዎችን በማሳተፍ የተካሄደ ሲሆን ሪፖርቱም የሃዋሳ ከተማ ባዘጋጀው ስድስተኛው የሴክተር ጉባዔ ቀርቦ ግምገማ አካሄዷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የ2006 የበጀት ዓመትን የመጀመሪያውን ግማሽ ዓመት ምዘና በማካሄድ በአዲስ አበባ ከተማ አዘጋጅነት በተካሄደ የሰባተኛው የሴክተር ጉባዔ ሪፖርት ቀርቦ ግምገማ ተካሂዷል፡፡ በሁለቱም ጉባኤዎች የቀጣይ ጊዜያት የጋራ አቅጣጫዎችንም አስቀምጧል፡፡

## V. ከሌሎች ተቋሞች ያለው ቅንጅታዊ አካሄድና ሥራ አፈጻጸም፣

የሴክተሩን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተሟላ ሁኔታ ከማስቀጠል ረገድ ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ዕቅዶቻቸውና ፕሮግራሞቻቸው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ መሰረት የተቃኙ መሆን እንዳለባቸው እሙን ነው። ከዚህ ረገድሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ 2006 በጀት ዓመት ዕቅድ ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በሚኒስቴር መስሪያቤቱ ስር የሚገኙ ቢሮዎችና ተጠሪ ተቋማት ዕቅድ ጋር በተናበበ መልኩ የማዘጋጀትና በዚሁ መሰረት የመፈፀሙን ሂደት የመከታተል ሥራ እየተከናወነ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እና አዳዲስ በሚገነቡ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ያለዉ ድጋፍ በተመለከተ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸዉ ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ ዕቅድ አውጥቶ ተከታታይነት ያለዉ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በዘርፉ የወጡና የተሰራጩ የህግ ማእቀፎች በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋላቸዉ ክትልና ድጋፍ ተደርጓል። ከሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በየ 45 ቀናቱ ቋሚ የግንኙነት ጊዜ ተፈጥሯል። የመስክ ሥራዎች በጋራ ይገመገማሉ፣ ችግሮች ሲገጥሙ ከተቋማቱ በተውጣጡ ባለሙያዎች ጥምረት መፍትሔዎች ይፈለጋሉ። ከከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሴክተር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሀገራዊ የመረጃ ጥናቶች ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት የማስፈጸም ሥራዎች በጠንካራ መልኩ እየተከናወኑ ይገኛል።

## VI. ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ ያለበት ሁኔታ፣

የዘርፉን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት ሁሉንም ክልሎች በመደጋገፍ የሴክተሩን ዕቅድ በጋራ ለማሳካት መረባረብ አስፈላጊነቱ የጎላ ይሆናል። ከዚህ አኳያ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ 4ቱ ክልሎች የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት ተከታታይነት ያለው ድጋፍ የመስጠት ስራዎች እየተፈፀሙ ሲሆን የዘርፉ ልማት አፈፃፀም እንዲያድግ ለማስቻል ተገቢው ክትትል ተደርጓል። ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የከተማ ልማት ዘርፍ ራሱን የቻለ የተቀናጀ የ2006 በጀት አመት የልዩ ድጋፍ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በተናጥልና በጋራ የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት በስምምነቱ መሠረት እየተፈፀመ ይገኛል።

የጋራ የልዩ ድጋፍ ዕቅድ አፈፃፀምን አስመልክቶ በሚደረግ ክትትልና ድጋፍ መሠረት በጋምቤላ፣ አሶሳ፣ ሰመራ-ሎጊያ እና ጅግጅጋ ከተሞች የጋራ መድረክ በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ግምገማዊ ውይይት በማካሄድ ለየክልሉ የከተማና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት በጽሑፍ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል። ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ከተሞችን ከአራቱ ዓበይት አጎራባች የክልል እህት ከተሞች ጋር ትስስር በመፍጠር ተሞክሮ እየተለዋወጡ የማስፈፀም አቅማቸውን የበለጠ እንዲያዳብሩ ለማድረግ የሰመራ-

ሎጊያ ከተማን ከመቀሌ፣ አሶሳ ከተማን ከባህር ዳር፣ ጅግጅጋ ከተማን ከአዳማ እና ጋምቤላ ከተማን ከሀዋሳ ከተማ ጋር የእህትማማችነት የመግባቢያ ሰነድ ትስስር የተፈጠረ ሲሆን አሶሳና ባህር ዳር፣ ሰመራ-ሎጊያና መቀሌ እንዲሁም ጋምቤላና ሀዋሳ የጋራ መድረክ በማዘጋጀትና የልማት ትብብር ዕቅድ አዘጋጅተው በመፈራረም ወደ ተግባር ገብተዋል፡፡ በሴክተር ጉባኤ ላይ በተካሄደው ግምገማም ክልሎቹ በመካከላቸው ያለው የልማት ትብብር ከቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና አማራ ክልል በስተቀር በሌሎቹ መካከል ክፍተት ያለው በመሆኑ በቀጣይ ትብብራቸውን እንዲያጠናክሩ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ የቀሩት ክልሎችና እህትማማች ከተሞች መካከልም የልማት ትብብር ዕቅድ ተዘጋጅቶ የልምድ ልውውጥ ተሞክሮ ማግኘት እንዲችሉ በእህት ከተሞች እና ተባባሪ አካላት ድጋፍና ዕውቅና ለማስገኘት የማስተባበር ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

## VII. በአፈጻጸም ሂደት ያገጠሙ ችግሮችና እየተወሰዱ ያሉ የመፍትሔ እርምጃዎች፡-

ባለፉት ዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ሂደት የነበሩብንን ቁልፍ ማነቆዎች ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በዚህ ሂደትም መሻሻል የታየባቸው ማነቆዎች ያሉ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ የተቀረፉ ባለመሆናቸው በቀጣይ ጊዜያትም ከዚህ የበለጠ ሥራ መስራት የሚያስፈልግ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ በአፈጻጸም ሂደት የገጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶችና እየተወሰዱ ያሉ የመፍትሄ እርምጃዎች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 1. በእቅዱ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች፡-

ሀ) የሠራዊት ግንባታ ሥራችን በሚጠበቀው ደረጃ አለመሆኑ፣

ለ) በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሥራ ተቋራጮች፣ ባለሙያዎች፣ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ፣ በአዲስ ፈቃድ አሰጣጥ እና በፈቃድ እደሳት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የነበረውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መቀነስ የተቻለ ቢሆንም አሁንም ጠንካራ ትግል የሚጠይቅ መሆኑ፣

ሐ) ከመረጃ ልውውጥ አንጻር ሴክተሩ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ለውውጥ ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት እየተደረገ ቢሆንም አሁንም ድረስ ከፌዴራል እስከ ከተማ የጠራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት ላይ ክፍተት መኖሩ፣

መ) የድጋፍና ክትትል ሥራዎቻችንን ከውጤት ጋር በማስተሳሰር በኩል ያለው ክፍተት የሚፈለገው ደረጃ ያልተፈታ መሆኑ፣ እና

ሠ) በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ቀደም ሲል በክልሎችና በድሬዳዋ ግንባታቸው የተጀመሩ ቤቶችን በተቀመጠው የመንግስት አቅጣጫ መሠረት ሙሉ በሙሉ ለተጠቃሚዎች በማስተላለፍ ከዕዳ ነጻ ከመሆን አንጻር መጓተት መኖሩ በዕቅድ አፈጻጸማችን ወቅት የገጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

## 2. እየተወሰዱ ያሉ የመፍትሔ እርምጃዎችን በተመለከተ፡-

ሀ) የሠራዊት ግንባታ ሥራችንን ለማሳለጥ እንዲረዳ ራሱንየቻለ የከተማ ልማት ሠራዊት ግንባታ ማስፈጸሚያ ጋይድ ላይን ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፣

ለ) በሥራ ተቋራጮች፣ ባለሙያዎች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ዙሪያ የነበረውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መቀነስ የተቻለ ቢሆንም አሁንም ጠንካራ ትግል የሚጠይቅ መሆኑ፣ ለማክሰም በተዘጋጀው የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍቻ አጣዳፊ ዕቅድ መሠረት የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅድ በማስቀመጥ አደረጃጀቱንና አሰራሩን የማሻሻል ሥራ ከማከናወን ጎን ለጎን የምዝገባ ሥርዓቱን በአውቶሜሽን በተደገፈ ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓትለመፍጠር እየተሰራ ነው፣

ሐ) በክልሎች እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል በጋራ ካሉን መድረኮች በተጨማሪ የሚታየውን የመረጃ ልውውጥ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ይረዳ ዘንድ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓታችን በአውቶሜሽን የተደገፈ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፣

መ) ከክልሎች ጋር ያለውን የመደጋገፍ አግባብ ከማጠከር አንጻር በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በክልሎች መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር በተለይ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የሚደረገው ድጋፍ የተዘጋጀውን የልዩ ድጋፍ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ወደ መሬት የወረደ ዕገዛ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፣

ሠ) በክልሎችና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ያልተላለፉ ቀሪ ቤቶች የሚተላለፉበትን መንገድ ለማመቻቸት ሚ/ር መ/ቤቱ የጋራ ውይይት በማድረግ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

## 3. ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ሀ) በዘርፉ የተጀመረውን ለውጥ ለማስቀጠል የሚያስችል የከተማ ልማት ሠራዊት ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣

ለ) በሴክተሩ ለኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ተጋላጭ የሆኑ የስራ ዘርፎችን ከአደጋው ለመከላከልና በዚህ ረገድ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችሉ የአደረጃጀቱና የአሰራር ማሻሻያዎችን በፍጥነት አጠናቆ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ ሲስተም መዘርጋት ፣

ሐ) ከክልሎች ጋር ያለውን የመደጋገፍ አግባብ በተለይም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት ሰጥቶና ከውጤት ጋር በማስተሳሰር እንዲከናወን ማድረግና የተጀመረውን ልዩ ድጋፍ አጠናክሮ ማስቀጠል፣

መ) ቀደም ሲል በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም በክልሎችና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ያልተላለፉ ቀሪ ቤቶች ሙሉ በሙሉ እንዲተላለፉና ክልሎች ላይ ያለው ውዝፍ ዕዳ ተመላሽ እንዲሆን አማራጭ አቅጣጫዎችን በጋራ በማስቀመጥ ለተግባራዊነቱ ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

## VIII. ማጠቃለያ፡-

እንደአጠቃላይ የ2006 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸማችን ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ አንጻር የሚያበረታታ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን የቀረቡት ሪፖርቶች ያመላክታሉ፡፡ በተነጻጻሪ በለውጥ ስራዎች፣ በሥራ ዕድል ፈጠራና የኢንተርፕራይዞች ልማት፤ በከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት እና በመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ግንባታዎች የታዩ ሥራዎቻችን አበረታች መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ለመታገል በተወሰደው እርምጃ አበረታች ውጤት ማምጣት ተችሏል፡፡ የከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት እና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ሥራችን አፈጻጸም ከሌሎቹ ዘርፎች አፈጻጸም አንጻር መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በቀጣይ ይህን አፈጻጸም የበለጠ ከማጎልበት እና በእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተያዙ ግዙፍ ዒላማዎችን ለማሳካት የበለጠ ጥረት ይጠይቃል፡፡

የከተሞች መልካም አስተዳደር ገድ በሰው ኃይል ልማት እና  የመሠረተ ልማት ሥራዎች አፈጻጸም በተነጻጻሪ ወደኋላ የቀረ መሆኑን የተዘጋጀው የአፈጻጸም ሪፖርት ያሳያል፡፡ በጽደትና ውበት አኳያ እንዲሁ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና በአረንጓዴ ልማት በቀጣይ ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቁ መሆናቸው መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በኮንስትራክሽን ሴክተሩ በተለይም በሕንጻ አዋጅ አተገባበር ዙሪያ ተጨማሪ ትኩረት የሚጠይቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የእነዚህ ሥራዎች አፈጻጸም የከተማውን ህብረተሰብ የመልካም አስተዳደርና የልማቱ ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ለማድረግ በቀሪ ሦስት ወራት ከፍተኛ ትኩረት ሠጥተን ልንረባረብባቸው እንደሚገባ ግንዛቤ ተወስዶባቸዋል፡፡

# የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
## የ2006 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **I.** | **የቁልፍ ሥራዎች ግቦች/ የማስፈጸም አቅም (Learning and Growth) ዕይታ** | | | | | | |
| **1** | **በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የለውጥና የልማት ሠራዊት ግንባታ ሥራዎች** | | | | | | |
| 1 | **የለውጥ ሠራዊት ማፍራትና ማጎልበት** | **የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት እና በዘርፉ ከሚኖሩት ሠራተኞች 80% የከተማ የለውጥና የልማት ሠራዊት በማድረግ ለውጡን በትግል የሚመሩና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትንና ተግባራትን አምርረው የሚታገሉ 25% ተኪ አመራሮች ይፈጠራሉ፡፡** | | | | | |
| 1.1 | | በየደረጃው የንቅናቄ መድረኮችን በመፍጠር የከተማ የለውጥና የልማት ሠራዊት በመገንባት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በዘርፉ ከሚኖሩት ሰራተኞች 80% የለውጥና የልማት ሠራዊት እንዲሆኑ ማድረግ፣ | የለውጥና የልማት ሰራዊትን የተቀላቀለ የዘርፉ ሠራተኛ በመቶኛ | 70 | 79.3 | 113 | |
| 1.2 | | ለውጡን በትግል የሚመሩና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትንና ተግባራትን አምርረው የሚታገሉ 25% ተኪ አመራሮችን ማፍራት፣ ከሚፈጠረው ተኪ አመራር ውስጥ 25% ሴቶች እንዲሆኑ ማድረግ፣ | የተፈጠሩ ተኪ አመራር ብዛት በቁጥር | 43 | 50 | 50 | |
| | | | የተፈጠሩ ተኪ ሴት አመራር ብዛት በቁጥር | 10 | 0 | 0 | |
| 1.3 | | በሚ/ር መ/ቤቱ 56 አመራሮች የአመራርና ማነቆ አፈታት (Problem Solving) እና ለ100 ሠራተኞች የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል ስልጠና ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ እንዲሁም እንዲሰጥ ማድረግ፣ | ስልጠና ያገኙ አመራሮች ብዛት በቁጥር | 56 | 0 | 0.00 | |
| | | | የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶችን ስልጠና ያገኙ ሠራተኞች ብዛት በቁጥር | 140 | 90 | 64.28 | |
| 2 | **አደረጃጀት መዘርጋት፣ ማናበብና ማሻሻል** | **የለውጥ መሳሪያዎች በፌዴራልና በክልል 100% የተናበቡ በማድረግ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እና በማስፋፋት እንዲሁም የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ሥራዎችን በመስራት እና ምቹ የሥራ አካባቢ በመፍጠር በዘርፉ በየደረጃው በሚሰጡት አገልግሎቶች የተገልጋዮች እርካታ 90% እንዲደርስ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 2.1 | | ስትራቴጂክ እቅዱ (SPM)፣ የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ /BPR/ እና የውጤት ተኮር ስርዓት ግንባታ (BSC) በፌዴራል፣ በክልሎችና በከተሞች 100% ተናበውና ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ማድረግ፣ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 2.2 | | የለውጡን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል፣ግምገማና ግብረ-መልስ ማኑዋል ይዘጋጃል፣ | የተዘጋጀ ሰነድ ብዛት በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 2.3 | | በሚ/ር መ/ቤቱ በየደረጃው በሚሰጡት አገልግሎቶች የተገልጋዮች እርካታ 95% እንዲደርስ ማድረግ፣ | በመቶኛ | 86 | 80 | 93 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.0 | **የማስፈጸሚያ ሥርዓቶችን ማሻሻል** | **የለውጡን አፈጻጸም በየጊዜው በመከታተል፣ በመገምገምና ግብረ-መልስ በመስጠት የሥራ አፈጻጸም ውጤትና ግብረ-መልስ 100% በውጤት ተኮር የምዘና ስርዓት /BSC/ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በተቋሙ የልማትና የለውጥ ስራዎቻችንን ውጤታማነት የሚያፋጥን የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡** | | | | | |
| 3.1 | | በዘርፉ በዓመት 2 ጊዜ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ በማድረግ የለውጥ ሂደቱ ወደ ኋላ የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ማድረግ፣ | የተካሄደ የክትትል፣ ድጋፍ ግምገማና ግብረ መልስ ውጤት የሰነድ ብዛት | 1 | 0 | 0 | |
| 3.2 | | የ360 ዲግሪ ግምገማ በየደረጃው ቀጣይነት ባለው መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን እና ወቅታዊ የሆኑ ማነቆዎችን መለየትና መፍታት የሚያስችል በበጀት ዓመቱ 2 ጊዜ ግምገማ ማካሄድ፣ | በጊዜ | 2 | 2 | 100 | |
| 3.3 | | የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ /BPR/ እና የውጤት ተኮር ሥርዓት ግንባታ (BSC) አተገባበርና ውጤት በየደረጃው በየወሩ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣ | የተሰጠ ግብረ መልስ ሰነድ በቁጥር | 9 | 9 | 100 | |
| 3.4 | | የሥራ አፈጻጸም ውጤትና ግብረ-መልስ 100% በውጤት ተኮር የምዘና ስርዓት /BSC/ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ፣ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| **ማስታወሻ:-** የለውጥና የልማት ሠራዊት ግንባታን በተመለከተ በሚ/ር መ/ቤቱ ከሚገኙ 546 ሠራተኞች ውስጥ 433 የሚሆኑት በ69 የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት ውስጥ የታቀፉ በመሆናቸው የአፈጻጸም ስሌቱ የተቃኘው ከዚያ አንጻር መሆኑ መግለጽ እንወዳለን፡፡ | | | | | | | |
| 2 | **የዕቅድ ዝግጅት እና የፖሊሲና ፕሮግራም የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥራዎች** | | | | | | |
| 2.1 | **ግብ 23፡- ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት** | **በፌዴራል እና በክልሎች/በከተማ አስተዳደሮች መካከል በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተናበቡ የጋራ ዕቅዶችን በማዘጋጀትና የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ አፈጻፀሞችን በመገምገም ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡** | | | | | |
| 2.1.1 | | በየበጀት ዓመቱ በፌዴራል እና በክልሎች/በከተማ አስተዳደሮች መካከል የተናበቡ 11 ዓመታዊ የጋራ የዕቅድ የስምምነት ሰነዶችን (MOA) በማዘጋጀት መፈራረምና ተግባራዊ ማድረግ፣ | የተዘጋጀ ዓመታዊ ዕቅድ ሰነድ | 11 | 11 | 100 | |
| | | | የጋራ የዕቅድ ስምምነት ሰነድ (MOA) የተዘጋጀላቸው ከተሞች ብዛት | 11 | 11 | 100 | |
| 2.1.2 | | በፌዴራል በበጀት ዓመቱ ሁለት ጊዜ እና በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በዓመት አንድ ጊዜ በመስክ የሴክተር ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና በማካሄድ ግብረ-መልስ መስጠት፣ | የተዘጋጀ የፌደራል ሴክተር ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ሪፖርት ሠነድ ብዛት | 2 | 2 | 100 | |
| | | | የተዘጋጀ የክልል/ከተማ አስተዳደር አፈጻጸም ምዘና | 11 | 11 | 100 | |
| 2.1.3 | | በፌዴራል ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችን ያሳተፈ በዓመት ሁለት ጊዜ እና በየክልል/ከተማ አስተዳደር በዓመት ሁለት ጊዜ የሴክተር ጉባኤ መድረኮች በማካሄድ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ግብረ-መልስ መስጠት፣ | የተካሄደ የፌደራል የሴክተር ጉባኤ መድረክ ብዛት | 2 | 2 | 100 | |
| 2.1.4 | | በዕቅድ ዝግጅት እና በአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ያለውን ልዩነት (Gap) ለማጥበብ እንዲቻል በፌዴራል፣ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር የጋራ ፎረም በዓመት ሁለት ጊዜ ማካሄድ፡፡ | የተካሄደ የጋራ ፎረም ብዛት | 2 | 2 | 100 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዕቅድ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.2 | **ግብ 4፡- የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት፣ ልውውጥና ደህንነት ማሻሻል** | **በዘርፉ መሠረታዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለፕሮግራሞች ውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ ግምገማ የመረጃ ምንጭ የሚሆኑ 4 ጥናቶች ይካሄዳሉ፡፡** | | | | | |
| 2.2.1 | | የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማት ለኢትዮጲያ ኢኮኖሚ እድገት እያበረከተ ያለውን ሚና በሞዴል የታገዘ እንዲሆን ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በ2005 በጀት ዓመት የተጀመረው ጥናት እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ማጠናቀቅ፣ | የተካሄደው ጥናት የአፈጻጸም ደረጃ በመቶኛ | 100 | 80 | 80 | |
| 2.2.2 | | የኢትዮጵያ ከተሞች ዕድገት እና የከተማ-ነክ አገልግሎቶች ደረጃ ጥናት ማካሄድ፣ | የተካሄደው ጥናት የአፈጻጸም ደረጃ በመቶኛ | 40 | | | ለun-habitat-3 ለአውደ ጥናት የሚቀርብ ሪፖርት በሚል ተተክቷል፡፡ |
| 2.2.3 | | የከተሞች መሠረተ-ልማትና አገልግሎት አቅርቦትን እና ፍላጎትን የሚዳስስ አንድ ጥናት ማካሄድ፣ | የተካሄደው ጥናት የአፈጻጸም ደረጃ በመቶኛ | 93 | 60 | 64.52 | |
| 2.2.4 | | የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎች አቅርቦትና አጠቃቀምን ጥናት ማካሄድ፣ | የተካሄደው ጥናት የአፈጻጸም ደረጃ በመቶኛ | 78.7 | | | በCSA እንዲሰራ የተወሰነ በመሆኑ |
| 2.2.5 | | የዘርፉን የአምስት አመት የልማት ሥራ ለመገምገም የሚያስችል የአብስትራክት (2001-2005) ሠነድ በማጠናቀቅ እንዲሰራጭ ማድረግ፣ | የተካሄደው ጥናት የአፈጻጸም ደረጃ በመቶኛ | 81.25 | 92 | 113.23 | |
| 2.2.6 | | በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የስታቲስቲክስ ዩኒት እንዲቋቋም ድጋፍና ክትትልና ማድረግ፡፡ | የተካሄደው ጥናት የአፈጻጸም ደረጃ በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 3 | **የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ሥራዎች** | | | | | | |
| 1 | **ግብ 4፡- የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት፣ ልውውጥና ደህንነት ማሻሻል** | **በተቋሙና በዘርፉ ለሚኖር ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥና ፍሰት አስተማማኝ የመረጃ መረብ ኢንፍራስትራክቸር እንዲኖር ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 1.1 | | ለ4 ሎካል ኤሪያ ኔትወርክ ያልዘረጉ የክልል አቻ ቢሮዎች፣ ተጠሪ ተቋማትና ከተሞች እንዲዘረጉ ማድረግ፣ | ላን የዘረጉ ተቋማት ብዛት | 3 | 3 | 100 | |
| 1.2 | | ለ11 በወረዳኔት ውስጥ ያልገቡ ተጠሪ ተቋማት፣ ክልሎች፣ አቻ ቢሮዎችና ከተሞች እንዲገቡ ማድረግ፡፡ | ወረዳ ኔት አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ተቋማት ብዛት | 5 | 4 | 80 | |
| 2 | **ግብ 4፡- የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት፣ ልውውጥና ደህንነት ማሻሻል** | **የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን አፕሊኬሽንኖች ዳታቤዞች እንዲለሙና የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ምዘና አውቶሜት እንዲሆን ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 2.1 | | በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአቅርቦትና የግምጃ ቤት፣ የሰው ኃይል አስተዳደር እና የተቀናጀ የጠቅላላ አገልግሎት የመረጃ ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲለማ ማድረግ፣ | የለሙ የመረጃ ስርዓት ብዛት | 3 | 3 | 100 | |
| 2.2 | | ለ22 ሰልጣኞች በፌዴራልና ለ113 ሰልጣኞች በክልሎች እንዲሰለጥኑ በማድረግ በተሠራው ዌብሳይትና ፖርታል ፔጅ በየሩብ ዓመቱ መረጃን ወቅታዊ ማድረግ፣ | በፌደራል ስልጠና እንዲያደጉ የተደረጉ የሰልጣኞች ብዛት በቁጥር | 22 | 20 | 90.9 | |
| | | | በክልል የሰልጣኞች ብዛት | 80 | 44 | 55 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዕቅድ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በየሩብ ዓመቱ ወቅታዊ የተደረገ ድህረ ገጽ ብዛት በቁጥር | 3 | 3 | 100 | |
| 2.3 | | የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ /BPR/ እና የውጤት ተኮር ስርዓት ግንባታ (BSC) ትግበራ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በየወሩ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡ | በየወሩ የተደረገ የክትትል ብዛት በቁጥር | 9 | 3 | 33.3 | |
| II. | የዋና ዋና ተልዕኮ ግቦች ዕይታ/Internal Process/ | | | | | | |
| 1 | የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ሥራዎች | | | | | | |
| | የክልሎች የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራ | | | | | | |
| 1.1 | ግብ 12፡-የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጎልበት | **በ2006 የዕቅድ ዘመን የዘርፉን አስፈጻሚ አካላትና የክልሎችን የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ ለ5,915 አመራር አካላትና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት እና ለ563,723 ነባር አንቀሳቃሾችና ወደ ሥራ ለሚገቡ አዲስ 1,799,539 አንቀሳቃሾች በድምሩ ለ1,810,244 የአመለካከትና ክህሎት ሥልጠና ይሰጣል፡፡** | | | | | |
| 1.1.1. | | የዘርፉ አመራሮችን፣ የልማት አስፈጻሚ አካላትን እና አንቀሳቃሾችን አቅም በመገንባት ጠንካራ መሰረት ያለው የልማት ሠራዊት ለመገንባት 867 ኮማንድ ፖስት ማደራጀት፣ | የተደራጀ ኮማንድ ፖስት ብዛት | 487 | 765 | 157 | |
| 1.1.2 | | የዘርፉን ልማት የሚያፋጥኑ በፌዴራልና በክልል 37 ዓይነት ጥናቶች፣ የድጋፍ ማዕቀፎች፣ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች እና ማንዋሎችን ማዘጋጀት፣ | የተዘጋጁ እና የተሰራጩ መመሪያዎች ብዛት በቁጥር | 37 | 34 | 92 | |
| | | | የተዘጋጁና የተሰራጩ ማንዋሎች ብዛት በቁጥር | 23 | 16 | 70 | |
| 1.1.3 | | ለ1,397 ከፍተኛ እና ለ3,995 መካከለኛ አመራሮች በድምሩ 5,392 በዘርፉ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ የአመለካካትና የክህሎት የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት፣ | የአሰልጣኞች ሥልጠና ላይ ተሳታፊ የሆኑ ከፍተኛ አመራሮች ብዛት በቁጥር | 1397 | 1397 | 100 | |
| | | | የአሰልጣኞች ሥልጠና ላይ ተሳታፊ የሆኑ መካከለኛ አመራሮች ብዛት በቁጥር | 3995 | 2224 | 55 | |
| 1.1.4 | | በየደረጃው ለሚገኙ ለ30,000 የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት ዝቅተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች፣ ለ60,826 ሥራ ፈላጊዎች በተለይ የዩኒቨርስቲና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን እንዲሁም ለ563,723 አመራሮችና አንቀሳቃሾች ክፍተትን መሰረት ያደረገ የአመለካከትና የክህሎት ሥልጠና መስጠት፣ | በስልጠናው ተሳታፊ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት ዝቅተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች ብዛት በቁጥር | 30000 | 63758 | 212 | |
| | | | በስልጠናው ተሳታፊ የሆኑ ሥራ ፈላጊዎች ብዛት በቁጥር | 60827 | 145429 | 239 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዓላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በስልጠናው ተሳታፊ የሆኑ አመራሮችና ባለሙያዎች ብዛት በቁጥር | 563723 | 1160336 | 206 | |
| **1.2** | **ግብ 29፡- የሕዝብ እርካታና አጋርነትን ማጎልበት** | **ለ8,502 አመራር አካላትና ለዘርፉ ባለሙያዎች እና ለ630,342 ህብረተሰብ እና አንቀሳቃሾች በዘርፉ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያዳብሩና ወደ ተግባር መግባት የሚያስችላቸውን መድረኮችን ፕሮግራሞች በማዘጋጀት የፓናል ውይይቶች፣ ወርክሾፖች፣ ሴሚናሮች፣ ሲምፖዚየሞች ይካሄዳሉ፡፡** | | | | | |
| 1.2.1 | | በዘርፉ ልማት 8,502 አመራሮችና ባለሙዎች የሚታዩትን የአመለካከት ክፍተቶች ለመሙላት የተለያዩ መድረኮችን በማመቻቸት ግንዛቤ መፍጠር፣ | ግንዛቤ ያገኙ ተሳታፊ አመራሮችና ባለሙያዎች ብዛት በቁጥር | 6375 | 13943 | 219 | |
| 1.2.2 | | ለ630,342 ህብረተሰብ እና አንቀሳቃሽ በገጽ ለገጽ የግንዛቤ መስጫ መድረኮች በማዘጋጀት የዘርፉን ልማት መልእክት ማስተላለፍ፣ | መልእክት የተላለፈላቸዉ አንቀሳቃሾችና የህ/ብ ክፍሎች ብዛት በቁጥር | 472754 | 565645 | 120 | |
| | **የኢንተርፕራይዞች ሽግግር፣ የተሻለ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ሥራ** | | | | | | |
| **1.3** | **ግብ 23፡- ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት** | **በበጀት ዓመቱ 2 በመቶ ኢንተርፕራይዞችን ወደ መካከለኛ እና 101,929 ኢንተርፕራዩዞች ወደ ተለያዩ እድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 1.3.1 | | 101,929 ኢንተርፕራዩዞች ወደ ተለያዩ እድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ማድረግ፣ ከዚህ ውስጥ 390 (2 በመቶ) ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ደረጃ እንዲያድጉ ማድረግ፣ | ከጥቃቅን ጀማሪ ወደ ታዳጊ ደረጃ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዝ ብዛት በቁጥር | 52518 | 23325 | 44 | |
| 1.3.2 | | | ከጥቃቅን ታዳጊ ወደ መብቃት ደረጃ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዝ ብዛት በቁጥር | 6943.21 | 7895 | 114 | |
| | | | ከበቃ ጥቃቅን ወደ አነስኛ ጀማሪ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዝ ብዛት በቁጥር | 1372 | 3528 | 257 | |
| | | | ከጀማሪ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ ታዳጊ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዝ ብዛት በቁጥር | 11082 | 2516 | 23 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከታዳጊ አነስተኛ ኢንትፕራዞች ወደ የበቁ አነስተኛ ደረጃ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዝ ብዛት በቁጥር | 1719 | 1069 | 62 | |
| 1.3.4 | | በሃገር አቀፍ አንድ ዓመታዊ የምርጥ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት ኤግዚቢሽን በማካሄድ በትኩረት መስኮች የላቀ ስኬት ያስመዘገቡት 127 ኢንተርፕራይዞች እዉቅና እንዲሰጣቸው ማድረግ፣ | እዉቅና የተሰጣቸዉ የኢንተርፕራይዝ ብዛት በቁጥር | 127 | 277 | 218 | |
| | የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራ | | | | | | |
| **1.5** | **ግብ 27፡- የሥራ ዕድልን ማስፋት** | **በዘርፉ የ5 ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በ2006 በጀት ዓመት በመደበኛ ለ799,539 ሥራ ፈላጊ ዜጎችና በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች አንድ ሚሊዮን በድምሩ 1,799,539 የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡** | | | | | |
| 1.5.1 | | በመደበኛ ሁኔታ የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ 50,321 ነባሮችን በማጠናከር ለ211,937 አዲስ በድምሩ 262,258 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ | የተፈጠረ የስራ እድል ብዛት በቁጥር | 222,919.30 | 180413 | 81 | |
| 1.5.2 | | በመደበኛ ሁኔታ የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በኮንስትራክሽን ዘርፍ 51,217 ነባሮችን በማጠናከር ለ154,318 አዲስ በድምሩ 205,535 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ | የተፈጠረ የስራ እድል ብዛት በቁጥር | 174704.75 | 297425 | 170 | |
| 1.5.3 | | በመደበኛ ሁኔታ የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በአገልግሎት ዘርፍ 40,754 ነባሮችን በማጠናከር ለ113,789 አዲስ በድምሩ 154,543 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ | የተፈጠረ የስራ እድል ብዛት በቁጥር | 131360 | 224725 | 192 | |
| 1.5.4 | | በመደበኛ ሁኔታ የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በከተማ ግብርና ዘርፍ 21,284 ነባሮችን በማጠናከር ለ85,205 አዲስ በድምሩ 106,489 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ | የተፈጠረ የስራ እድል ብዛት በቁጥር | 90514 | 123907 | 167 | |
| 1.5.5 | | በመደበኛ ሁኔታ የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በንግድ ዘርፍ 14,714 ነባሮችን በማጠናከር ለ56,000 አዲስ በድምሩ 70,714 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ | የተፈጠረ የስራ እድል ብዛት በቁጥር | 60108 | 137336 | 228 | |
| 1.5.6 | | በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ዙሪያ ማለትም፣ በ10 ዩኒቨርሲቲዎች፣ በመገንባት ላይ ባሉ 2 የስኳር ፋብሪካዎችና በተጨማሪ 7 የስኳር ፋብሪካዎች፣ በመንገድ ልማት፣ በባቡር ኔትወርክ፣ በኃይል ማመንጫዎች በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በጊዜያዊነትና በቋሚነት በአማካይ ለአንድ ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፡፡ | የተፈጠረ የስራ እድል ብዛት በቁጥር | 850000 | 750117 | 88.25 | |
| | የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ሥራ | | | | | | |
| **1.6** | **ግብ 23፡- ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት** | **የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥን ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን በማድረግ፣ እንዲሁም ነባር 452 ማዕከላትን በማጠናከር እና አዲስ 167 ማዕከላትን በማቋቋም የአገልግሎት አቅርቦት ሥርዓቱ ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግ ለ2.6 ሚሊዮን ሥራ ፈላጊዎች ድጋፎች እንዲመቻች ይደረጋል፡፡** | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዕቅድ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.6.1 | | የተለያዩ 452 ነባር የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ያለባቸውን የቁሳቁስና የሰው ሃይል በማሟላትና በማብቃት አገልግሎት የመስጠት አቅማቸው እንዲጠናከር በማድረግ በ107 ሞዴል ማዕከላት ግንባር ቀደም ባለሙያዎች ማበረታቻ መስጠት፣ | የተጠናከሩ ነባር የአንድ ማእከላት ብዛት በቁጥር | 316 | 467 | 148 | |
| 1.6.2 | | 167 አዳዲስ አንድ ማዕከላት በመገንባት የዘርፉ ልማት አገልግሎት ተደራሽነት እንዲሰፋ ማድረግ፣ | የተቋቋሙ አዲስ ማእከላት ብዛት በቁጥር | 100 | 148 | 148 | |
| 1.6.3 | | ለ1,799,539 ሥራ ፈላጊዎች የአንድ ማእከል አገልግሎቶች ተጠቃሚ በማድረግ ለሥራ እድል ፈጠራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ | በአንድ ማእከል አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሥራ ፈላጊዎች ብዛት በቁጥር | 1079724 | 1006954 | 93 | |
| 1.6.4 | | ለ103,640 ነባርና ለአዲስ ኢንተርፕራይዞች የእድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ የአንድ ማእከል አገልግሎት ድጋፎች እንዲመቻቹ ማድረግ፣ | አገልግሎት ያገኙ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 77730 | 294561 | 379 | |
| 1.6.5 | | ለ9,902 በትኩረት ዘርፎች የተካተቱ ኢ-መደበኛ ንግድ ላይ የተሰማሩ ዜጎች በመለየት የዘርፉ ልማት መንግስታዊ ድጋፍ ተጠቃሚ ለማድረግ በአንድ ማዕከል አገልግሎቶች በ190 ኢንተርፕራይዞች በማደራጀት ወደ መደበኛ እንዲዛወሩ ማድረግ:: | ወደ መደበኛ ንግድ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 500 | 2367 | 473 | |
| | **የቁጠባ ባህል ማዳበርና የፋይናንስ አቅርቦት ድጋፍ ሥራ** | | | | | | |
| **1.7** | **ግብ 7፡- የቁጠባ ባህል፣ የፋይናንስ አቅርቦትንና ኢንቬስትመንትን ማስፋፋት** | **በበጀት ዓመቱ በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ወደ ሥራ ለሚገቡ አዲስና ነባር አንቀሳቃሾች ብር 5.055 ቢሊዮን እንዲሁም በዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች ብር 1,656,500 እንዲቆጥቡ በማበረታታ 2,307,963 አንቀሳቃሾች ብር 6,740,655,534 ብድር በማመቻቸት ቀደም ሲል የተሰጠም ሆነ አዲስ የሚሰጥ ብድር 100% እንዲመለስ ይደረጋል::** | | | | | |
| 1.7.1 | | በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ከሚገኙ ነባርና አዲስ አንቀሳቃሾች ብር 5.055 ቢሊዮን እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የዩኒቨርስቲና የቴክኒክና ሙያና ትምህርት ሥልጠና ተቋማት ተማሪዎች ገና ሲገቡ በሚሰጠው የግቢ ቆይታ ኦረንቴሽን ተከታታይ የዘርፉ ልማትና የቁጠባ ባህል ማዳበሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ቤተሰብ ከሚልክላቸው ገንዘብ ብር1,656,500 እንዲቆጥቡ ድጋፍ ማድረግ፣ | በዘርፉ አንቀሳቃሾች የተቆጠበ የብር መጠን በቢሊዮን ብር | 30.84 | 35.99 | 117 | |
| | | | ቁጠባ የጀመሩ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር | 10733 | 2839 | 26 | |
| | | | የተማሪዎች የቁጠባ መጠን በብር | 1490850 | 2050033 | 137 | |
| 1.7.2 | | በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ወደ ሥራ ለሚገቡ 2,307,963 አንቀሳቃሾች ብር 6.741 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት ማመቻቸት፣ | የብድር ተጠቃሚ የሆኑ አንቀሳቃሾች ብዛት በቁጥር | 1730973 | 439246 | 25 | |
| | | | የተመቻቸ ብድር መጠን በብር | 3,377,002,998 | 2,355,336,577 | 70 | |
| 1.7.3 | | ከተሰራጨው እና በበጀት ዓመት ሊመለስ የሚገባው ብድር ብር 4.39 ቢሊዮን እና ቀደም ብሎ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ብድር ብር 173.9 ሚሊዮን እንዲሰበሰብ ማድረግ፣ | የተሰበሰበ የብድር መጠን ብዛት በቢሊዮን በብር | 2.24 | 1.54 | 69 | |
| | | | ተመላሽ የሆነ የውዝፍ ብድር መጠን ብዛት ሚሊዮን በብር | 139.1 | 65.57 | 47.17 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.7.4 | | በፌዴራል በኩል አስፈላጊዉ ችግር ፈቺ የመሣሪያዎች ሊዝ የአሰራር መመሪያ በማፅደቅ እና ሥርዓቱን በመዘርጋት 8,031 ኢንተርፕራይዞች የብድሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡ | የፀደቀ የመሳሪያ መመሪያ ብዛት በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | | | የመሳሪያ ሊዝ ሥርዓት የተዘረጋላቸዉ በኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 5019.38 | 2639 | 52 | |
| | | | የመሳሪያ ሊዝ ሥርዓት የተዘረጋላቸዉ አንቀሳቃሾች ብዛት በቁጥር | 17820 | 13495 | 76 | |
| | **የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሥራ** | | | | | | |
| **1.8** | **ግብ 12፡-የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጎልበት** | **ለ15,860,636 ነባርና አዲስ የኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራ አመራርና የቴክኒክ ስልጠና እና ለ6,505,481 የመረጃና ምክር አገልግሎት ድጋፍ በመስጠት እና ለ128,096 ኢንተርፕራዞች የBDS አገልግሎት በመስጠት ተወዳዳሪነታቸው ዘላቂነት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 1.8.1 | | ለ15,860,636 ነባርና አዲስ የኢንተርፕራይዝ አባላት የንግድ ስራ አመራርና ለ6,505,481 ነባርና አዲስ የኢንተርፕራይዝ አባላት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንዲያገኙ ማድረግ፣ እንዲሁም 128,096 ኢንተርፕራዞች የBDS አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ | የንግድ ስራ አመራር ስልጠና ያገኙ አባላት ብዛት በቁጥር | 1090710 | 575108 | 53 | |
| | | | የቴክኒክ ስልጠና ያገኙ አባላት ብዛት በቁጥር | 540239 | 730182 | 135 | |
| | | | የBDS ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 89668 | 94493 | 105 | |
| 1.8.2 | | ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድባቸው 645 ፕሮቶታይፖችን ማዘጋጀት፣ | የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድባቸው ፕሮቶታይፖች ብዛት በዓይነት | 430 | 771 | 179 | |
| 1.8.3 | | በየክልሉ ትኩረት በተሠጣቸው የሥራ መስኮች 806 የተሻሻሉ የመሣሪያ ዓይነቶች ተመርተው ማሰራጨት፣ | ተመርተው የተሰራጩ መሳሪያዎች ብዛት በዓይነት | 537 | 553 | 103 | |
| 1.8.4 | | ለ2,259,394 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች አንቀሳቃሾች የመረጃና ምክር አገልግሎት መስጠት፣ | የመረጃና የምክር አገልግሎት ያገኙ በአንቀሳቃሽ ብዛት በቁጥር | 1055577 | 699981 | 66 | |
| 1.8.5 | | ለ8,852 ሞዴል ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ትግበራ ተጠቃሚ በማድረግ ተወዳዳሪነታቸው ዘላቂ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ ለ650 ፈጻሚዎች የካይዘን ሥራ አመራር የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣ | የካይዘን ትግበራ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 6639 | 6639 | 100 | |
| 1.8.6 | | | የካይዘን ሥራ አመራር የአሰልጣኞች ስልጠና ያገኙ ፈጻሚዎች ብዛት | 650 | 403 | 62 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዕቅድ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.8.7 | | በክልል ደረጃ ካሉ የጥ/አ/ኢ/ል/ኤጀንሲዎች ውስጥ 60% በሚሆኑት የካይዘን የሥራ አመራር ሥርዓት እንዲተገበር ማድረግ፣ | የካይዘን ስራ አመራር የዘረጉ የክልል ጥ/አ/ኢ/ል/ኤጀንሲዎች ብዛት በመቶኛ | 55 | 5 | 9.06 | |
| 1.8.8 | | በአንቀሳቃሾች ላይ የሚታዩ የምርትና ምርታማነት ክፍተቶችን ለመፍታት ለ290,515 አንቀሳቃሾች እና ለ42,330 የአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ሥራ አመራር ሥልጠና መስጠት፣ | የካይዘን ሥራ አመራር አመለካከት ሥልጠና ያገኙ የኢንቀሳቃሾች ብዛት በቁጥር | 217886 | 155632 | 71 | |
| | | | የካይዘን ሥራ አመራር አመለካከት ሥልጠና ያገኙ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 31747 | 76808 | 242 | |
| 1.8.9 | | የሞዴል ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ትግበራ ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ቢያንስ ለ5,897 እጩ ሞዴል ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ሥራ አመራር እንዲተገብሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡ | የካይዘን ሥራ አመራር የተገበሩ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 5897 | 552 | 9.36 | |
| | ***የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ድጋፍ ሥራ*** | | | | | | |
| **1.9** | **ግብ 6፡- የምርት፣ ምርታማነትና የገበያ ልማትን ማሳደግ** | **በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች ለማምረቻና ለመሸጫ አገልግሎት የሚውል 6,288 ሄ/ር ቦታ በማዘጋጀት 10,332 ሼዶች እና 390 ህንጻዎች እንዲገነቡ በማድረግ በበጀት ዓመቱ 982,211 አንቀሳቃሾች ወደ ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ሴቶች 50 በመቶ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 1.9.1 | | በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ወደ ሥራ ለሚገቡ 982,211 አንቀሳቃሾች 6,288 ሄ/ር የለማ መሬት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ በማድረግ 10,332 ሼዶች እና 390 ሕንፃዎች እንዲገነቡ ማድረግ፣ ሴቶች 50 በመቶ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ | ወደ ስራ በሚገቡ አንቀሳቃሾች ብዛት በቁጥር | 589327 | 235373 | 40 | |
| | | | የተዘጋጀ መሬት መጠን በሄ/ር | 3518 | 1446 | 41 | |
| | | | የተገነቡ ሼዶች ብዛት በቁጥር | 6449 | 4685 | 73 | |
| | | | የተገነቡ ህንጻዎች ብዛት በቁጥር | 224 | 275 | 123 | |
| 1.9.2 | | ለሚገነቡት የማምረቻና የመሸጫ ክላስተር ማዕከላትን መሰረተ-ልማት 100 ፐርሰንት እንዲሟላላቸው ማድረግ፣ | መሰረተ ልማት የተሟላላቸዉ ክላስተሮች በመቶኛ | 59 | 45 | 76 | |
| | ***የገበያ ልማት፣ የግብይት ድጋፍ ሥራ*** | | | | | | |
| **1.10** | **ግብ 6፡- የምርት፣ ምርታማነትና የገበያ ልማትን ማሳደግ** | **የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽኖችንና ምርክሾች በማዘጋጀት በ250,000 ኢንተርፕራይዞች ለተደራጁ 1,906,542 አንቀሳቃሾች የብር 9.139 ቢሊዮን ሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር እንዲሁም ለ10,050 ኢንተርፕራይዞች 400 ሚሊዮን ብር የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ በገበያ ትስስሩ 50 በመቶ ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡** | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዕቅድ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.10.1 | | በ250,000 ኢንተርፕራይዞች ለተደራጁ ለ1,906,542 አንቀሳቃሾች በሀገር ውስጥ የብር 9,138,566,610 እና በ10,050 ኢንተርፕራይዞች ለተደራጁ ለ50,100 አንቀሳቃሾች ብር400 ሚሊዮን የውጭ አገር የገበያ ዕድል መፍጠር፣ | የአገር ዉስጥ የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸዉ አንቀሳቃሽ ብዛት በቁጥር | 1448.97 | 1081.11 | 75 | |
| | | | የአገር ዉስጥ የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸዉ ኢነተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 190,000 | 216,222 | 114 | |
| | | | የተፈጠረ የሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር መጠን በቢሊዮን ብር | 7.76 | 6.74 | 97 | |
| | | | የውጭ አገር የገበያ እድል የተፈጠረላቸው ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | 7650 | 2475 | 32 | |
| | | | የዉጭ አገር የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸዉ አንቀሳቃሽ ብዛት በቁጥር | 38075 | 12375 | 32 | |
| | | | በዉጭ አገር የገበያ የተፈጠረ ትስስር በሚሊዮን ብር | 304 | 263.86 | 87 | |
| 1.10.2 | | ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በተዘጋጀው የዌብ ፖርታል ለ39 የሸማ አምራች ድርጅቶች የኢንተርኔት (online) ሽያጭ እንዲያካሂዱ ድጋፍ ማድረግ፣ | በኢንተርኔት ሽያጭ እንዲያካሂዱ የተደረጉ ኢንተርፕራይዝ ብዛት በቁጥር | 26 | 15 | 58 | |
| 1.10.3 | | በኤክስፖርት ለተሰማሩ እና አምራች ድርጅቶች ስለዓለም አቀፍ ግብይት 4 የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፕ ማዘጋጀት፣ | የተካሄዱ ግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፕ በመድረክ ብዛት በቁጥር | 3 | | | ለማካሄድ ዝክረ ነገር ተዘጋጅቶ መረጃ የማሰባበስ ስራ በመሰራት ላይ ነው |
| 1.10.4 | | ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሳተፉበትና ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ተቋማት ተሞክሮ ሊያገኙ የሚችሉባቸው 6 ሃገራዊና ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽኖች ማዘጋጀት፣ | የተካሄዱ ሀገር ዉስጥ እና ዓለም አቀፍ የኤግዚቢሽን ብዛት በቁጥር | 4 | 3 | 75 | |
| 1.10.5 | | ነባር ኤክስፖርት አድራጊ ድርጅቶችና ከድርጅቶቹ ጋር ተሳስረው ለሚሰሩ አምራች ድርጅቶች የጥሬ ዕቃ ችግሮቻቸውን ለመፍታት 15 የጋራ ፎረም መድረኮች ማካሄድ፣ | የተካሄዱ የጋራ ፎረም መድረክ ብዛት በቁጥር | 11 | | | የጋራ ፎረም ለማካሄድ ዝክረ ነገር ተዘጋጅቶ ለፎረም የሚያስፈልጉ |
| | | የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ 10 የምርት ዓይነቶች የእሴት ሰንሰለት ሰነዶች እና የተጠኑ 20 የምርት ዓይነቶችን ማሰራጨትና ለተግባራዊነቱም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡ | ተግባራዊ የሆኑ ነባር የእሴት ሰንሰለት ጥናቶች በሰነድ ቁጥር | 20 | 16 | 80 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.10.6 | | | አዲስ የተጠኑና ተግባራዊ የሆኑ የእሴት ሰንሰለት ብዛት በሰነድ ቁጥር | 8 | | | የሚደረግባቸው ምርቶች የመለየት ስራ ተሰርቷል። ነገር ግን ጥናቱ አልተጀመረም |
| 2 | **የከተሞች መልካም አስተዳርና አቅም ግንባታ ሥራዎች** | | | | | | |
| | **የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሴክተር የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍቻ ሥራ** | | | | | | |
| 1 | **ግብ 29፡- የሕዝብ እርካታና አጋርነትን ማጎልበት** | **በከተሞች ተልዕኮውን በብቃት መፈጸም የሚችል የከተማ ልማት ዘርፍ የልማት ሠራዊት በመገንባት የሚሰጡ አገልግሎቶችን በማሻሻል የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እንዲቀረፍ ይደረጋል።** | | | | | |
| 1.1 | | በከተሞች የመልካም አስተዳደር ችግሮች የሚፈታበት አጣዳፊነት ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | የተዘጋጀ የዕቅድ ሰነድ ብዛት በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| 1.2 | | በዘርፉ የለውጥ ሠራዊት ግንባታ የተናበበ አደረጃጀት እና ወጥ ሥርዓት መዘርጋት፣ | ተግባራዊ የሆነ የለውጥ ሠራዊት ግንባታ ሥርዓት በመቶኛ | 1 | 1 | 100 | በረቂቅ ደረጃ ላይ የሚገኝ |
| 1.3 | | የመንግስት እና የህዝብ ክንፉ በመልካም አስተዳደር ዕቅድ፣ በልማትና የመልካም አስተዳደር አጀንዳዎች እና በለውጥ ሠራዊት ግንባታ ዓላማ እና ፋይዳ ላይ በቀጣይነት ግንዛቤ እንዲጨብጥ በማድረግ ልማታዊ አመለካከቱን ማዳበር፣ | ግንዛቤ የጨበጠ የመንግስትና የህዝብ ክንፍ በመቶኛ | 1 | 1 | 100 | |
| 1.4 | | በከተማ ልማት ዘርፍ በህዝብና በመንግስት ክንፍ መካከል ጠንካራ ጥምረት በመፍጠር በከተሞች የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እንዲሻሻሉ ማድረግ፣ | በመንግስት ክንፉና በህዝብ ክንፉ ጥምረት የተከናወኑ የመልካም አስተዳደር አጀንዳዎች በቁጥር | 3 | 6 | | በጥ/አ/ኢና በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በመኖሪያ ቤቶች (መሬትና --- አቅርቦት)፣ መሠረተ ልማት አቅቦት፣ ማዘጋጃ ቤታዊ ተደራሽነት፣ አረንጓደ ልማጽና ፅዳትና ውበት እና ኮንስትራክሽንና ንግድ ኢንዱስትሪ |
| 1.5 | | የዘርፉ ቢሮክራሲ ግልጸኛነትና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ለማድረግ ያልተማከለ አስተዳደር ሥርዓትን ማጠናከር፣ | ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ወርደው መሠጠት የጀመሩ አገልግሎቶች በመቶኛ | 60 | 37.5 | 62.5 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.6 | | ልማታዊ ባለሀብቱን የሚደግፍና የሚያበረታታ አመለካከትና አሰራር ማዳበር፣ | በጥራትና በብቃት ለልማታዊ ባለሀብቱ የተሰጠ አገልግሎት በመቶኛ | 60 | 0 | 0 | |
| 1.7 | | በዘርፉ በኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር ላይ ቀጣይና የአስተሳሰብና የተግባር ትግል ማካሄድ፣ | ቀጣይነት ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት ለማድረግ የተተገበረ የአሰራር ሥርዓት በመቶኛ | 60 | 0 | 0 | |
| 1.8 | | በከተማ ልማት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለሚነሱ የተለያዩ ቅሬታዎች መፍትሔ የሚሰጥበት እንዲሁም ለዜጎች የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ፈጣን መልስ ለመስጠት የሚስችል ሥርዓት መዘርጋት፣ | በፌደራል፣ በክልልና ከተሞች የተሰባሰቡና የተፈቱ ቅሬታዎች በመቶኛ | 60 | 0 | 0 | |
| | **የከተሞችና የክልሎች የሰው ኃይል ልማትና ስታንዳርዳይዜሽን ሥራ** | | | | | | |
| **2** | **ግብ 12፡-የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጎልበት** | **ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቁ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ለማቅረብ በ12 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የሙያ መስኮች ላይ 6 የማስተማሪያ ሰነዶች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር አንድ የትብብር ሰነድ አዘጋጅቶ ስልጠናዎችን በመስጠት የዘርፉ የሰው ኃይል ልማት እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 2.1 | | በሚዘጋጁና በተዘጋጁ የሙያ ደረጃዎች ላይ ግንዛቤ ለሚሰጡ 100 የሴክተሩ አመራሮች ባለሙያዎች እና የባለድርሻ አካላት የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣ | የአሰልጣኞችስልጠና የወሰዱ አመራሮችና ባለሙዎች ብዛት | 100 | 100 | 100 | |
| 2.2 | | ለአዳዲስ 4 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ሙያዎች 20 የብቃት አሀዶች (የሙያ ስታንዳርዶች)፣ 20 የመመዘኛ መስፈርቶች እና ለ12ቱ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች የሙያ መስኮች ላይ 6 የማስተማሪያ ማኑዋል ማዘጋጀት፣ | የተዘጋጁ የብቃት አሀዶች ብዛት | 20 | 25 | 125 | |
| | | | የተዘጋጁ የመመዘኛ መስፈርቶች ብዛት | 20 | 0 | 0 | |
| | | | የተዘጋጀ የመማሪያ ሰነድ ዓይነት በቁጥር | 400 | 300 | 75 | |
| 2.3 | | ኮዲፋይድ በሆኑ 12ቱ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የሙያ መስኮች 84 መሪ መዛኞች፣ 80 የትብብር ስልጠና የሚሰጡ መምህራን እና 34 የምዘና ጣቢያዎች እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ | የሰለጠኑ መሪ መዛኞች ብዛት በቁጥር | 84 | 7 | 83 | |
| | | | የተዘጋጁ የምዘና ጣቢያዎች ብዛት በቁጥር | 34 | 57 | 167.6 | |
| | | | የተዘጋጁ የትብብር ስልጠና ሰጪ መምህራን | 80 | 7 | 8.75 | |
| 2.4 | | ከትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲና ከብቃት ምዘና ማዕከላት (ከባለድርሻ አካላት) ጋር አንድ የትብብር ሰነድ በማዘጋጀትና በየሩብ ዓመቱ የትብብርና ትስስር ግንኙነት በመፍጠር የዘርፉ የሰው ኃይል ልማት ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፡፡ | የተዘጋጀ የትስስር ሰነድ ብዛት በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | | | በየሩብ ዓመቱ ከባለ ድርሻ ካላት ጋር የተፈጠረ ግንኙነት ብዛት | 3 | 3 | 100 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **3** | **ግብ 12፡-የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጎልበት** | **በከተማ ልማት ነክ ሙያዎች 10 የሰው ኃይል ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ በዘርፉ አዲስ ለሚሰማሩ እና በሥራ ላይ ያሉ አመራሮችና ፈጻሚዎችን ለ10,000 በአጭርና የመካከለኛና ለ1,047 የረዥም ስልጠና ፕሮግራም ሥልጠና በመስጠትና ምዘና በማካሄድ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ቀልጣፋና ጥራት ያለው 12 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 3.1 | | የሥራ ላይ የትምህርትና ስልጠና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በተዘጋጁ የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂዎችና ማንዋሎች ላይ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎች ለ200 (50% ሴቶች) አመራሮችና ባለሙያዎች መስጠት፣ | የተካሔደ የሰው ኃይል ዳሰሳ ጥናት ሰነድ ብዛት | 1 | 1 | 100 | |
| | | | ስልጠና የወሰዱ ሠልጣኞች በቁጥር | 200 | 0 | 0 | |
| 3.2 | | ኮዲፋይድ በሆኑ 12 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የሞያ መስኮች በዘርፉ ውስጥ ተሰማርቶ የሚገኝ 10,000 (50% ሴቶች) አመራሮችና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ በማድረግ የዘርፉ የሰው ኃይል ብቃት ማረጋገጥ፣ | የብቃት ምዘና ላይ ግንዛቤ የፈጠሩ አመራሮችና ባለሙያዎች ብዛት | 7500 | 8299 | 110 | በክልሎች ጭምር የተከናወነ |
| | | | የተመዘኑ አመራሮችና ባለሙያዎች ብዛት | 5000 | 7 | 0.14 | |
| 3.3 | | 12 የሰው ኃይል ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከሌቭል አንድ እስከ አምስት ለ10,000 (50% ሴቶች) ሰልጣኞች ከቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ (ከባለድርሻ አካላት) ጋር በመተባበር እዲሰለጥኑ በየወሩ (በዓመት 12 ጊዜ) ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣ | የተደረገ የሰው ኃይል ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት ሰነድ በቁጥር | 12 | 12 | 100 | |
| | | | ለቴ/ሙ/ የተላለፉ ሰልጣኞች ብዛት በቁጥር | 10000 | 421 | 4.21 | |
| 3.4 | | በተለያዩ የከተማ ልማት ሙያዎች ለ2,000 (30% ሴቶች) ሰልጣኞች የድህረ ምረቃ ስልጠና እንዲሁም ለ17 ሰልጣኞች PhD ደረጃ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣ | የድህረ ምረቃ ሰልጣኞች ብዛት | 2000 | 742 | 37.1 | |
| 3.5 | | አንድ የዳሰሳ ጥናት በማዘጋጀት በተለያዩ የከተማ ልማት ሙያዎች በ5 የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በ12 ፕሮግራሞች ስልጠና የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ | የተዘጋጁ የስልጠና ፕሮግራሞች ብዛት በቁጥር | 12 | 0 | 0 | |
| | **የሕዝብ ተሳትፎና ያልተማከል አስተዳደር ማሻሻያና ማጠናከሪያ ሥራ** | | | | | | |
| **4** | **ግብ 28፡- የሕዝብ ተጠቃሚነትን ማጎልበት** | **ቀጣይነት ያለው የከተሞች ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የህዝብ ተሳትፎን የሚያረጋግጡ 2 ሰነዶች በመቅረፅ ለዘርፉ 5000 አመራሮችና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት ያልተማከለ አስተዳደርን በማጠናከር የህዝብ ባለቤትነት እና ተሳትፎ 33 በመቶ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 4.1 | | የከተማ የሕዝብ ተሳትፎና ንቅናቄን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል የህዝብ አደረጃጀት፣ የልማት ፕሮጀክት አዘገጃጀት፣ የሃብት አሰባሰብና አስተዳደር እና የምዘና ስነ-ምግባር ተጠያቂነት ጋይድላይን 2 ሰነዶች በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ | የተዘጋጁ ጋይድ ላይን ሰነዶች በቁጥረው | 2 | 2 | 100 | 1የማስፈፀሚያ ሰነድም ተዘጋጅቷል |
| 4.2 | | በከተሞች በኅብረተሰቡና በመንግስት የሚካሄዱ የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች ኅብረተሰቡ በገንዘብ፣ በጉልበትና በእውቀቱ 33% አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማድረግ፣ በዚህም የሴቶችን ተሳትፎ 50% እንዲደርስ ማድረግ፣ | የተደረገ የህዝብ አስተዋፅኦ በመቶኛ | 30 | 30 | 100 | |
| | | | የሴቶች ተሳትፎ መጠን በመቶኛ | 35 | 0 | 0 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.3 | | 5000 የከተማ ምክር ቤት አባላት፣ አመራሮችና ባለሙያዎች በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ | ግንዛቤ ያገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች ብዛት | 5000 | 5000 | 100 | |
| 4.4 | | በየዓመቱ የሚከበረውን የከተሞች ሳምንት በዓል በህዝብ ንቅናቄ በማክበር የተወዳዳሪ ከተሞችን ቁጥር 2005 ዓ.ም ካለበት 132 ወደ 150 እንዲደርስ ማድረግ፣ | በከተሞች ሳምንት በዓል ላይ የተሳተፉ ከተሞች ብዛት በቁጥር | 150 | 182 | 121.33 | ተጨማሪ 6 ድርጅቶች ተሳትፈዋል |
| 4.5 | | ዲያስፖራው በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚያደርገውን ተሳትፎ ለማጠናከር አንድ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ ማድረግ። | የዳሰሳ ጥናት ሰነድ | 1 | 2 | 200 | |
| 5 | ግብ 19፡- የአገልግሎት ሰታንዳርዳይዜሽንና ምዘናን ማጎልበት | **የከተሞች ያልተማከለ መልካም አስተዳደር የፕሮጀክቶች 3 ማስፈፀሚያ ማዕቀፎችን አዘጋጅቶ በመተግበር አገልግሎቶች 80 በመቶ የሚሆኑት በታችኛው የመንግስት አስተዳደር እርከን እንዲሰጡ ይደረጋል።** | | | | | |
| 5.1 | | ያልተማከለ አደረጃጀትን ለማጠናከር የሚያግዙ 2 ማስፈጸሚያ/ የአሰራር ማንዋሎች ማዘጋጀት፣ | የተዘጋጁ ሰነዶች ቁጥር ብዛት | 2 | 2 | 100 | |
| 5.2 | | 60 ከተሞች የደረጃ ለውጥ እንዲያገኙ ማድረግ፣ 100 የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ህጋዊ የከተማነት ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፣ | የደረጃ ለዉጥ ያገኙ ከተሞች ብዛት በቁጥር | 45 | 3 | 6.67 | |
| | | | የከተማነት ዕውቅና ያገኙ የገጠር ማዕከላት ብዛት በቁጥር | 75 | 88 | 117.33 | |
| 5.3 | | በ50 ከተሞች ከሚሰጡት የከተማ አገልግሎቶች መካከል 80 በመቶ የሚሆኑት በታችኛው የመንግስት አስተዳደር እርከን እንዲሰጡ ማድረግ፣ | አገልግሎቶችን ወደታችኛው የመንግስት መዋቅር ያወረዱ ከተሞች ብዛት በቁጥር | 35 | 32 | 91.43 | |
| | | | ወደታችኛው የመንግስት መዋቅር የወረዱ አገልግሎቶች በመቶኛ | 60 | 37.5 | 62.5 | |
| | **የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት ላይ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ክፍተቶችን በአጣዳፊነት ለማሻሻል የሚከናወን ሥራ** | | | | | | |
| 6 | ግብ 28፡- የሕዝብ ተጠቃሚነትን ማጎልበት | **በተለዩ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ዙሪያ የዜጎች ቻርተር መሰረት ያደረገ የአገልግሎት ስታንዳርድ በማዘጋጀትና እንዲተገበር በመደገፍ፣ የህዝብ መድረክ በመፍጠር ከነዋሪው ጋር በተለዩ አጀንዳዎች ዙሪያ ውይይት እንዲካሄድ በማድረግ እና ሕዝቡ መብቱ የተጓደለበት ጊዜ ቅሬታ የሚያሰማበት ስርዓት በመፍጠር በከተሞች ያለውን የመልካም አስተዳደር ዙሪያ ፈጣን ለውጥ እንዲመጣ ይደረጋል።** | | | | | |
| 6.1 | | የዜጎች ቻርተርን መሠረት ያደረገ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት ስታንዳርድ በማዘጋጀት በከተሞች የሚሰጡ አገልግሎቶች እንዲሻሻሉ ማድረግ፣ | ተግባራዊ የተደረገባቸው ከተሞች ብዛትበቁጥር | 43 | 0 | 0 | የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርዶች ባለመፅደቃቸው ወደ ትግበራ አልተገባም |
| 6.2 | | የሕዝብ መድረክ በመፍጠር፣ ከሕዝቡ ጋር በመወያየትና መግባባት በመፍጠር የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲቀረፉ ማድረግ፣ | ተግባራዊ የተደረገባቸው ከተሞች ብዛት በቁጥር | 43 | 0 | 0 | |
| 6.3 | | በከተሞች የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት በመዘርጋት ከሕዝቡ የሚቀርቡ ቅሬታዎች እንዲፈቱ በማድረግ የህዝብ እርካታና አመኔታ እንዲጎለብት ማድረግ። | ተግባራዊ የተደረገባቸው ከተሞች ብዛት በቁጥር | 43 | 0 | 0 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽን፣ የአፈጻጸም ክትትልና ምዘና ሥራ** | | | | | | |
| **7** | **ግብ 19፡- የአገልግሎት ሰታንዳርዳይዜሽንና ምዘናን ማጎልበት** | **ከተሞቻችን ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቁ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲችሉ 12 ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት በ12 ከተሞች እስከታችኛው የመንግስት መዋቅር ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡** | | | | | |
| 7.1 | | ለማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርድ ዝግጅትና ትግበራ መነሻ የሚሆን በ8 አገልግሎቶች መረጃ (Baseline data) በማሰባሰብና በማደራጀት ለ12 ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርድ ማዘጋጀት፣ | የተዘጋጁ የስታንዳርድ ሰነዶች ብዛት በቁጥር | 12 | 12 | 100 | |
| 7.2 | | የአገልግሎት ስታንዳርዶችን ለመተግበር የሚያስችል ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንዲቻል ከፌዴራል፣ ከክልሎችና ከከተሞች ለተውጣጡ 251 ተሳታፊዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣ | የሰለጠኑ አመራሮችና ባለሙያዎች በቁጥር | 251 | 26 | 10.4 | |
| 7.3 | | የተዘጋጁ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን ወደታችኛው የመንግስት መዋቅር በማውረድ በ12 ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ፡፡ | አገልግሎቶችን ወደታችኛው የመንግስት መዋቅር ያወረዱ ከተሞች ብዛት በቁጥር | 12 | 0 | 0 | |
| **8** | **ግብ 19፡- የአገልግሎት ሰታንዳርዳይዜሽንና ምዘናን ማጎልበት** | **በከተሞቻችን ግልፅ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው አሰጣጥን ለማስፈን አንድ የምዘና ማንዋል በማዘጋጀት በ132 ከተሞች የአገልግሎት አፈፃፀም ምዘና እንዲካሄድና 2 ስኬታማ ተሞክሮዎችን በመቀመር በ27 ከተሞች እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 8.1 | | የከተማ አገልግሎት አፈጻጸም ምዘና ለማካሄድ የሚያስችል የምዘና መለኪያ መሥፈርቶችና የማስፈፀሚያ ማኑዋል ሠነድ ማዘጋጀት፣ | የተዘጋጁ ሰነዶች ብዛት በቁጥር | 2 | 2 | 100 | |
| 8.2 | | የከተማ አገልግሎቶች አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችል ሥልጠና ከፌዴራል፣ ከክልሎችና ከተሞች ለተውጣጡ 256 ታሳታፊዎች መስጠት፣ | የሰለጠኑ አመራሮችና ባለሙያዎች ብዛት በቁጥር | 256 | 26 | 10 | |
| **3** | **የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች** | | | | | | |
| **3.1** | **የከተማ ኘላን መሬት አጠቃቀም ሥራዎች** | | | | | | |
| **3.10** | **ግብ 2፡-የማስፈጸሚያ ሥርዓቶችን ማሻሻል** | **በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ፕላን ተቋማት የፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን በተሟላ መልኩ ለማከናወን የሚያስችላቸውን አቅም ለማጎልበት 67 የተለያዩ የሕግ ማቃፎች እና የአሰራር ማኑዋሎች በማዘጋጀት ትግበራቸውም ላይ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 3.1.1 | | የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ሥራዎች በተሟሉ የህግ ማዕቀፎች እና ማኑዋሎች መሰረት እንዲከናወን 16 የሕግ ማዕቀፎች፣ 33 የአሰራር ማኑዋሎች፣ 6 ስታንዳርድ ማዘጋጀት እና 12 ጥናቶችን ማካሄድ፣ | የተዘጋጀ የህግ ማዕቀፍ ሠነድ ብዛት በቁጥር | 6 | 4 | 66.67 | |
| | | | የተዘጋጀ የማኑዋል ሠነድ ብዛት በቁጥር | 12 | 12 | 100 | |
| | | | የተዘጋጀ የስታንዳርድ ሠነድ ብዛት በቁጥር | 2 | 1 | 50 | |
| | | | የተካሄዱ ጥናቶች ሠነድ ብዛት በቁጥር | 9 | 9 | 100 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1.2 | | የሃገር አቀፍ የልማት ቀጠና እና የልማት ማዕከላትን ታሳቢ ያደረገ የከተማ ልማት ስኪም (National Urban Development Scheme) እና የአዲስ አበባ ከተማን ተወዳዳሪ ሆኖ ማስቀጠል የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፤ | የጥናቱ የአፈጻጸም ደረጃ በመቶኛ | 66 | 45 | 68 | |
| **3.20** | **ግብ 16፡- የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራን ማሻሻል** | **የከተማ ፕላን የተዘጋጀላቸው ከተሞች የፕላን አፈጻጸም በከተማ ፕላን አዋጅ፣ ስትራቴጂ፣ ማኑዋል እና ስታንዳርድ መሠረት ስለመሆኑ በ131 ከተሞች የክትትልና ግምገማ ሥራ በማከናወን ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡ የተሰጠው ግብረ-መልስ ተግባራዊ ስለመሆኑ በክትትል ይረጋገጣል፡፡** | | | | | |
| 3.2.1 | | በ61 ከተሞች የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም እንዲሁም የካርታና የቅየሳ አሃዶች እንደየከተሞቹ የእድገት ደረጃ ተቋማዊ የአደረጃጀት ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው ማድረግ፤ | በተዘጋጀ የክትትል ሪፖርት ብዛት በቁጥር | 9 | 9 | 100 | |
| 3.2.2 | | በ61 የከተማ ፕላን ዝግጅት ተቋማት የፕላን ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት በተዘጋጁ 149 ፕላኖች ላይም የጥራት ቁጥጥር በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣ | ስርዓቱ የተዘረጋላቸው ተቋማት ብዛት በቁጥር | 36 | 9 | 25 | |
| | | | የጥራት ቁጥጥር በተደረገላቸው ፕላኖች ብዛት በቁጥር | 90 | 30 | 33.3 | |
| 3.2.3 | | ከፌዴራል እስከ ከተሞች በሚገኙ የከተማ ፕላን ዝግጅት የአፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስን በሚያከናውኑ 148 ተቋማት ወጥ የሆነ የከተማ ፕላን መረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና ልውውጥ ሥርዓት ማጠናከር፤ | መረጃው የተደራጀላቸው ከተሞች ብዛት በቁጥር | 109 | 9 | 8.29 | |
| 3.2.4 | | የ84 ከተሞች መሠረታዊ መረጃዎችን (Urban Profile) በማሰባሰብና በማደራጀት በድረ-ገጽ (በኢ.ኮ.ቴ) ለተጠቃሚዎች ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ፡፡ | መሠረታዊ መረጃዎች የተዘጋጀላቸው ከተሞች ብዛት በቁጥር | 63 | 80 | 127 | |
| **3.30** | **ግብ 16፡- የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራን ማሻሻል** | **በክልሎችና በከተሞች በሚዘጋጁ 205 አነስተኛ ከተሞች መሰረታዊ ካርታና ፕላን፣ 35 መዋቅራዊና 119 የአካባቢ ልማት ፕላኖች እንዲሁም ለመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች በሚዘጋጁ 6 የመዋቅራዊና 6 አካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ በየሩብ አመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 3.3.1 | | በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች መሠረታዊ ካርታ እና መሠረታዊ የከተማ ፕላን ለሚዘጋጅላቸው 205 አነስተኛ ከተሞች አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ በየሩብ ዓመቱ በማካሄድ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፤ | መሠረታዊ ካርታ የተዘጋጀላቸው ከተሞች ብዛት በቁጥር | 100 | 130 | 130 | |
| | | | መሰረታዊ ፕላን የተዘጋጀላቸው ከተሞች ብዛት በቁጥር | 100 | 70 | 70 | |
| | | | የተዘጋጀ የግብረ-መልስ ሰነድ ብዛት በቁጥር | 100 | 3 | 3 | |
| 3.3.2 | | በ35 ከተሞች በሚዘጋጁ የመዋቅራዊ ፕላኖች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ በየሩብ ዓመቱ በማካሄድ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፤ | የተዘጋጁ መዋቅራዊ ፕላኖች ብዛት በቁጥር | 24 | 5 | 20.8 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.3.3 | | በከተሞች በሚዘጋጁ 119 የአካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ በየሩብ ዓመቱ በማካሄድ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፤ | የተዘጋጁ የአካባቢ ልማት ፕላኖች ብዛት በቁጥር | 80 | 52 | 65 | |
| 3.3.4 | | 10 የስኳር ልማት ፕሮጀክተች፣ 10 ዩኒቨርሲቲዎች እና 11 የማዳበሪያ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በሚሆኑባቸው ከተሞች በሚዘጋጁ 6 የመዋቅራዊና 6 የአካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፤ | የተዘጋጁ መዋቅራዊ ፕላኖች ብዛት በቁጥር | 4 | 2 | 50 | |
| | | | የተዘጋጁ የአካባቢ ልማት ፕላኖች ብዛት በቁጥር | 4 | 2 | 50 | |
| | | | የክትትልና ግብረ-መልስ ሰነድ ብዛት በቁጥር | 3 | 3 | 100 | |
| **3.40** | **ግብ 12፡-የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጎልበት** | **በከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ዙሪያ በተለያዩ መስኮች በዘርፉ ለተሰማሩ 522 አስፈጻሚዎች፣ ለ64 የከተማ ፕላን የግል አማካሪ ድርጅቶችና ባለሙያዎች፣ ለ3,179 ከተማ ከንቲባዎች፣ ሥራ አስኪያጆችና ባለሙያዎች እንዲሁም 664 የዘርፉ ባለሙያዎች በልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮችሥልጠና በመሥጠት የሙያ ብቃታቸው ያድጋል፡፡** | | | | | |
| 3.4.1 | | በ193 ከተሞች የከተማ አመራሮች ኘላኖችን በአግባቡ ተገንዝበው እቅድ እንዲያዘጋጁ ለማስቻል ከየከተሞቹ ለተውጣጡ 522 አስፈጻሚዎች ዕቅድ እንዲያዘጋጁ የሚያስችል ሥልጠና መስጠት፣ | የከተሞች ብዛት በቁጥር | 193 | 482 | 249 | |
| | | | ስልጠና ያገኙ ፈጻሚ ሰልጣኞች ብዛት በቁጥር | 522 | 996 | 190 | |
| 3.4.2 | | ለ3,179 ከተማ ከንቲባዎች፣ ሥራ አስኪያጆችና ባለሙያዎች ስለ ከተማ ኘላን አዘገጃጀትና አተገባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣ | ስልጠና ያገኙ ከንቲባዎች፣ ሥራ አስኪያጆችና ባለሙያዎችሰልጣኞች በቁጥር | 3179 | 2623 | 82.5 | |
| 3.4.3 | | በመንግስት ተቋማት በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ለተሰማሩ 664 ባለሙያዎች በሶሺዮ ኢኮኖሚ፣ በፊዚካል፣ በስፓሻል እና በጂ.አይ.ኤስ ሙያ ዘርፍ ስልጠና መስጠት፣ | ሥልጠና ያገኙ ሰልጣኞች ብዛት በቁጥር | 458 | 499 | 108.9 | |
| 3.4.4 | | በከተማ ፕላን ስትራቴጅዎች ዙሪያ በአካልና በፕላዝማ አማካይነት ለ12,200 ያህል መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ተሳታፊዎች አገር አቀፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ማከናወን፣ | በግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሙ የተሳታፊዎች ብዛት በቁጥር | 12200 | 0 | 0 | |
| 3.4.6 | | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፓይለት ደረጃ የመሬት ላይ የቅየሳ ዘዴን በመጠቀም ከከተማው ለተውጣጡ 75 የቅየሳ ባለሙያዎች በ25 ቡድኖች/አሃዶች በአማካሪነት እንዲደራጁ ድጋፍ መስጠት፣ | የተደራጁ አሀዶች ብዛት በቁጥር | 25 | 0 | 0 | |
| 3.2 | **የከተማ መሬት ልማት፣ ማኔጅመንት እና አስተዳደር ሥራዎች** | | | | | | |
| 1 | **ግብ 13፡- የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ማሻሻል** | **ለ360 ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ ወሰን እንዲኖራቸዉ እና 10,921 ሄክታር መሬት ተቆጥሮ እንዲመዘገብ በማድረግ በጊዜያዊነት ለማዕድን ማውጫ፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ፣ ለከተማ ግብርና እና የእርሻና የግጦሽ መሬቶች እየተጠቀሙ ለሚገኙ 2,919 ተጠቃሚዎች ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡** | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዕቅድ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.1 | | የከተማነት እውቅና ከተሰጣቸው ከተሞች ውስጥ ለ360 ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ ወሰን እንዲኖራቸዉ በማድረግ የመሬት ሃብታቸውን በሚገባ ማስተደደርና መጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ፣ | ወሰን የከለሉ ከተሞች ብዛት በቁጥር | 250 | 215 | 86 | |
| 1.2 | | በ360 ከተሞች የከተሞች የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ ሥርዓት መሠረት 10,921 ሄክታር መሬት ተቆጥሮ እንዲመዘገብ ማድረግ፣ | የተመዘገበ መሬት በሄክታር | 7,000 | 6687 | 95.53 | |
| 1.3 | | በከተሞች የአስተዳደር ወሰን ውስጥ በጊዜያዊነት ለማዕድን ማውጫ፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ፣ ለከተማ ግብርና እና የእርሻና የግጦሽ መሬቶች እየተጠቀሙ ለሚገኙ 2,919 ተጠቃሚዎች ጊዚያዊ የመጠቀሚያ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ማድረግ፡፡ | ጊዚያዊ የመጠቀሚያ ሰነድ ያገኙ ተጠቃሚዎች ብዛት በቁጥር | 1,500 | 1300 | 86.67 | |
| 2 | ግብ 13፡- የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ማሻሻል | **የደቀቁና የተጎሳቆሉ የከተማ አካባቢዎችን ከ45% ወደ 35% በመቀነስ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 231 እና በሌሎች አካባቢዎች 6,100 ሄክታር መሬት መሠረተ ልማት ተሟልቶለት እንዲዘጋጅ በማድረግ 13 የኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 2.1 | | በተለያዩ የከተማ አካባቢዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 6,100 ሄክታር መሬት መሰረተ ልማት ተሟልቶለት እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ | መሰረተ ልማት ተሟልቶለት የተዘጋጀ መሬት በሄክታር | 3,500 | 9226.16 | 263.60 | |
| 2.2 | | የደቀቁና የተጎሳቆሉ የከተማ አካባቢዎችን ከ45% ወደ 35% ለመቀነስ በ5 ፕሮጀክቶች 231 ሄክታር መሬት በተቀናጀ የመልሶ ማልማት ሥራ እንዲለማ ማድረግ፣ | መሬት የተዘጋጀላቸው የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች ብዛት | 6 | 5 | 83 | የመሬት ዝግጅቱ በሂደት ላይ ያለ(ነዋሪን ማወያየት፣መረጃ መሰብሰብ) |
| 2.3 | | በከተሞች 13 የኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲለሙ ማድረግ፡፡ | የተከለሉ የኢንዱስትሪ ዞኖች ብዛት በቁጥር | 6 | 5 | 83 | |
| | | | የለሙ የኢንዱስትሪ ዞኖች ብዛት በቁጥር | 6 | 5 | 83 | |
| 3 | ግብ 15፡- የመሬትና መሬት-ነክ ግብይትን ማሳደግ | **በከተሞች ያሉ ሰነድ አልባ እና ህገ ወጥ ይዞታዎች ሥርዓት እንዲይዙ በማድረግ፤ የመሬት ኪራይ፣ የቤት ግብር ተመን እና የሊዝ መነሻ ዋጋ ዝግጅትና ክለሳ በማካሄድ፣ 233 ከተሞች ወደ ሊዝ ስሪት እንዲገቡ በማድረግ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል 5,573 ሄክታር መሬት በጨረታ እና በምደባ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
| 3.1 | | በከተሞች ያሉ ሰነድ አልባ እና ህገ-ወጥ ይዞታዎች 100% ሥርዓት እንዲይዙ ማድረግ፣ | ህጋዊ የሆኑ ሰነዶች በመቶኛ | 50 | 61 | 1.22 | |
| 3.2 | | በ42 ከተሞች ነባር የይዞታ ማህደሮች እንዲደራጁ ማድረግ፣ | ነባር የይዞታ ማህደሮች እንዲደራጁ የተደረገባቸው ከተሞች ቁጥር | 20 | 67 | 3.35 | |
| 3.3 | | ሊዝ ተግባራዊ ያልተደረገባቸው 233 ከተሞች ወደ ሊዝ ስሪት እንዲገቡ ማድረግ፣ | ወደሊዝ ስሪት የገቡ ከተሞች ብዛት | 100 | 412 | 4.12 | |
| | | በከተሞች የመሬት ኪራይ፣ የቤት ግብር ተመን እና የሊዝ መነሻ ዋጋ ዝግጅትና ክለሳ ማድረግ፣ | የሊዝ መነሻ ዋጋ የከለሱ ከተሞች በቁጥር | 26 | 67 | 257.69 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዒላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.4 | | | የሊዝ መነሻ ዋጋ ያዘጋጁ ከተሞች በቁጥር | 100 | 412 | 412 | |
| | | | የመሬት ኪራይ፣የቤት ግብር ተመን የከለሱ ከተሞች በቁጥር | 235 | 242 | 103 | |
| 3.5 | | በከተሞች ለተለያየ አገልግሎት የሚውል 5,573 ሄክታር መሬት በጨረታና በምደባ በማስተላለፍ በውሉ መሰረት ስለመፈፀማቸው ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣ | ለተለያዩ አገልግሎቶች የተላለፈ መሬት በሄክታር | 2,500 | 4661.87 | 186 | |
| **4** | | **የመሬት ልማትና ማናጅመንት ፕሮግራምን ላይ የአመራሩንና የፈጻሚውን ግንዛቤ በማሳደግ በከተሞች ስታንዳርዱን የጠበቀ 146,059 የግንባታ ፈቃድ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡** | | - | | | |
| 4.1 | **ግብ 12፡-የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጎልበት** | የመሬት ልማትና ማናጅመንት ፕሮግራምን ለማስፈጸም የሚያስችሉ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ለ317,023 አመራሮች እና ፈጻሚዎች (30% ሴቶች) ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣ | ግንዛቤ ያገኙ ተሳታፊዎች በቁጥር | 317023 | 249 | 0.08 | |
| 4.2 | **ግብ 13፡- የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ማሻሻል** | በከተሞች 146,059 ስታንዳርዱን የጠበቀ የግንባታ ፈቃድ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ማድረግ፣ | የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ብዛት በቁጥር | 97373 | 0 | 0 | |
| 4.3 | **ግብ 23፡- ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት** | በተሰጡ የግንባታ ፈቃዶች አፈፃፀም ላይ በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡ | በግንባታ ፈቃዶች ላይ የተሰጠ ግብረመልስ ሠነድ | 3 | 0 | 0 | |
| **3.3** | **የተቀናጀ መሬትና መሬት ነክ መረጃና ቴክኖሎጂ ሥርዓት ዝርጋታ ሥራዎች** | | | | | | |
| **7.1** | **ግብ 14፡- የመሬትና መሬት-ነክ ምዝገባን ማጎልበት** | **በ23 ከተሞች 1,846 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመዘርጋት እንዲሁም የአየር በረራ የተደረገባቸው ከተሞችና በሳተላይት ስትሪዮ ምስል 44 የከተሞች መሰረታዊ ካርታ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለከተሞች የአድራሻ ሥርዓት ትግበራ መሰረት የሚጥል አንድ ስታንዳርድ እና ማኑዋል ይዘጋጃል፡፡** | | | | | |
| 7.1.1 | | በ23 ከተሞች 1,846 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች እንዲተከሉ ማድረግ፣ | በከተሞች የተዘረጉ የቅየሳ ነጥቦች በቁጥር | 1384.5 | 1158 | 83.6 | |
| | | | የቅየሳ ነጥቦች የተዘረጋባቸው ከተሞች በቁጥር | 16 | 11 | 68.75 | |
| 7.1.2 | | ለከተሞች የአድራሻ ሥርዓት ትግበራ መሰረት የሚጥል ስታንዳርድ እና ማኑዋል ማዘጋጀት፡፡ | የተዘጋጀ የአድራሻ ሥርዓት ትግበራ ስታንዳርድ ብዛት በሰነድ | 1 | 1 | 100 | |
| **7.20** | **ግብ 12፡-የዘርፉን የሰው ኃይል ማፍራትና አቅም ማጎልበት** | **በከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ዘርፍ ያለውን የሰው ሀይል እጥረት ለማቃለል እንዲቻል በስድስት ተቋማት በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በማስተርስ እና በፒኤችዲ 3 ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ ተግባራዊ ይደረጋል፤ ስልጠናም ይሰጣል፡፡** | | | | | |
| 7.2.1 | | በከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ዘርፍ በስድስት ተቋማት በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በማስተርስ እና በፒኤችዲ 3 ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ፡፡ | ስርአተ ትምህርት የተቀረጸላቸው ደረጃዎች ብዛት በቁጥር | 3 | 3 | 100 | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግቦች | የፕሮግራም ግብና ተግባራት | የውጤት አፈጻጸም አመላካቾች | የ9 ወር ዓላማ | ክንውን | ንጽጽር በ% | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7.2.2 | | የመሬት ልማትና ማናጅመንት ፕሮግራምን ለማስፈጸም የሚያስችሉ 242 የመሪ መዛኝነት ስልጠናና ምዘና፣ 1,711 የአጭርና 1,225 የመካከለኛ ጊዜ የሰው ኃይል እንዲሰለጥን ማድረግ፣ ከዚህ ውስጥ 30% ሴቶች እንዲሆኑ ማድረግ፡፡ | የሰለጠኑ መሪ መዛኞች ብዛት በቁጥር | 242 | 0 | 0 | |
| | | | የአጭር ጊዜ ስልጠና ያገኙ ሰልጣኞች ብዛት በቁጥር | 1450 | 986 | 68 | |
| | | | የመካከለኛ ጊዜ ስልጠና ያገኙ ሰልጣኞች ብዛት በቁጥር | 1225 | 685 | 55 | |
| 7.3 | **ግብ 4፡- የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት፣ ልውውጥና ደህንነት ማሻሻል** | **የተቀናጀ የከተማ መሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ የመረጃ ሥርአት ለመዘርጋት እንዲቻል የቅየሳ መረጃ አያያዝ ስርዓት እና መረጃ ቋት በ42 ከተሞች በማዘጋጀት በመሬት ቆጠራ፣ የሊዝ ውል ክትትል እና የመሬት ኪራይ የቤት ግብር ትመና 2 ሶፍትዌሮች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡** | | | | | |
